# የእምነቴ ፈተና

ከ
ደበበ እሸቱ

መጋቢት 2000 ዋሽንግተን ዲሲ

አሳታሚ
ሊንክ ግሎባል
1334 9th St.NW
Washington DC 20001-4251
info@linkglobal.biz

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።©2000
ይህን ሥራ በማንኛውም መልኩ ማባዛት መገልበጥም ሆነ በተለያየ ዘዴ
ለመጠቀም በቅድሚያ የባለመብቱን ፈቃድ በጽሑፍ ማግኘትያስፈልጋል

ስለ ደራሲው 4
መግቢያ 8
ለምን ወደ ፖለቲካ 12
ጉዞ ወደ ቀስተ ደመና 18
የምርጫ ዝግጅት 22
የዓላማና የሃገር ፍቅር እምነቱ በፈተና ውስጥ 24
የምርጫ ዘመቻ 29
ከስብሰባዎች ናሙናዊ እይታ 34
ከደሴ ወደ አዲስ አበባ 46
ወደ ቅንጅት ጉዞ 50
ዶ/ር ብርሃኑ ስለ መቀናጀት 51
ገዢው ፓርቲና የምርጫ ስልቱ ምላሽ 58
የፖለቲካ ዳጥ፣ አንሸራቶ ጉልበት ይቀጠቅጥ 62
ውሃ ቢወቅጡት እምቦጭ 70
ከአረንቋ ወደ አረንቋ 75
ወደ ወልቂጤና አካባቢው 78
ሚያዝያ 29 80
እንደፈርዖን ጦር ...... በቅንጅት ሱናሚ ተዋጠ 85
የፓርቲና የመንግሥት መገናኛ ብዙሃን 98
ቅንጅት ስለወታደሩ 101
ሕዝባዊ ስብሰባዎች 108
ስብሰባ በናዝሬት 129
የመከራ ዋዜማ 136
የጨነቀው እርጉዝ ያገባል... 141
ቀኑ ደረሰ 147
ምርጫ 97 149
ሰቆቃወ ሰኔ 160
«አልቅሺ ዝም ክምል» 175
አዲስ ክስተት 191
የትዝብትና የማስጠንቀቂያ ደብዳቤዎች 203
ማጅራት መቺ ይመስል? 224
ውህደት 232
የትግል ሰላማዊ ጥሪ 247
የድል ጮራ 270
እስር በእለተ አርብ 285
የውህደት ክህደቱ በነአቶ ልደቱ 300
ምርጫ መጭበርበር ያስነሳቸው ጥያቄዎች 320
ፖርላማ መግባትና አለመግባት 340
ወደ ድምሳሴ ቅንጅት 359



ወደ ቃሊቲ 381
ኑሮ በ ቃሊቲ 389
ወደ ፖሊስ ሆስፒታል 395
የቃሊቲ 2ኛ ወንጀል ችሎት 410
የግለሰቦች ለአስተያየት በክሱ ላይ 443
«ግልጽ ደብዳቤ» (በረከተ መርገም) 451
የፍርድ ሂደቱ 457
ፍትሕ ገደል የገባበት እለት 476
«በሕግ ዓምላክ» 496
ወዳጆቼ ለነበራችሁ 504
ድመቶቼ 519
መደምደሚያ 526

ከመስቀል አደባባይ የተነሱት የቅንጅት የድጋፍ ሰልፎች ፎቶግራፍ በሙሉ እንዳርጋቸው ፅጌ ያነሳቸው ናቸው::

ይህን መጽሐፍ ለማሳተም በማዘጋጅበት ወቅት ለማተሚያ ቤቱ በሚሆን መልኩ ለማዘጋጀትና ሽፋኑን በመሥራት እርዳታውንና ድጋፉን ያደረገልኝን መዋ ብርሃነን ከልብ ላመሰግን እወዳለሁ::

## ስለደራሲው

### ዓለም ፀሐይ ወዳጆ

ይህን ስመ ጥር ባለሙያ ለመጀመርያ ጊዜ ያየሁት ገና የ16 ዓመት ልጅ ሆኜ ከትምሕርት መልስ የሬዲዮ ቴአትር በዕውቁ ባለ ሙያ በወንድወሰን ገብረ ኢየሱስ አዘጋጅነት ለመሣተፍ ማስታወቂያ ሚኒስቴር ግቢ ውስጥ ሄጄ ነው፡፡ሕይወታችን በጥበብ የተጣመረ ነውና ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፡በመምሕርነት፤በአዘጋጂነት፤፡አልፎም፡በጓደኝነት፤በወን ድምነት እስከዛሬ በሕይወቱ ጎዳና ዘልቆ እነሆ ከ30 ዓመታት በላይ ቆየን፡፡በጣም ከሚያውቁትና ከሚያውቁኝ አንዱ ነውና ለምስክርነት እንበቃቃለን፡፡

ውቅያኖስ ከሆነው ታሪኩ ጨልፌ ትንሽ ላካፍላችሁ፡-
ጋሽ ደበበ፤ደቤ፤ደቢሾ!

የትወና ችሎታው ገና ከአዲስ አበባ ባሕል ማዕከል ጀምሮ የተስተዋለ ቢሆንም፤ሀንጋሪ በትምሕርት አጎልብቶ ከተመለሰ በኋላ ነው በሙያው ብርሃን መላውን የኢትዮጵያን መድረክ ያሞቀው፡፡ይህ ትልቅ የኪነጥበብ ባለሙያና አርበኛ፤ ይህ የወገንና የአገር አለኝታ አንቱታን ለማግኘት የበቃው እጅግ ብዙ የሙያ የሥራና የትግል ውጤቶችን ካስመሰከረ በኋላ ነው፡፡

በሙያው የእውቅ ደራሲያንን የነሎሬት ጸጋዬ ገብረመድህንን የነመንግሥቱ ለማን የነመስፍን ዓለማየሁንና የሌሎቹንም በመተወን ተደምጦ በማይጠገበው ጉልሕ ድምጹ አዳራሹን ሲያሞቀው፤ በችሎታው መድረኩን ሲያደምቀው ለኢትዮጵያ የኪነጥበብ ሞያ ለተመልካች ከተሰጡት ውድ ስጦታዎች ውስጥ አንዱ መሆኑ ተረጋገጠለት፡፡

ደበበ ከብዙዎቹ በፊት ችሎታውን አስመስክሮ ስመ ጥር የሆነው በሃገሩ መድረክ ብቻ ሳይሆን በአፍሪካ በአውሮፓና በአሜሪካም ጭምር ነው፡፡እንጋፋው ከያኒና አርበኛ ደበበ እሸቱ፤በተለያዩ ዘርፎች ተሰጥኦ ያደለችው ለመሆኑ፤በድርሰቱ ውስጥ፤የተዋነዩት፤በዝግጅቱ የተሳተፉት፤ በትወናው የረኩት፤በመምህርነቱ ያደጉት በሙሉ የሚመሰክሩት ነው፡፡



በአዘጋጅነት ችሎታው የደራሲ መንግሥቱ ለማን «ጠያቂ» የተስፋዬ ገሰሰን «ተሐድሶ»የአያልነህ ሙላቱን «ሻጥር በየፈርጁ»የነጋሽ ገብረማርያምን «የእዛውንቶች ክበብ»የዊሊያም ሼክስፒርን(የመስፍን ዓለማየሁን ትርጉም) «ሊር ነጋሲን» ክሸን አድርጎ ማቅረቡ ለምሳሌ ያህል ቢጠቀሱ ይበቃል፡፡በሥነ ጽሁፍ ዘርፍ ደግሞ፤ወጣት የኪነጥበብ ባለሙያዎችን ካፈራበት ከስታንስላቭስኪ የመጽሐፍ ትርጉም «ከተዋናይ ሀ ሁ» ጀምሮ የሻለቃ ዳዊት ወልደ ጊዮርጊስን «የደም እንባን» ከተውኔት «ድብልቅልቅ»ን «ያልታመመው በሽተኛን» ማውሳቱ ለዋቢነት ይበጃል፡፡

በዓለም አቀፍ የሲኒማ ጥበብ ውስጥ ቀድመውና በብዛት ከተሳተፉት ኢትዮጵያዊያን ባለሙያዎች ብቸኛው ደበበ እሸቱ ነው፡፡ከሪቻርድ ራውንድ ትሪና ከሰር ፍራንክ ፊንሊ፤ከቴሬንስ ስታምፕ፤ከጃን ሞሮና ከሂዩ ግሪፊዝ፤ከሶፍያ ሎሬን ጋር ከተሳተፈበት «ሻፍት ኢን አፍሪካ» «ዘ አፍሪካን ስፓይ» «ዘ ሴይለር ፍሮም ጂብራልታር» «ኤ ሲዝን ኢን ሄል» «ዜልዳ» «ዘ ግሬቭ ዲገር» « ዘግራንድ ሪቤሊየን» የመሳሰሉት ድንቅ ሥራዎችን ያካትታል፡፡በዚህ ጉልህ ሙያው የተለያዩ ሽልማቶችንና ስጦታዎችን ያገኘ ሲሆን በአሜሪካ አትላንታ ከተማ «ኖቬምበር 24» የደበበ ቀን ተብሎ ተሰይሟል፡፡

ደበበ የማስተባበር ችሎታው የተነገረለት ብቻ ሳይሆን የተከበረበትም ጭምር መሆኑን የሚያሳየን የአፍሪካ መድረክ ባለሙያዎች ማሕበርን በመመሥረትና ሊቀ መንበር በመሆን ያገለገለ ሲሆን በዩኔስኮ የዓለም ኮንቴምፖራሪ ቴአትር ኢንሳይክሎፒዲያ ኤዲቶርያል ቦርድ አባል በመሆን ሠርቷል፡፡የዓለም አቀፍ ቴአትር ኢንስቲቲዩት (ITI) የአፍሪካ አስተባባሪ፤ የኢትጵያ ሰብሳቢና የሌሎችም አህጉራዊና ዓለማ አቀፋዊ ድርጅቶች አባልና መሪ በመሆን አገልግሏል፡፡ኤች አይቪ ኤይድስን በቴአትር ጥበብ ለመከላከል በተደረገው ዓለም አቀፍ ዘመቻ አስተባባሪ በመሆን ውጤታማ ሥራዎችን አስመዝግቧል፡፡

በሃገሩ በኢትዮጵያ፤የብሔራዊ ቴአትር የፕሮግራምና ፕሮዳክሽን ኃላፊ፤የራሥ ቴአትር ዋና ሥራ አስኪያጅ፤በሃገር ፍቅር ቴአትር የኪነጥበብ አገልግሎት ሃላፊ ሆኖ ሠርቷል፡፡

ደበበ እንደሰው እሩህሩህ ና አዛኝ፤እንደወንድም፤ጋሻ እንደጓደኛ ጽኑ ነው፡፡እንደአባት ከአብራኩ ከወጡት

ውጤታማ ልጆቹ በተጨማሪ የብዙ ከያኒ ባለሙያዎች አባት ነው::

ከእያንዳንዱ ውጤታማና ጀግና ወንድ ጀርባ ጠንካራ ሴት አለች እንደሚባለው የ32 ዓመት የትዳር ጓደኛው አልማዝ ደጀኔ የእሱን ክብርና ውጤት ልትካፈል ይገባታል::

በሬዲዮ በቴሌቪዥን በተለያዩ የሕብረተሰብ የልማትና እርዳታ አገልግሎቶችና ዝግጅቶች ያበረከተው የዕድሜ ልክ ሥራው ልዩ ክብርና ደረጃን እንዲጎናጸፍ አድርጎታል::ይህ ተናግሮ የማሳመን ችሎታው፤ይህ ልዩ ተሰጥኦው እንደገና ለሀገርና ለወገን እንዲውል ወስኖ የኢትዮጵያን ሕዝብ ከመከራ ገፈትና ከችግር ለማላቀቅ ወደ ትግል ተሠማራ:: አገሩ ነጻነቷን ተጎናጽፋ ሰላምና ዴሞክራሲ የሰፈነባት ሕዝቦች በእኩልነትና በአንድነት የሚኖሩባት እንድትሆን ለማድረግ በቆራጥነት ከቆሙት ጋር አብሮ በማበር የእውነትን መንገድ መረጠ::ይህ ጎዳና ረጅምና መራር በመሆኑ በሚከበርበት ዕድሜው እንደልጅ ተደበደበ::በሙያ ደረጃው በአደባባይ እንደጌጥ በሚታይበት ወቅት በጨለማ ክፍል ውስጥ ተወረወረ::በሥራ ልምዱ በሚሸለምበትና በሚወደስበት ጊዜ ላይ በየፍርድ ቤቱ ተጉላላ::በሠለጠነው ዓለም መሰል የሙያ ጓደኞቹ «ሰር » የሚባል ማዕረግና «ላይፍ ታይም አቺቭመንት አዋርድ» በመሪዎቻቸውና በድርጅታቸው ለስማቸው ሲታከልላቸውና ሲበረከትላቸው እሱ ግን ባለመታደል ለዚህ አልበቃም::ይሁንና፤ኢትዮጵያ ጥበብ በነጻነት እስኪቀርብባት፤ሕዝቦቿ በጤናና በሠላም፤ በነጻነት በእኩልነትና በአንድነት እስኪኖሩባት እሱም ሆነ ሌሎች ቆራጥ ልጆቿ ትግላቸው አያበቃም::

እነሆ ከምርጫ 97 እስከ ቃሊቲ እሥራት ያለውን ትዝታውን «የእምነቴ ፈተና» (የሃገር የወገን ፍቅርና የዓላማ እምነቴ በፈተና ውስጥ) የሚለውን መጻሐፉን ጀባ ብሎናል!!

## <u>አንዳርጋቸው ጽጌ</u>

በምርጫ 97 ወቅት በስልጣን ላይ ያለው ገዥ ፓርቲ የመንግስት ጋዜጣ፣ ሬድዮንና ቴሌቪዥን በእጁ ስለነበረ 24 ሰአት ሙሉ የፓርቲውን ፕሮፓጋነዳ ሲነፋበት፣ ተቃዋሚዎቹን ሲያጥላላበት፣ ሲከሰበትና ሲያወግዝበት ቢውል ተቀጣጣሪ



አልነበረውም። ደበበ ደግሞ በቀን ውስጥ በገዥው ፓርቲ መልካም ፈቃድ ተቆንጥራ የምትሰጠውን የደቂቃዎች የአየር ግዜ አብቃቅቶ የገዠውን ፓርቲ ጥቃት መክቶና የቅንጅትን መልእክት ማስተላለፍ ነበረበት። ትግሉ የጎሊያድና የዳዊት አይነት ነበር። ደበበ እንደ ዳዊት ጎልያድን ዘርሮታል። የአርቲስት ሙያተኛነቱ የሰጠውን የፈጠራ ችሎታ በመጠቀም ለሰአታት የሚካሄደውን የገዥውን ፓርቲ የቸከ ፕሮፓጋንዳ ዶጋ አመድ አድርጎታል። ለምርጫ 97 ድል በደበበ ተጽፎ በእሱ ተነቦና ተቀናብሮ በቴሌቢዥንና በሬድዮ የተላለፈው የቅንጅት መልእክት ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ነው። በትንሽ ደቂቃዎች የሚተላለፍ ምልእክት ማዘጋጀት በጣም ከባድ ነበር። ተጽፎ የሚቀደደው ተቀርጾ የሚሰረዘው ብዙ ነው። በእዚህ ላይ የሰአት ገደብ አለ። ደበበ ጸጉሩን ነጭቶ የጨረሰው በእዚህ የምርጫ ወቅት ይመስለኛል። ከሁሉ የሚደንቀው ግን በእዚህ ሁሉ ወከባ መሃል ግዜ አግኝቶ የምርጫውን ታሪክ ለመጻፍ አስቀድሞ ቁርጠ መነሳቱ ነው። ቅንጅት ቢሮ በምመላለብት በእዚያ የምርጫ ወቅት ደበበ ከሌላው ስራው ጋር ደምሮ የምርጫ 97ን ሂደት ቀን በቀን ይመዘግብ ነበር። ስለታሪክ የተሰጠ ስሱነት ይሏል ይህ ነው። ያሰበው አልቀረም ከምረጫ 97 ጀምሮ ሲከትበው የነበረው ጽሁፍ ዛሬ መጸሃፍ ሆኖ ወጥቷል። ስለምርጫው የተጻፉ ወደፊትም የሚጻፉ በርካታ መጽሃፎች ይኖራሉ። የደበበ ግን ሁሌም የተለየ እንደሆነ ይዘልቃል። ምክንያቱም ይህ መጽሃፍ የተጻፈው እንደ ፖለቲከኛ እንደ ታሪክ ተመራማሪ አይደለምና። ጸሃፊው የነጻነት እሳት በውስጡ የሚንቦገቦግ፣ ያለነጻነት እንደ ሰው ብቻ ሳይሆን በሙያውም ጭምር የሚሞት እንደሆነ የተረዳ ሃገር ወዳድ አርበኛ ነውና!።

አንዳርጋቸው ጽጌ

# በወቅቱ ለመግቢያ ያዘጋጀሁት

የኢትዮጵያ ሕዝብና ተቃዋሚ ፓርቲዎች በፈጣሪ ኃይልና በሕዝቡ የአንድነት ጥንካሬ የ97ን ምርጫ አሸንፈዋል:: ይህ ድል የተገኘው በጉቦ፣ በወከባ፣ በዱላ፣ በማስፈራራት፣ በእስርና በጉልበት ሳይሆን ፈጣሪ በለገሰው ሕዝባዊ ጥንካሬ ነው::

የሕዝቡ መሳሪያ፣ አንድነትና የፈጣሪ ፈቃድ ብቻ ነው:: ፈጣሪ ደሞ የሕዝብን ጩኸት፣ ዋይታ፣ የመከራውን እሮሮ ብቻ ሰምቶ፣ በላያችን ላይ የተጫነውን የግፍ አገዛዝ ለማንሳት የሚያስፈልገንን ጥንካሬና ሃይል ሰጠን:: ለሃገራችንና ለራሳችን ደህንነት፣ ብልጽግና፣ ነጻነትና ዴሞክራሲያዊ መብት መረጋገጥ ለሰብአዊ መብታችን በብርታት ቆመን የማስከበር አቅማችንን ማጠናከር አለብን::

ከዚህ በመነሳት ምን ማድረግ ይጠበቅብናል? በውጪ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ወገኖች ይህን ሁኔታ ከግንዛቤ በማስገባት ቀደምት እርምጃቸውን ወስደዋል:: የኮንግሬስ አባላትን በማሳወቅ፣ የተለያዩ ሃገራት ፓርላማዎችን በመቅረብና እውነታውን በማስረዳት፣ በውርጭና በሀሩር በመንገድ ላይ ለሰላምና ለነጻነት ሰልፍ በመውጣት፣ "ከጉልበተኛ አምባገነናዊ አገዛዝ ታደጉን" በማለት ተንቀሳቅሰዋል:: ጩኸታቸውም ተሰምቷል::

የተሰማው እሪታና አቤቱታ በከንቱ አልቀረም::የአሜሪካ ኮንግሬስ አባላት ጠንካራ መልእክታቸውን አስተላልፈዋል:: የአውሮፓ ሕብረት ያስተላለፈው የምርጫ መዛባትና በምርጫ ወቅት የነበረው ሰላም መሰል አካሄድ በምርጫው መሃል ላይ በተፈጠረው የኢህአዴግ ወከባና ማስፈራራት ተበላሸ:: ሕዝቡ በነቂስና በሌሊት ወጥቶ ድምፁን እንደሰጠው ሁሉ፣ ለማስከበርም ዘብ ቢቆም በኢህአዴግ ካድሬዎች በሚካሄደው አጉል ሥነስርአት ያጣ እሥር፣ አፈና፣ ወከባ የተነሳ ያ የተጀመረው መልካም አካሄድ በምርጫ



ሽንፈቱ ምክንያት መጥፋቱንና ነጻ ፍትሐዊና ሰላማዊ እንዳልነበረ ዓለም በመላ ሰማው አወቀው:: ማስረጃውም ይህንኑ አረጋገጠ:: ወያኔ/ኢህአዴግ ድጋፍ አገኘበታለሁ ያለውም የካርተር ማእከል ገዢው ፓርቲ ከሪፖርቱ መርጦ የሚጠቅም የሚጠቅመውን ብቻ ቢያቀርብም ሙሉ ሪፖርቱ ግን ከአውሮፓ ሕብረት ሪፖርት ያላነሰ እንጂ እንደተባለው አልሆነም:: የማንም አምባገነንና ሥልጣን ፈላጊ ጠባይ አንድና ተመሳሳይ ነው:: ሳዳም ሁሴንም ከነዚህ አይነቶች መሪዎች የተለየ አልነበረም:: ልዩነት ቢኖር በሳዳም ላይ ጦርነት መታወጁና በሌሎቹ ተመሳሳይ እርምጃ አለመወሰዱ ነው:: እርግጥ ቀናቸው ሲደርስ ጓዛቸውን ጠቅልለው እብስ ብለው ከሃገር መጥፋታቸው አይቀርም::

ገዢው ፓርቲ ልዩ ጦር ፈጥሮ፣አግአዚ ብሎ ስም ሰጥቶ፣ ከሕዝብ በታክስ የሰበሰበውን ገንዘብ ለሕዝብ ማዋከቢያና መግደያነት እያዋለው ነው::እነዚህ ታክሶች ቢቆሙ የአግአዚም ገቢ አብሮ ይደርቃል:: በዚህም አባላቱ እራሳቸውን በማጥፋት ከሕዝብ ጫንቃ ላይ ይነሳሉ:: ካልተሳሳትኩ 30 በመቶ የሚሆነው የመንግሥት በጀት ከውጭ እርዳታ የሚገኝ፣ ቀሪው ከሕዝብ በሚሰበሰብ ግብርና ታክስ የሚገኝ ነው:: ከዚህ ውጪ ገዢው መንግሥት በምንም መልኩ አገዛዙን ሊቀጥል አይችልም:: ገንዘብ እንኳን ቢያትም ዋጋ የሌለው ስለሚሆን እርባና አይኖረውም:: ብድርም ለማግኘት ተአማኒነትና የሃገር ሰላም ወሳኝ በመሆኑ ማንም ባንክ እንዲህ ያለውን መንግሥት አምኖ አያበድርም::ውክልና ሳይኖርም ቀረጥ መሰብሰብ አይቻልም::

አሁን ካለው ሁኔታና ከምርጫው ውጤት አኳያ ኢህአዴግ የሕዝብ ውክልና የለውም:: የሕዝብ ውክልና የሌለው ኃይል ደግሞ ልግዛ፣ ሥልጣን ወይ ሞት ካለ አግባብነት ያለው ሊሆን አይችልም፣ የሚሆነው ወራሪና ቅኝ ገዢ ነው:: ምርጫውን ያሸነፈው የሕዝብ ድምጽና ተቃዋሚ ፓርቲዎች የጦር ኃይል የላቸውም፣ ኃይላቸው የሕዝብ ድምጽ ብቻ ነው::

አንድ የሕዝብ ድጋፍ ያለው መንግሥት በምንም መልኩ ከሕዝብ የወጣውናና በሕዝብ ገንዘብ የሚተዳደረውን የደህንነት ሰራዊት መልሶ በሕዝቡ ላይ አያሰልፍም፤ ምክንያቱም ሕዝብ ይወደዋላ!?:: ኢህአዴግ የሕዝብ ድምጽ አግኝቼ ተመርጫለሁ ካለ ለምን ሕዝቡን ያዋክባል? ለምን አግአዚን "በለው" እያለ ትዕዛዝ ይሰጣል? ለምን ሕዝቡን ያስፈራራል? ለምን የተቃዋሚ ደጋፊዎችን በጦር መሳሪያ ያሳድዳል? ለምንስ የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮችን ሥነስርአት በጎደለው መልኩ "በማንቋሸሽና በማስፈራራት ከቤታቸው ሲወጡ፣ ወደቤታቸው ሲሄዱ በመኪና በመከታተል ተስፋ እንዲቆርጡ አድርጉ" የሚል መመሪያ ይሰጣል?

የኢትዮጵያ ሕዝብም ከተጫነበት መከራና ከወረደበት የሰቆቃ መአት ለመውጣት ድምጹን ሰጥቶ በቃኝ!! ብሏል::

## በቃኝ ደሞ በቃኝ ነው::!

ግልጽና ተጠያቂ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ፣ ለልማትና ለመልካም አስተዳደር አጋዥ የሆነ ተቋም እንዲመጣ፣ እንዲቋቋም የኢትዮጵያ ሕዝብ ፅኑ ፍላጎትና መስዋዕትነት ሊከፍልበት የተዘጋጀበት ነው::»





ሞተሩ በቃኝ ብሎ አገልግሎት መስጠት ሲያቆም፣ተሐድሶውም አልሠራም ሲል እንዲህ አለአባት ተገጥሞ በግድ ግልጋሎት ስጥ ይባላል::

ግዴታ ነውና ግልጋሎት መስጠት ከተባለ እዎን እያገለገለ ነው ግና ግልጋሎቱ ተጎታች፣ኋላ ቀር፣ ሥርአት አልባ ነው::

ያን ግልጋሎት ለመስጠትም ሕጋዊ መስመሩን መጠበቅ አይችልም መሪው ተባላሽቷል!

ጭርሱን መሪው የታለና!!

ለሚሌኒየሙ ከተዘጋጁት መፈክሮች ሁሉ እውነቱን የተናገ

## የሚሌኒየም ምርጥ መፈክር

«*በአዲሱ ሚሌኒዬም* ሰቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ግልጽና ተጠያቂ፣ቀልጣፋና አጋዥ የሆነ ተቋም *ይሆናል*» በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ዋና መ/ቤት መግቢያ ላይ አራት ኪሎ የተሰቀለ መፈክር::

እስከዛሬ፣ኢህአደግ ሥልጣን ላይ ከወጣ ጀምሮ ባለው ጊዜ ግን «ድብቅና ከተጠያቂነት የተገለለ፣አዝጋሚና ውጤት አልባ፣ጸረ ልማትና መልካም አስተዳደር አልባ የሆነ ተቋም» ነበር ማለት ነው?:: ምናለ ሁሉም መንግሥታዊ ተቋማት እንደዚህ እውነት እውነቱን ቢናገሩ! ብራቮ! ሰቪል ሰርቪስ ኮሚሽን::



« ሰለመብት! »የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች

# ለምን ወደ ፖለቲካ?

ዕድሜዬን በሙሉ ያሳለፍኩት በቴያትር ሙያ ነው::የተራዘመልኝ ጡረታ ተቋርጦ ጡረታዬ እንዲከበርልኝ ማመልከቻ እስካስገባሁበትና ተቀባይነት አግኝቶ ከቴያትር ቤት ቋሚ ሠራተኛነት እራሴን እስካገለልኩ ድረስ ሌላ ሙያም፣ ሌላ ሥራም የተፈጠረ አይመስለኝም ነበር::

የጡረታዬን መራዘም እንድተው ያደረገኝ ምክንያት ከራሴ ጥቅም ጋር የተያያዘ ሳይሆን ከሙያዬና ከሃገር ጋር በተገናኘ ጉዳይ፣ በወቅቱ በሥልጣን ላይ ከነበረ የሐገር ፍቅር ኃላፊ ጋር በተፈጠረ አለመግባባት ነበር::

ሻእቢያ ኢትዮጵያን በወረረበት ወቅት የእርዳታ ማሰባሰብ ተግባር በየአቅጣጫው ይደረግ ነበር:: በነጋዴዎች ምክር ቤት፣ ያዋቀረውን የእርዳታ አሰባሳቢ ኮሚቴ ቢሮ በማደራጀትና በማስተባበር እኔ እንድሠራ የክልል 14 ባህልና ስፖርት ቢሮን ጠይቆ፣ ቢሮውም በመስማማት ለሐገር ፍቅር ደብዳቤ ጽፎ ወደተጠቀሰው ቦታ ሄጄ ሥራዬን ቀጠልኩ:: ኮሚቴው፣ የጉዳዩን አጣዳፊነት በመመልከት፣ ሥራው ቀን ተሌት እንዲሠራ፣ አዳዲስ የእርዳታ ማሰብሰቢያ ዘዴዎች እንዲቀየሱ በሚል ሥራውን አስረከቦኝ፣ በርካታ እቅዶች ወጥተው በኮሚቴው ከጸደቁ በኋላ፣ በረጂምና በአጭር የሚከናወኑት ተለይተው በአዲስ አበባና በክልልም ሂደቱ ቀጠለ::

በመጀመሪያው እቅድ በኮሚቴው አባላት አማካኝነት በሚዘጋጀው በአዲስ አበባ ከተማ ካሉ የንግዱ ሕብተሰብ አባላት ማለትም በእራት ግብዣ፣ በጨረታ፣ በእንኳን ያደረሳችሁ መግለጫ ከቤት ቤት በመዞር የቃል ኪዳን ሰነድ ማስፈረም፣ በኤግዚቢሽን ማእከል ባዛር ሲዘጋጅ ማስተባበሩን እኔው ነበርኩ የምሠራው:: በተጓዳኝ ደግሞ፣ ከተገኘው ገንዘብ ላይ አስቸኳይ እርዳታ ለጦሩ ለማድረስ ኮሚቴው ሲያዝዝ፣



ፕሮግራም ማውጣትና ማከናወንም የኔው ነበር:: በየክልሉም ይህንኑ መሰል የገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራም ሲኖርም በክልሉ ያለው የንግድ ምክር ቤት ቢሮ እየጠየቀ የአዲስ አበባው የነጋዴው ሕብረተሰብ ኮሚቴ እያዘዘኝ መሄዴ አልቀረም:: ሥራው በጣም የተዋጣና ግንባር ቀደም የነጋዴው ስኬታማ ተሳትፎ የታየበት ሆነ:: እኔንም ቀንም ማታም ያሰራኝ ነበር::

በዚህ ጊዜ ነበር እኔ በድብቅ ከሁለት ቦታ ደመወዝ እንደምበላ ተደርጎ ሪፖርት የቀረበው::ሪፖርቱ የደረሰውም የነጋዴው ሕብረተሰብ ኮሚቴ በጉዳዩ በጣም በማዘን፣ «የሚከፈለው የነዳጅ ወጪ ሆኖ ሳለ ለሚያደርገው አስተዋጽኦ ደመወዝ እንደሚከፈለው ሆኖ የቀረበው ክስ አሉባልታ እንጂ አንድም እውነታ የሌለው መሆኑ እንዲታወቅ» የሚል ምላሽ ሰጠበት::ኮሚቴው ይህንን እንዳልሰማ ጥረት ቢያደርግም ሰማሁት፣ የተሰጠውንም መልስ ተረዳሁ::

መስማቴ እንዳይታወቅ በመጠንቀቅ ለኮሚቴው ወደ ምድብ ቦታዬ እንድመለስ እንዲፈቅድልኝና የሚረከብ ሰው እንዲመድቡልኝ ጠየቅሁ የኮሚቴው አባላት በግንባር ጉዳዩን በማስረዳታቸው «ሥራውን ቀጥል» የሚል ትእዛዝ ከባህል ቢሮው ደረሰኝ::ትእዛዙ በቀጥታ ከቢሮው ለኔ መጻፉ የሃገር ፍቅር አለቃዬን አበሳጨው መሰለኝ አንድ ደብዳቤ ጻፈልኝ::

ደብዳቤው «የእርዳታ ማሰባሰብ በሚል ሰበብ ወደ ክልልና ከሀገርም ውጪ በመሄድ የመስሪያ ቤቱን ሥራ የበደሉ ስለሆነ በአስቸኳይ ወደ ሥራ ገበታዎ እንዲመለሱ» ይላል:: ደብዳቤው እንደደረሰኝ ከአለቃዬ ቢሮ በመገኘት በጨዋነት፣ ሥራውን እንድቀጥል ከባህል ቢሮው እንደተጻፈልኝና ከእሳቸው የተጻፈው ደብዳቤ አለአግባብ ስለሆነ እንዲነሳልኝ ብጠይቅ «አንድ ጊዜ የተጻፈና በፋይል የተቀመጠ ስለሆነ አይነሳም» ተባልኩ::ይህም ማለት ውሳኔው ይጸናል ማለት ነው::ስለዚህም፣ ለባሕል ቢሮው «ለኔ ሲጻፍ ለመስሪያ ቤቴ ግልባጭ አለመደረጉ አግባብነት የሌለው ነው በሚል የደብዳቤውን ግልባጭ አያይዤ ለቢሮ ሃለፊው

አቀረብኩ:: ለሃገር ፍቅር አለቃዬ ማዘዣ ደርሶት ደብዳቤው ከግል ማሕደሬ የተነሳ መሆኑ ተገልጾ ተጻፈልኝ፣ እኔም ሥራዬን ከነጋዴው ሕብረተሰብ ጋር ቀጠልኩ::

ከዚሁ ሥራ ጋር በተገናኘ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በተዘጋጀው የውጭ ሃገር የኢትዮጵያውያን የእርዳታ ማሰባሰቢያ ፕሮግራም ላይ እንድሳተፍ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በተጠየቅሁትና ከ ከነጋዴው ሕብረተሰብም በተሰጠኝ ትእዛዝ መሰረት ይህንኑ ኮሚቴው ለቢሮው አሳወቀ:: ወደ አውሮፓና እስካንዲኔቪያ ሃገሮች አንድ የሙዚቃ ቡድን ይዤ እንድሄድ ተደርጎ የሙዚቃ መሳርያ ተጫዋቾቹንና ድምጻውያንን ለማካተት በሚደረገው ምርጫ እኔው እንድወስን ሆነ:: ይህንን በሚገባ አስተካክዬ ቡድኑ ጉዞ አደረገ:: ይህም የሃገር ፍቅር አለቃዬን አላስደሰተም::ይህ ሁሉ ከተከናወነና የድሉ ደስታም በኤግዚቢሽን ማእከል ከተከበረ በኋላ ወደ ሃገር ፍቅር ተመልሼ መደበኛ ስራዬን ቀጠልኩ::

አዲስ አበባ ቢሮ ያለው አንድ የጃፓን እርዳታ ድርጅት አንድ ቀና ሃሳብ ይዞ ደወለልኝና ከሃላፊዎቹ ጋር እንድነጋገር ጠየቀኝ፣ማነጋገር ያለብኝ እኔ ሳልሆን የቴያትር ቤቱ ሃላፊዎች መሆናቸውን ነግሬ በቀጠሮ ሰዎቹን ይዤ አለቃዬ ቢሮ ገባሁ:: ሰዎቹ ሁለት ፎቅ ያለው ክብ ቤት ለመስራት መወሰናቸውን የምድር ቤቱ ከተቻለ አርቲስቶቹ ለሱቅ፣ ለላውንድሪ፣ ለጸጉር ቤትና ለመሳሰሉት አገልግሎቶች የሚጠቀሙበት፣ ካልሆነም ቴያትር ቤቱ በማከራየት ጥቅም የሚያገኝበት እንደሚሆን፣ሁለተኛው ፎቅ ምግብ ቤትና የቤት ውስጥ ጨዋታ- እንደ ኮረንቦላ፣ ፑል፣ የጠረጴዛ ኳስ የሚካሄድበት ሲሆን ሶስተኛው ፎቅ ደሞ በአንድ ጎን ከ800 እስከ 1000 ሰው የሚይዝ አዳራሽና፣ በሌላ በኩል ከ300 እስከ 500 ሰው የሚይዝ መለስተኛ አዳራሽ ሁለት የመለማመጃ ቦታዎች የሚኖሩት የመሥራት እቅድ ስላለን ፎርሙን ሞልታችሁ ለአዲስ አበባ ቢሮ በቶሎ ዓመቱ ሳያልቅ ስጡ በሚል ስምምነት ተለያየን::



ወደ ፈረንሳይ ሃገር ለስብሰባ ሄጄ ስመለስ በስምምነቱ መሰረት ፎርሙ የተላከ መሆኑን አምኜ እንዳለሁ ከኦሳካ /ጃፓን/ ስልክ ተደወለልኝ:: ስለ ሚሰራው የቴያትር ቤት ጥሩ ዜና ነው ብዬ ደስ አለኝ:: ግን አልነበረም:: የደወሉልኝ ጃፓናዊ «ፎርሙ አልደረሰንም፣ ደጋግመን ጠይቀን አልመጣልንም ምነው?» አሉኝ:: ማታ በመሆኑ ምንም ማድረግ እንደማልችል፣ ግን ነገ በዚሁ ሰአት ቢደውሉልኝ መልስ ይዤ እንደምጠብቃቸው ቃል ገባሁ:: አልተላከም ብዬ አላመንኩም፣ምናልባት በአላላክ ዘግይቶ ወይም በአድራሻ ስህተት ይሆናል የሚል ጥርጣሬ ነበር ያለኝ::ሲነጋ ቢሮ ሄጄ ሃላፊያችንን ጠየቅሁት:: « ኦ! ያ ፎርም? አምን ገና አልሄደም:: ለቢሮው አሳውቄ ነው መላክ ያለብኝ:: እስቲ ሰሞኑን!» አለኝ::የጉዳዩን አስቸኳይነት ባስረዳም ብዙ የሚያበረታታ መልስ አላገኘሁምና«ምን ልበላቸው?» ስለው«ሰሞኑን እንልከዋለን» ብሎ ጉዳዩን አቀለለው::

በበነጋታው ሲደውሉ የተባልኩትን መልስ ሰጠሁና እንደገና ጠዋት ተመልሼ አለቃውን ስለጉዳዩ ሳነሳበት «አሁን ሊሆን አይችልም፣ ቢሮውም ይህን ጉዳይ የሚፈቅድ አይመስለኝም» ሲለኝ፣ «እንግዲያው ፎርሙን ስጠኝና እኔ ልሞክር» ስለውም ፈቃደኛ አልሆነም:: የጃፓኑም ቢሮ ደጋግሞ ሞክሮ ስላቃተው ተወው:: ይህ በጣም ያበሳጨኝና ተስፋ ያስቆረጠኝ አንዱ ጉዳይ ነው::

ሌላው ከዚህ ቀደም ብሎ የጦርነቱ ሁኔታ እንደተሰማ ጥቂት ባለሙያዎች በፈቃደኝነት በመሰባሰብ አንድ ፕሮግራም ቀረጽን:: ለዚህም መነሻ የሆነን እስከዛሬ ድረስ በደርግም ዘመን ቢሆን እኛ ያልተሳተፍንበት ሃገራዊ ጉዳይ ባለመኖሩ ነው:: ውጤቱ ሲመዘገብ ግን «እንዲህ የሚባለው ከፍተኛ፣ ክልል፣ ወይም ቀበሌ ፣ አለዚያም ድርጅት፣ እንዲህ አይነት ገቢ አሰባስቦ ገቢ አደረገ» ነው የሚባለው እንጂ የአርቲስቶች ውለታ አይነሳም:: ለማሰባበሰቡ ዋናው መሣሪያ ግን በየዘርፉ ያለው የአርቲስቶች ግልጋሎት ነው::አሁን የተሰባሰብነውና ያወጣነው ፕሮግራምም

ሁሉንም የጥበብ ባለሙያ ያካተተ ሆኖ እኛው በኛው አዘጋጅተን፣ አሰባስበን በስማችን የምንሰጠው እንዲሆን በማለት ነበር:: የትብብር ችግር ሳይገጥመን እንቅስቃሴው ተጀመረ::የኤግዚቢሽን ማእከልም ከነናችን ቆመ:: ድርጅቶች የቃልኪዳን ሰነድ እንድንልክላቸው ጠየቀውን ምን ያህል እንደሚሰጡንም በገቡት ቃል መሰረት ስናሰላው ወደ 700 000 ብር ገደማ ደረሰ:: ከዚህ በተጨማሪ ፕሮግራማችን ተግባራዊ ሲሆን በርከት ያለ ገንዘብ ማሰባሰብ እንችላለንና ተስፋ ያለው ጅምር እንደሆነ አምነንበት መንቀሳቀስ ያዝን::

ይህን ለማዘጋጀትና ፕሮግራሙንም በየቦታው ለማከናወን በሂደት ላይ እያለን አንድ ቀን ጠዋት በሜጋ ማእከል ስብሰባ ተብለን ከኛ ሁለት ሰዎች ሄድን:: ስንደርስ ልክ እኛ እያካሄድን ያለውን አይነት ተግባር የሚያከናውን ኮሚቴ ተፈጥሮ ሥራ ሲጀምር ስለሆነ እኛ የጀመርነውን እንድናስረክብና ሥራውን በኮሚቴው ውስጥ ሆነን እንድንሰራ ተነገረን:: ጥያቄም አይደለም፣ ትእዛዝ ነው:: ግራ ተጋባን:: እኛ በአዲስ አበባ መስተዳድር ሥር ያለን ሆነን እንዴት ከፌዴራል ባህል ቢሮ በመጣ ተእዛዝ ፕሮጀክታችን ይወሰዳል? ከሆነስ ደግሞ ባለሙያው በሙሉ ተሰባስቦ ዴሞክራሲያዊ በሆነ መልኩ በምርጫ እንጂ በግል፣ በድብቅ በተቋቋመ ኮሚቴ ውስጥ መግባቱን አልፈቀድንም::ይህን ለማስረዳት ስንሞክር ሰብሳቢው «ካድሬው እኮ እኔ ነኝ!» በማለት ፉከራና ማስፈራራት የጀመረው::እዚህ ላይ ነው ሁለታችንም ጥለን በመውጣት የኛንም ፕሮጀክት ትተን፣ ቃል ለገቡልንም ድርጅቶችና ግለሰቦች የምስጋና ደብዳቤ በመጻፍ የተውነው:: የቴያትር ቤቱ ሥራ አስኪያጅ የብአዴን እጩ አባል፣ እኝህኛው ደሞ የሕወሃት አባል በመሆናቸው ጎዱኝ::እኔ ደሞ ነጻ ስለሆንኩ ነው ጥላ ያጣሁና የተጎዳሁ::

በጣም በርካታ አጋጣሚዎች ናቸው ምክንያት የሆኑኝ::ሌላው አንድ ምሽት በሼራተን በተከናወነ ሥርአት ላይ ከአስተማሪዬ ከጋሽ ተስፋዬ ገሰሰ ጋር በአንድ ጠረጴዛ ላይ ነበርን::ዝግጅቱ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ነበር:: በሥነስርአቱ ሂደት ላይ እኔም ጋሽ



ተስፋዬም የምናውቀው አንድ ከፊል ካድሬነት የሚቃጣው፣ በሌላ በኩል ባለሙያነት የሚያምረው የተዋጣለት የሚባል ሙያ ተብሎ ቢጠየቅ ግራ የሚጋባ የሚሆንበት በድንገት ወደ ጠረጴዛችን መጥቶ ጋሽ ተስፋዬን « የአብዬ መንግሥቱ በዓል ስለሚከበር በዚያ ላይ ስለእሳቸው አንዳንድ ነገር እንድትፅፍልን እንፈልጋለን» አለው «በጣም ጥሩ እንዲያውም ከደበበ ጋር ብዙ ግንኙነት ነበራቸው፣ ጎረቤታሞችም ነበሩ፣ እና እሱንስ ለምን አትጨምረውም?» ሲለው ሰውዬው በተፈጥሮው ግልፅነት የሚጎለው ነውና ወደ ጋሽ ተስፋዬ ጆሮ ጠጋ ብሎ «እሱ እኮ .. .. .. ..» አለ ሙሉውን ንግግር አልሰማሁትም::ጋሽ ተስፋዬ ያን እለት በጣም ሲናደድ አየሁት::«ለምን በማታውቀው ነገር ትገባለህ?አለና ነገር ላለማቀጣጠል ተወው::እኔም አልጠየቅሁትም:: አንድ ነገር ግን የዚያ ሰው ሁኔታ ፍንጭ ሰጥቶኛል:: አዘጋጅ ኮሚቴው በበዓሉ ላይ እንኳን እንዳልገኝ አድርጓል:: ለዚህ ነው እራስን ነፃ ማውጣት የሚለውን መርህ የተቀበልኩትና ወደ ቀስተ ደመና የተቀላቀልኩት::

**አ**ንዳንድ ሰዎች ህሊናቸውን ለተንኮልና ለምቀኝነት ብቻ ስለሚያስልፉት ከዚያ ውጪ ማሰብ አይችሉም::እንዲህ አይነት ተንኮለኞችም በአንድ ሙያ ብቃት ያለው ተግባር ሳያከናውኑ በየቦታው ብቅ ጥልቅ በማለት ብቻ ጊዜያቸውን ያጠፉና በማብቂያው ታሪካቸው«ተወለደ፣ አደገ፣ በላ፣ ጠጣ፣ አረጀ፣ ሞተ» ይሆናል:: ይህም የዚያው ቢጤ ነው ብዬ ችላ አልኩት:: በኋላ በቴያትር ቤት አካባቢ ካሉ ሰዎች የብአዴን እጩ አባል ሆኖ ለብዙ ጊዜ አባልነት ደረጃ ያልደረሰ ነው ሲሉ ሰማሁ:: እንግዲህ እነዚህ ሁኔታዎችና ተመሳሳይ ገጠመኞች ናቸው ወደ ፖለቲካው እንድገባ የገፋፉኝና የመጣውን አጋጣሚ ተቀብዬ እራሴን ነጻ ለማውጣት እንድችል ያስወሰኑኝ::

እርግጥ በሃገራችን ፖለቲካ በጣም የሚያስፈራ ጉዳይ ነው::እንደ ደንቡ ግን በጭራሽ ማስፈራት አልነበረበትም::ሰው ሃሳቡን በነፃ ቢገልፅና ቢያንሸራሽር

ምንድን ነው ክፋቱ? ማንም ስለ ሰብአዊ መብት መከበርና ሁሉም የዚህ መብት ተጠቃሚ እንዲሆን ቢናገር ለምን አስፈሪ ይሆናል? የምንፈራው ጉዳዩ እውነት የሚያስፈራ ሆኖ ካሳለፍናቸው ስርአቶች የተነሳ ፈሪዎች ስለሆንን ብቻ ይመስለኛል:: ገዢው ፓርቲ ሲናገረው ያጨበጨብንለት ጉዳይና ርእስ በሌሎች ሲነገር የሚያሸማቅቀንና ተዘዋውረን አካባቢያችንን በጥራጣሬ ከማየት በፊት ወደመጣንበት መመለስ የምንፈራው ፈሪዎች ስላደረጉን ብቻ ነው:: በቃ! ከዚህ እስካልወጣንና የፈሪ ሕብረተሰብ ከፍርሃቱ እንዲላቀቅ ካላደረግን ለውጥ ማምጣት አንችልም::ይህን ለማድረግ ደሞ እኔ አስቀድሜ ፍርሃቴን አራግፌ መጣል አለብኝ ብዬ ወሰንኩ:: ሰዎች ደጋግመው « ምን አጣህና ነው ፖለቲካ ውስጥ የገባሽው?» አሉኝ:: «ያጣሁት ነጻነት ነው:: እኔ ያጣሁትን ነጻነት መልሼ ማግኘትና ልጆቼ ነጻ ሆነው እንዲኖሩ እፈልጋለሁ» ነበር መልሴ::

## ጉዞ ወደ ቀስተደመና

ቀስተደመና ሲመሰረት አሜሪካ ነበርኩ:: የሄድኩበትን ጉዳይ ጨርሼ ወደ ሃገሬ ልመለስ ጥቂት ሳምንታት ቀርተውኛል:: አንድ ቀን እህቴ ጓደኛዬ ዓለምፀሐይ ወዳጆ፤«ቀስተ ደመና የሚባል ፓርቲ ተመሰረተ»ብላ አባላቱን ስትዘረዝራቸው፤ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት አልቻገረኝም::ዓለም፤«ምናልባት አሁን ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን የሚገባንን እናገኝ ይሆናል» አለች:: «በራስ ወዳድነትና በአምባገነንነት ያልተወጠረ፤ ለሃገርና ለወገን የሚያስብ፤ባለብዙ ብሄር ብሄረሰቦች ኢትዮጵያን በፍቅር፤በመግባባት፤በመከባበር፤በአንድነት አንድ ኢትዮጵያን ለማቆየት የሚቻልበት ፍንጭ ሊሆን ይችላል::» አለችኝ በመኪና ወደ ዋሺንግተን ዲሲ ስንሄድ::»

«ግን ለምን ቀስተደመና አሉት?» አልኳት፤

«እንዴት?» አለችኝ



«ቀስተደመና እኮ ሰአት ጠብቆ ሲመቸው ብቅ የሚል ነው፤ለእኛ ደሞ የሚያስፈልገን ሲመቸው ብቅ የሚል ሳይሆን ሁል ጊዜ የሚገኝ መሆን አለበት» አልኳት:: እሷ ያየችበትን ትርጉም፤«ቀለማቱን ስታያቸው ምን ይሰማሃል? እኔ በበኩሌ ያ ሁሉ ቀለም በአንድነት ተዋህዶ ውበትን ስምምነትን አንድነትን ሰላምን ነው የሚያሳየኝና በዚያ መልክ ማየት አይሻልም? እስቲ ልብ ብለህ እየው? የቀስተ ደመና ሕብረ ቀለም አያምርም?» ስትለኝ እውነቱ ታየኝ፣ ያምራል::

ዓለምና እኔ በዚህ ጉዳይ ላይ ሃሳብ ከተለዋወጥን በኋላ ተክሌ ደስታ ስለ ቀስተ ደመና የሚያስረዳውን መጽሐፍ ይዞት መጣና በአንድ ሌሊት አንብቦት ጠዋት ወደሥራ ሲሄድ ለኔ ትቶልኝ ሄደ በደንብ ሳነበው ዓለም ካለችው ጋር በጣም የሚቀራረብ ሃሳብ አለበት:: ከዚያ በኋላ ብዙም አልተነጋገርንበትም::

ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ወደ አዲስ አበባ ስመለስ ስለ ቀስተደመና ብዙ ይወራል:: በጣም ግልፅነት ያላቸው፤ለሃገርና ለወገን ተቆርቋሪዎች የተሰባሰቡበት፣ ጥቅም የማያሸንፋቸው፤ በዘር በጎሳ ያልተደራጁ፤ ራዕይ ያላቸው ሲባል ሰማሁና ለማረጋገጥ ፈለግሁ::አንድ ወዳጄ የአርብ ሳምንታዊ ማሕበረተኛዬ፣ «ቆይ እነግራቸውና ይደውሉልሃል» አለኝ:: ከጥቂት ቀናት በኋላ የተፈሪ መኮንን ት/ቤት የዱሮ ጓደኛዬ ሽመልስ ተ/ፃድቅ (ዶ/ር) ደወለልኝና «እንገናኝ» አለኝ:: «የት?» አልኩት:: ቀስተ ደመና ፅ/ቤት ሲለኝ «አሁኑኑ መጣሁ» ብዬው አድራሻውን ስጠይቀው ከመኖርያ ቤቴ አጠገብ ነው::ወዲያው ሄድኩ::

ስለ ቀስተደመና ከማውራታችን በፊት ቡና አዞልኝ ስለ ዱሮው የወጣትነት እድሜያችን እያነሳን፤ጓደኞቻችንን እያስታወስን ስናወራ ቆይተን ወደ ጉዳዩ ገባን::የቀስተደመናን ዓላማውን፣ ራዕዩን፤ግቡን ካስረዳኝ በኋላ የማነበው ሰጥቶኝ ቀጠሮ ይዘን ልንለያይ

ስንል በጣም የማደንቀውና በጋዜጣና በመፅሔት ላይ ስራዎቹን በማንበብ አልፎ አልፎ ስንገናኝ በሚያሳየኝ አክብሮት በጣም የማደንቀው በፈቃዱ ደግፌ(ዶ/ር) መጣ:: ሰላም ተባብለን መሄዴ ቀርቶ እንደገና ቡና ታዞ ጨዋታ ቀጠልን:: ዶ/ር በፈቃዱ «ከማለፋችን በፊት ለሃገርና ለሕዝብ ለማገልገል እንድንችል በቅድሚያ እራሳችንን ነፃ እናውጣ ብለን ነው የተሰባሰብነው::» አለኝ:: እውነቱን ነው::

መጀመርያ እኔ ነፃ ሳልሆን ለሌላ ነፃነት መቆም መታገል አልችልም:: በቅድሚያ እራሴን ነፃ ካወጣሁ በኋላ ለሌላው ነፃነት ለመታገል አይቸግረኝም:: ደሞ እያንዳንዱ ነው ለራሱ ነፃነት መታገል ያለበት፤ስለዚህም ሁላችንም ለየራሳችን ነፃነት አብረን ስንቆም እራሳችንን ነፃ እያወጣን ለሌላውም ነፃነት እንታገላለን» አለኝ:: ብዙም አልገባኝምና እስቲ ምናልባት ሽመልስ በሰጠኝ ፅሁፍ ውስጥ ይኖር እንደሆነ አየዋለሁ በሚል ከራሴ ጋር ተማክሬ ያን እለት ተለያየን::ቤቴ ከሄድኩ በኋላ ያንን ፅሁፍ አነበብኩት:: ሽመልስም፣ በፈቃዱም ያሉት በሚገባ ተተንትኖ አገኘሁትና ደጋግሜ በማንበብ ገባኝ:: እኔ ከማስበው ጋር የሚገጣጠም ፕሮግራም ያለውና በውስጡ የተካተቱት አሰባሳቢና መሥራች ሰዎቹ ለሕዝብ አገልጋይ ለመሆን የፈቀዱና ተጠያቂነትን የሚቀበሉ ለዕድገት እንደሚቆሙ አሰብኩና ለመቀላቀል ፈቃደኛ ሆንኩና ማመልከቻ አስገብቼ በአባልነት ተመዝግቤ መንቀሳቀስ ወሰንኩ::

አባል ልሆን ወደ ቢሮ ማመልከቻ ይዤ ስሄድ፤ ጋሽ መስፍንን (ፕሮፌሰር) አገኘሁትና ሰላም ስለው፤«እንኳን ደህና መጣህ! ስሰማ በጣም ነው ደስ ያለኝ፤»አለኝና ቡና ታዘዘልኝ:: ወዲያው ብርሃኑ( ዶ/ር) መጣ:: ገና ሲያየኝ «ጋሽ ደቤ! ይሄው እንግዲህ ተሰባስበን ጀምረናልና ያንተ ሙያዊ እርዳታ ያስፈልገናል::እራሳችንን ነፃ ለማውጣት ነው በአንድነት የቆምነው» ሲለኝ «አይ እኔም ነፃ መውጣት ስለምፈልግ



ነው የመጣሁት» አልኩት::ማመልከቻዬን አስገብቼ ተለያየን::

ዶ/ር ሽመልስ ደውሎ «ዛሬ ስብሰባ ስላለ ና» አለኝና ስሄድ በአባልነት እንደተቀበሉኝ ነግሮኝ «እስከዛሬ ድረስ የሕዝብ ግንኙነትን ይሰራልን የነበረው ጋሽ መስፍን ነው፤የሥራ አስፈፃሚው ያንተን ማመልከቻ ካየና በአባልነት ከተቀበለህ በኋላ ፈቃደኛ ከሆንክ የሕዝብ ግንኙነቱን እንድትይዝልን ጠይቅ ተብያለሁ» አለኝ:: «ጋሽ መስፍን እያለ!» ስለው፣ «አይ! በፊትም ችግሩን ለማቃለል ሲል ደርቦ ነበር የሚሰራው» አለኝ:: «እንደሱ ከሆነ በደስታ» አልኩት:: ወዲያው የቀስተ ደመና ፓርቲ የሕዝብ ግንኙነት ሆንኩና ሥራውን ቀጠልኩ::

የሚገርመው፣ ይህ ሁሉ ሲሆን ከቤተሰቤም ሆነ ከጓደኞቼ የሰማ አልነበረም::መስማትም የለባቸውም ወይም መንገርም የለብኝም የሚል እምነት ነው የነበረኝ::በአንድ ስብሰባ ላይ የቀስተደመናን፤ሕዝባዊ ስብሰባ ስመራ ነው ለመጀመርያ ጊዜ ያዩኝ::ስብሰባው በሚኒሊክ ትምሕርት ቤት የተካሔደ ሲሆን፣ እዚያ ያቀረብኩት «ተረግመናል እንዴ?» የሚል ፅሁፍ ነበር::በጽሁፉ የበርካታ ተሳታፊዎች ስሜት ተነክቶ ያለቀሰም ነበር::ወዲያው የግል ጋዜጣ ስለሁኔታው ተረከ::ስብሰባውም በቴሌቪዥን ቀረበ::አንዳንድ ጓደኞቼ «ምን ጎድሎብህ ገባህ?» የሚል ጥያቄ አቀረቡልኝና ታዘብኩዋቸው ግን አልተቀየምኩዋቸውም:: «እኔ ሳይገባኝ ብዙ እንደቆየሁ ነው የማውቀው» ብዬ ተውኩዋቸው::የነሱ አመለካከትና የኔ አለማወቅ ግን ይለያያል:: ከአነጋገራቸው:የነሱ ትንሽም ቢሆን «ፍርሃት፣ ፍርሃት» ይሸታል::ካለፈ ልምድ እንደተረዳሁት በኛ ሙያ አካባቢ ወዶ ፈቅዶ ወይም ምርጫው ሆኖ ወደ ፖለቲካው የገባ በጣም ጥቂት ነው::አብዛኛውን ጊዜ በግዴታ ወይም ከጥቅም ጋር በተያያዘ፤ አለዚያም ድንገት ነው::የእኔን ተሞክሮ ብንወስድ፣ በጃንሆይ ጊዜ በታህሳሱ ግርግር ሰሞን ወንድሜ የክብር ዘበኛ መኮንን ስለነበርና የመንግሥት ግልበጣውም የተጀመረው በክብር ዘበኛ አዛዥ በመሆኑ መርዳት አለብኝ በሚል የጉርምስና ስሜት ነበር

በግቢው የነበረውን የነገሥታቱን ፎቶግራፍ መሰባበር የጀመርነው::ያን ጊዜ ደብረ ብርሃን መምህራን ማሰልጠኛ ነበርኩ::እውነቱን ለመናገር፤ ስለ ፖለቲካ ምንም እውቀት አልነበረኝም:: ከፎቶግራፍ መሰባበሩ ባሻገር የወንድሜ ጓደኞች ከአዲስ አበባ በደብረብርሃን በኩል ሲሸሹ ከማሰልጠኛው በታች በበሬሳ ወንዝ ጠርዝ ላይ ሲያልፉ አግኝቼያቸው የአቅሜን ለመደበቅ መሞከሬ ትዝ ይለኛል:: ያም ቢሆን በወንድሜ በኩል የማውቃቸውን በማየት እንጂ፣ በመንግሥት ግልበጣው በማመን ያደረግሁት አልነበረም::

በደርግ ጊዜ የካድሬው ብዛት፣ የአንዳንዶቹ የፖለቲካ መሃይም መሆን፤ስለሶሻሊዝም ያላቸው ግንዛቤ ደካማነት፤ካድሬነታቸውን ለጥፋት፣ ለተንኮል፣ ለግል ጥቅም፤ ለማስፈራርያነት፤ለደረጃ እድገት ይጠቀሙበት ነበር::በተለያየ ወቅት ወደ ፖለቲካው ለመግባት የፈለግሁበት ወቅት ቢኖር አንዳንድ ባካባቢዬ የነበሩ ደካማ «ካድሬዎች» በሚያደርጉብኝ ቅጥ ያጣ ጫና ነበር:: በዚያው መጠን ደግሞ የበሰሉ ያነበቡ፤ያወቁ፤ ጥቂትም ቢሆኑ በአካባቢዬ ስለነበሩ በነሱ በኩል የነበረኝ ድጋፍና የነሱ ጥብቅና በተደጋጋሚ ከተሰነዘረብኝ የጥቃት አደጋ አድኖኛል::

ኢህአዴግ እንደገባ እኔም በኢሰፓነት ተጠርጥሬ ያልተገላበጠ ፋይል፣ ያልተጠየቀ ቢሮ አልነበረም::ምንም እንኳን ኢሠፓነት ወንጀል ባይሆንም እኔ ግን አልነበርኩምና ፍለጋው፣ ልፋቱ ሁሉ ከንቱ ሆነ::ደሞስ ኢሠፓዎች ካለው መንግሥት ጋር አይሰሩም ቢባል አሁን ስልጣን ላይ ያሉት ኢሠፓዎች፣ፈላጭ ቆራጭ ሆነው የሚያገለግሉት ቅር አይላቸውምና ነው?

## የምርጫ ዝግጅት

**ቀ**ስተደመና ለምርጫው በመዘጋጀት ላይ ነው::አንዳንድ ሕዝባዊ ስብሰባዎች ያካሂዳል:: አባል ከሆንኩበት እለት ጀምሮ ከልብ መስራት እንዳለብኝ በማመን አቅሜ በፈቀደ ሁሉ እየሞከርኩ ነው:: ቀደም



ሲል በፊት ለፊት ገብቼ የፖለቲካ ተሳትፎ ያደረግሁበት ጊዜ አልነበረም::አርግጥ በደርግ ጊዜ ውይይት ክበብ እገባ ነበር:: በኋላም፣ በሌለሁበት ተመርጬ፤ የሸንጎ አባል ነበርኩ እንጂ ብዙም ልምድ የለኝም::አሁን ግን በቀስተደመና ውስጥ ሆኜ በመጠየቅም በማንበብም ማወቅ የሚገባኝን መረዳት ይገባለሁ:: አብሬያቸው ያለሁት ሰዎች ደሞ አብዛኛዎቹ እራሳቸው ት/ቤት ናቸውና ለመማር እችላለሁ ብዬ አመንኩ::

አንድ ፍርሃት ነበረኝ::እውነት አሁን በሃገራችን ነፃና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ይካሄዳል? የሚለው ጥርጣሬ ያሳስበኝ ነበር::ምንም ይሁን ምን፤ያለነው ኢትዮጵያ ውስጥ ነው:: ኢትዮጵያ ደሞ ያለችው አፍሪካ ውስጥ ነውና ያሳስበኛል:: ዱሮ በተማሪነቴ ወቅት አንድ ሀንጋሪያዊ አስተማሪዬ « በአፍሪካ ፖለቲካ ውስጥ መግባት በዝናብ ውስጥ ጥላ ሳትይዝ እያንዳንዱን የዝናብ ፍሬ አምልጦ ማለፍ ማለት ነው» ይል የነበረው ትዝ አለኝ::

የአሜሪካንን ምርጫ ተከታትዬ ነበርና የትም ቢሆን ሥልጣን ያጓጓል፣ ይጣፍጣል:: የበለፀገው ሃገር ምርጫ ሕይወት አያልፍበትም፣ ቢበዛ በርካታ ገንዘብ ነው የሚያልቅበት:: ባልዳበሩ ሃገሮች ደሞ የሰው ሕይወት ርካሽ ነው::ማሰር፤ ማስፈራራት፤ ማሰቃየት፤ ቂም መያዝና መወጣት፤ማፈናቀል፤ቤተሰብ መበተን፤ምንም የማይደረግ ነገር የለም:: ይህ ደሞ እንደልብ የሚያንቀሳቅስ አይደለም::ምን ሊደርስ ይችላል የሚለው ስጋት ይጎትታል:: በተለይ ገዢ ፓርቲ በስልጣን ላይ እያለ፣ በምርጫም እየተወዳደረ ባለበት ሁኔታ ለፓርቲው መመረጥ ሲል መንግሥትነቱን ሊጠቀምበት፤ በዚያም ያሻውን ሊያደርግ፡ በምርጫ ቢሸነፍ ያሸነፈውን ፓርቲ አመራሮችና አባላት « እንዴት ብትደፍሩኝ ነው? እንዴት ጠገባችሁ?» ማለትና ማሰር ይችላል:: «ያዙት» ይላል፣ ያስይዛል፤እሰሩት ብሎ ያስቀፈድዳል፤እርገጡት ይልና ያስቀጠቅጣል:: ይህ ሁሉ ዙርያው ገደል የሆነ ሁኔታ ያሳስባል::ያም ሆኖ «ሕልም ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደርም» ነውና

ስጋቱና ጥርጣሬው እንዳለ፤ «ማን ያውቃል ያሁኑ የተለየ ቢሆንስ?» በሚል ይገባበታል::

በመገናኛ ብዙሃን ስለምርጫው ሚዛናዊና ዴሞክራሲያዊነት ተደጋግሞ በመነገሩ፤መንግሥት ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ሕጋዊ ፈቃድ ሰጥቶ በጅምሩ ወቅት አብሮ ቁጭ ብሎ መደራደሩ ደሞ፣ በሌላው የአፍሪካ ሃገር ከተደረገው የተለየ አስገራሚ ሁኔታ ፈጥሮ ዓለምን ጉድ በማሰኘቱ ያደፋፍራል:: ያም ይሁን ይህ ሁኔታው ምንም ያስከትል ምንም እኔም አቅሜ በፈቀደ የሚቻለኝን አስተዋጽኦ ማድረግ አለብኝ አልኩ:: ገዢው ፓርቲ ሕጋዊ ፈቃድ ሰጥቶ ሕዝባዊ ስበሰባም ፈቅዶ፤ውድድርን ፈልጎ «ኑ እስቲ እንያችሁ» ሲል ወደ ኋላ ማፈግፈግ ተገቢነት የለውም:: ይህን ሁሉ ካየሁ በኋላ ልምድ ከላቸው ጋር በመነጋገር፤የሂደቱ አካል ሆንኩ::

ከሁሉም በላይ ያደፋፈረኝ በተደጋጋሚ ውይይት ላይ የሚነሳው «ለራስ ነጻነት በቅድሚያ ታግሎ ራስን ነጻ በማውጣት የሌሎች ነጻነት ተሟጋች መሆን» የሚለው አባባል ነው::ያን ሳገናዝበው ደሞ አሳመነኝ:: እኔ የነጻነትን ጣእም ካወቅሁ፤የራሴን የዴሞክራሲ መብት ካገኘሁና ጥቅሙን ከተረዳሁ በዚያ ላይ በመመርኮዝ የሌሎችን ዴሞክራሲያዊና፤ሰብአዊ መብትን በማስከበር ነጻ ሕብረተሰብ እንዲመሰረት ለመታገል ብቃት ይኖረኛል ብዬ አረጋገጥኩ::

## የሀገር የወገን ፍቅርና የዓላማ እምነቴ በፈተና ውስጥ

በሥራ አጋጣሚ ወደ ጅማ ሄጄ ነበር:: እዚያ ያየሁት ደሞ ይበልጥ ብርታት ሆነኝ:: የሄድኩት የኦሮሚያ ሴቶች ማሕበር ዓመታዊ በዓሉን በንግድ ትርኢት ሲያከብር የተመረጠው ቦታ ጅማ ስለነበር በዚያን ጊዜ ደሞ የምርጫውን ቅስቀሳና ማስተዋወቁን ሥራ ጀምሬያለሁ:: «ቀስተደመና- ቅንጅት» መሆኔ ታውቋል::የንግድ ትርኢቱን የሥራ ኮንትራት



የተፈራረምኩት አባልነቴ ከመታወቁ ቀደም ብሎ ስለነበር አሁን መተው ችግር ነበር:: ደሞስ ሥራንና የፖለቲካ አቋምን ምን ያገናኘዋል?

የንግድ ትርኢቱ በሚከፈትበት እለት የሩጫ ፕሮግራም ስለነበር የከተማው ሰው በብዛት ፕሮግራሙ በሚካሄድበት ቦታ ተሰባስቧል:: እኔና ሌሎች ፕሮግራሙን የምናዘጋጀውም በቦታው ተገኝተን ስነስርአቱን በማስተከከል ላይ እያለን አቶ ጁነዲን ሳዶ፤ወ/ሮ ጊፍቲ አባሲያ፤ወ/ሮ ገነት ዘውዴ፣ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ባለቤት ወ/ሮ አዜብ፣ የአሜሪካን አምባሳደር በሰአት በቦታው ደረሱ::አቀባበሉን የሚያደርጉት ወ/ሮ አምሳለ፣ የሴቶች ማሕበር ሰብሳቢና ሌሎችም የኮሚቴ አባላት ስለነበሩ እኛ ቦታ ለቀን እነሱ ማስተናገዱን ያዙ::

ሩጫው ተጀመረ::ድንገት አቶ ጁነዲን አዩኝና በሩቅ ሰላምታ ተለዋውጠን ሳለ በምልክት ጠሩኝ:: ሄጄ የአክብሮት ሰላምታ ሰጠሁ፣ እሳቸውም አክብረው ተቀበሉኝ::ከአሜሪካን አምባሳደር ጋር ማንነቴንና የሙያ ስራዬን ገልፀው አስተዋወቁኝ:: አምባሳደሯ ቀደም ሲል የት እንደተዋወቅን ጠይቀውኝ ነግሬያቸው ልሄድ ስል አቶ ጁነዲን ባጠገባቸው እንድቀመጥ ጋበዙኝ:: ያለብኝን የሥራ ሂደት አስረድቼ ለተደረገልኝ ከበሬታ አመስግኜ ወደ ነበርኩበት ተመለስኩ:: ለመሸሽ ሳይሆን በእውነት ነው ስራ ነበረኝ::በሩጫ ውድድር ለሚያሸንፉት ተወዳዳሪዎች ሜዳልያውን አዘጋጅቼ ለአቶ ጁነዲንና ለአምባሳደሯ እንዲሸልሙ በኮሚቴ አባላት መቅረብ ነበረበት::

የጠዋቱ ፕሮግራም ካለቀ በኋላ እስከምሽቱ እራት ግብዣ ድረስ ሌላ ፕሮግራም ስላልነበረ ሁሉም በየፊናው ተሰማራ::ሆቴል ስደርስ ሆቴሉ በረንዳ ላይ የነበሩ በመሃከለኛ የእድሜ ክልል ያሉና ወጣቶች፤ ወደ 7 የሚሆኑ በረንዳው ላይ ያለውን አንዱን ጠረጴዛ ይዘው ይጫወታሉ::ባጠገባቸው ሳልፍ አንደኛው ተነስቶ ሰላምታ ሰጠኝና ቡና እንጋብዝህ ብሎ ከሌሎቹም አስተዋወቀኝ፤ እኔም ድንገት ለመጣ የቡና ግብዣ

ተቀላቀልኩ:: ያው ድንገት ቡና የጋበዘኝ ሰው፣ «ትላንት ማታም መጥተን ነበር ግን ልናገኝህ አልቻልንም፤ ብንጠይቅ ተኝተሃል አሉን:: አሁንም ተስፋ ቆርጠን ልንሄድ ስንል ነው ይመጣል ተብለን የቆየነው» አለኝ::

የታዘዘው ቡና መጥቶ በመታደል ላይ ሳለ « ምን ፈልገው ይሆን? ባለስልጣኖች ይሆኑ?» እያልኩ ሳሰላስል አሳላፊው እንደሄደ አንደኛው ከመሃከላቸው፣ « ጋሽ ደቤ! በእውነት በጣም ጥሩ ነገር እያየን ነው:: እስከዛሬ ከነበረው የፖለቲካ አካሄድ ለየት ያለ ነገር እያየን ነውና ስለ ፓርቲያችሁ ብትነግረን» አለኝ:: የተቻለኝን ያህል አስረድቼ ይበልጥ ማወቅ ከፈለጉ ብዬ ሙሉ አድራሻዬን ሰጥቻቸው፣ የነሱንም ተቀብዬ ስንለያይ እስክሄድ ድረስ እንደማይለዩኝ ቃል ገብተው ተሰነባብትን:: እውነትም ጅማን ለቅቄ እስክወጣ ድረስ አልተለዩኝም::ፍላጎታቸው አባል ለመሆን ነበር፣ አልቀረም ሆኑ::አዲስ አበባ እንደተመለስኩ ቅፅ ላኩላቸውና ሞልተው ልከው ቀንደኛ የጅማ የቅንጅት አባሎቻችን ሆኑ::

ማታ የእራት ግብዣ ነበር:: እራት ላይ ደሞ እርዳታ ማሰባሰቢያ ፕሮግራሙን የምመራው እኔ ነበርኩ::እንግዶቹ ገብተው ቦታቸውን እንደያዙ እኔ ከሥራ ባልደረቦቼ ጋር ተቀምጬ ሳለሁ አቶ ጁነዲን እንደሚፈልጉኝ ተነግሮኝ ሄድኩና ሰላምታ ከተለዋጥን በኋላ ካጠገባቸው እንድቀመጥ ጋበዙኝ:: ፕሮግራም መምራት ስላለብኝ ስለተደረገልኝ ከበሬታ ከልብ አመሰግናለሁ ብዬ፤ወደቦታዬ ልመልስ ስል «አቶ ደበበ፣ ጥላሁን እንዴት ነው? ተሻለው? በጣም የማከብረው ሰው ነው»ብለውኝ በደህና መመለሱን ነግሬ ወደ ቦታዬ ተመለስኩ::ይህን ሳይ በውነት የምርጫው ሂደት በፍቅር የሚከናወን ይሆናል የሚል የልብ ልብ ተሰማኝ:: አቶ ጁነዲን እኔ የቀስተደመና ቅንጅት አባል መሆኔን አውቀዋል፣ በቴሌቪዥንም አይተዋል:: ያም ሆኖ ግን የተቃዋሚ ፓርቲ አባል ነው በማለት ጥላቻ አላሳዩኝም::



እራት ተበልቶ አልቆ የገንዘብ ማሰባሰቢያው ፕሮግራም ሲቃረብ ወ/ሮ አምሳለ የማሕበሩ ሊቀመንበር አስጠርተውኝ ፕሮግራሙን እኔ መምራት እንደማልችል፤የተቃዋሚ ፓርቲ አባል ሆኜ ፕሮግራሙን ብመራ በአዳራሹ ውስጥ ያሉት ባለስልጣናት ሁሉ ጥለው እንደሚወጡ እንደነገሯቸው አሳወቁኝ:: እኔም በጓሮ በኩል ሹልክ ብዬ ወጣሁ:: ነገሩ ግን በጣም አስገርሞኛል:: «ታዲያ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ጠርተውኝ አጠገባቸው እንድቀመጥና ስለጥላሁን የጠየቁኝ፣ አክብሮት ያሳዩኝ ቁንጮው የኦሆዴድ ሹመኛ ለምን ያን አመለካከት አሳዩኝ? ዲፕሎማሲ መሆኑ ነው? ወይስ ለታይታ ያህል የፈለጉት ነገር ኖሮ ነው?» ብዬ እየተገረምኩ ነው የወጣሁት::

ከወጣሁ ከ20 ደቂቃ በኋላ ሞባይል ተደወለ፤የሥራ ባልደረባዬ ነበር:: «ምን ፈለክ?» ስለው «የት ነህ?» አለኝ:: ቡና ቤት እየጠጣሁና ከሰዎች ጋር ሞቅ ያለ ጨዋታ ላይ እንዳለሁ ነገርኩት:: «እባክህ ቶሎ ድረስ» አለኝ:: «ለምን?» ስለው ፕሮግራሙ ቆሟል፤ ለምን? አልኩት:: ሁሉም አንተ ካልመጣህ አይሆንም ብለዋል፣ ቶሎ ና! አለኝ:: «ምን ማለትህ ነው? የተባለው እኮ እኔ ፕሮግራሙን.. .. ..» ስል «እሱን ተወውና ቶሎ ና! እባክህ ሊበላሽ ነው» አለኝ:: ደግነቱ ሩቅ አልነበርኩምና ደረስኩ:: እኒያው ፕሮግራም አትመራም ያሉኝ ሴት ተቀብለውኝ፤« እባክህ ቶሎ ጀምርልን» ሲሉኝ:: «ቅድም ምን አሉኝ?» ስላቸው፣ «በቃ ተወው፣ ይቅርታ! ብቻ ፕሮግራሙን አሳምርልኝ» አሉ::ምርጫ አልነበረኝም::ያንን በሌላ ሰው ተሞክሮ ያልተሳካውን ፕሮግራም አሳክቼ ማንነቴን ማሳወቅ ትልቅ ድል ነውና ገባሁ::

እዚህ ላይ በጣም የገረመኝ ነገር ቢኖር ያ የድርጅቱ ባለቤት የሆነው ግለሰብ፣ያ እኔን እንደተአምር ሰሪ አድርጎ ሲያየኝ የነበረ ሰው፣ ፕሮግራሙን አትመራም ስባልና ወጥቼ ስሄድ አንድም ቃል ትንፍሽ አለማለቱ ነው::ፕሮግራሙ ከተጠናቀቀ በኋላ ስለዚህ ጉዳይ አንስተን ስናወራ ጠይቄው ነበር::«ነጋዴ ነኝ እኮ! እንደዚያ አይነት ተቃውሞ ባሰማ ሁለተኛ ከኔ ጋር

አንሰራም ሊሉ ስለሚችሉ ዝም ማለት ነበረብኝ» አለኝ:: ይህንኑ ጉዳይ ስንወያይና ልክ እንዳልነበረ ሳስረዳው፣ ባይገባውም እራሱን መነቅነቁንና እንደተቀበለ ማመኑን አልተወም:: በዚሁ ላይ እንዳለን እኒያ የማህበሩ ሊቀ መንበር ሴትዮ መጥተው ካጠገባችን ተቀምጠው ስለሁኔታው ሊያስረዱ ሲሉ፣ የድርጅት ሃላፊው ሰው ትክክል እንዳልነበሩ ሊያስረዳ ጀመረ:: «ተው እንጂ ማታ ያልከው እንደዚህ አልነበረም:: ማታ አቶ ደበበ ፕሮግራሙን ማካሄድ አይችልም ስልህ፣ ግድ የለም ሌላ ሰው እናደርጋለን፣ አያሳስብም አልነበረም ያልከኝ?» ሲሉት ተነስቼ ከጠገባቸው ሄድኩ::አይልም ብዬ ማመን ያዳግተኛል::

እውነትም እግዚአብሔርም፣ሕዝብም ይወደኛል፣ ስገባ በጭብጨባ ተቀበሉኝ::ወዲያው ፕሮግራሙን ጀምሬ እንደተመኘሁትም የተሳካ ገቢ ተሰበሰበ::

እዚህ ላይ ማንሳት የምወደው በፕሮግራሙ ሂደት ሁሉ አቶ ጁነዲን ሳዶ ያናግሩኝና ስለጨረታው ይጠይቁኝ የነበረው በአክብሮት ነበር:: ይህን ሳይና ለውጥ እንዳለና ምርጫው ሰላማዊና ፍትሓዊ ይሆናል የሚል ከግማሽ በላይ እምነት አደረብኝ::ቀደም ሲልም «ለምን?» የሚል ጥያቄ ያነሳሁበትን ሁኔታ እኔው እኔን ታዘብኩህ አልኩና ሰዎች ፍላጎታቸውን በሰው ስም አስታከው መፈጸም፣ ወይም እወደድ ብለው ሊያከናውኑት እንደሚችሉ ተረዳሁ:: እኚህ ሴትዮ ካጥፊ፣ካስወቃሽ፣ከራስ ወዳድና ከአልኩ ባይ ካድሬዎች ወገን የሚሰለፉ ናቸው::

አቶ ጁነዲን የቅንጅት አባል መሆኔን ያውቃሉ፣ በቴሌቪዥን አይተዋል፣ ያም ሆኖ አንዳችም ለውጥ አላየሁባቸውምና ስጋቴ በጣም ቀነሰ:: ሴትዮዋ ያልተባሉትን «ተባልኩ» ያሉበት ምክንያት እስካሁን ምን እንደሆነ ባላውቀውም፣ በግምት ግን እንዳሰቡት ቢሳካላቸው ኖሮ ለባለስልጣናቱ፣ እኔ የተቃዋሚ ድርጅት አባል በመሆኔ፣ ያባረሩኝ መሆኑን በምሽቱ በሚያገኙት አጋጣሚ በመንገር ቆራጥ የማህበር መሪ በሚል ከበሬታ ሊያገኙ አስበው የነበር ይመስለኛል::



አንዳንድ ትናንሽ ባለስልጣናት ትልቅ የሚባሉት ባለስልጣኖች ፊት ያላሰቡትን በመከወን፣ ለራሳቸው ዝና ለማግኘት ታማኝ ለመባል በሚያደርጉት የራስ ወዳድነት ሂደት በሚመሩት ድርጅት ላይ ምን ያህል ጉዳት እንደሚያደርሱ ይህ አንዱና በጣም ትንሹ ምሳሌ ሆኖ አግኝቼዋለሁ::

## የምርጫ ዘመቻ

የሕዝባዊ ስብሰባ በይፋ የተጀመረው ምርጫው ጥቂት ወራት ሲቀሩት ቢሆንም ገዢው ፓርቲ ግን በሚያዝዛቸው መገናኛ ብዙሃን በተለያየ ርዕስ ኢህአዴግ ያደረጋቸውን የልማት ውጤቶችን ማስተዋወቅንና ለምርጫው የሚረዱትን ጉዳዮች ሁሉ ለሕዝብ ማቅረቡን በጣም ቀደም ብሎ ነበር የጀመረው:: በጣም ያስገረመኝ ጉዳይ ገዢው ፓርቲ በመንግሥትነቱ ባአለበት ግዴታ ያደረገውን ሁሉ ኢህአዴግ ልዩ ሕዝባዊ፣ ሃገራዊ እንደሃነ ተደርጐ እንደአስተዋጽኦ እንዲቆጠርለት ሲያቀርብ የተቃዋሚዎችን ሃገራዊና ሕዝባዊ አስተዋጽኦም በሙሉ በመንጠቅ ነበር:: ቀደም ብሎ አቶ በረከት ገዢው ፓርቲ እንደሚመረጥ እርግጠኛ በመሆንና በተኩራራ ስሜት ለአንድ ጋዜጣ በሰጡት ቃለ ምልልስ እንዲህ ነበር ያሉት::

*ጥያቄ -«የኢህአዴግ አባላትና ካድሬዎች በምርጫ ወቅት የማጭበርበር ድርጊት እንዲፈፅሙ በተቃዋሚ ፓርቲዎች ላይ ወከባ እንዲያደርሱ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸዋል» የሚል ዜና ተሰምቷል:: ይኸ እውነት ሆነ ወይ?*

**መልስ -«አልጨረስነውም እንጅ ይኸውና በምርጫው ወቅት የኢህአዴግ አባላትና ደጋፊዎች የሚከተሉት የስነ-ምግባር ደንብ አዘጋጅተናል:: በዚህ ደንብ ላይ አባሎቻችንን እናወያያለን፣ እናሰለጥናለን:: ይህን ደንብ የሚጥስ አባል ከሁሉ በፊት ከድርጅቱ ይወገዳል:: የአገሪቱን ህጎች የጣሱ ደግሞ እንዲጠየቁ ይደረጋል:: ይህም በጥብቅ ተግባራዊ ይሆናል:: ከሁሉም**

በላይ ይህ ምርጫ ጥቁር ነጥብ የማይጣልበት እንከን የለሽ ምርጫ እንዲሆን ነው እየሰራን ነው ያለነው።»

*ጥያቄ -አሁን እንዲህ ልትሉ ትችላላችሁ ነገር ግን የምርጫው ዕለት እየተቃረበ ሲመጣና በምርጫው ወቅት ተቃዋሚ ፓርቲዎች የሚያሸንፉ አይነት ሆነው ቢታዩአችሁስ ዝም ትላላችሁ? ወደ ወከባና ተፅእኖ አታመሩም?*

መልስ -ለምን? ከተሸነፍንኮ ምክንያት ይኖረዋል። ያለምክንያት አትሸነፍም። ኢህአዴግ የሚሸነፈው ህዝቡ አመኔታ ካጣበት ነው። ሕህቡ አመኔታ ካጣብንና በአቋማችን ላይ ደስተኛ ካልሆነ አልመርጣችሁም ይለናል። ሉአላዊነት የሚባለው እኮ ይሄ ነው። ስለዚህ የግድ እንቀበላለን። አንቀበልም ብንልስ የት እንደርሳለን? ዛሬ አንድ ፓርቲ በማጭበርበር ስልጣን ላይ መቆየት የሚችልበት ዘመን አይደለም። በማጭበርበር ወይም በወከባ የህዝቡን የመምረጥ መብት የተጋፋም የትም አይደርስም። ሕዝቡ ወደ አደባባይ ይወጣል። ይኸ የማይቀር ነገር ነው። በቅርቡ በውጭው አለም እንዳየነው አንድ ፓርቲ ምርጫ ላይ ጥፋት ሲፈፅም ሕዝቡ አደባባይ ወጥቶ ለሳምንት መንገዶችን በማጥለቅለቅ ተቃውሞ እንዳደረገ ይታወቃል። ያጭበረበረውን ፓርቲ አንበርክኳል። ዛሬ የዲሞክራሲ ዘመን ስለሆነ ሁሉም ነገር ግልጥልጥ ብሎ ዓለም ሁሉ ያየዋል። በማጭበርበር ስልጣን ላይ መቆየት አይቻልም ለሕዝቡ የሚቀርብ ሀሳብ በማቅረብ እንጂ። ስለዚህ በገጠርም ሆነ በከተማ ሕዝቡ ኢህአዴግን ይመርጣል የሚል ተስፋ አለን። ነገር ግን በሆነ ምክንያት ካልተመረጥን የሕዝቡ ውሳኔ የግድ ተግባራዊ ይሆናል።»ነበራ የተገባው ቃል።

ኢህአዴግ ስልጣን በያዘ ማግስት ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ጋዜጣዊ መግለጫ በሰጡበት አንድ ፕሮግራም ላይ ጋዜጠኞችን በተመለከተ፣ *«እናንተ ጋዜጠኞች! በደርግና ከዚያም በፊት ስታደርጉት እንደነበረው በሥልጣን ላይ ላለው መንግሥት ትእዛዝ ብቻ መስራታችሁን ማቆም ለሕዝብ እውነቱን ማቅረብ*



*የሙያ ግዴታችሁ ማድረግ ይኖርባችኋል»* ያሉትን አደራ በመብላት ሽንጣቸውን ገትረው በመንግሥት መገናኛ ብዙሃን ያልተሰራውን ሁሉ የኢህአዴግ ገድል አድርገው ማቅረባቸውን ተያያዙት።

«. . . . . . በመንግሥት ትእዛዝ ብቻ መሥራታችሁን አቁሙ» የሚለው መመሪያና ምክር ከስሩ ያለው እውነተኛው ትእዛዝ ሲታይ መንግሥትን ሰማየ ሰማያት ከማውጣት ውጪ ፤መንግሥትን ቅዱስ ወቅዱሳን ከማድረግ ሌላ፤ መንግሥት ሲያጠፋም አበጀህ፣ ሲሳሳትም እሰየው የኔ ጌታ ከማለት ባሻገር ትንፍሽ ብትሉ በግምገማ እቶን እየተቃጠላችሁ እንደምታልቁ እወቁት» የሚል መሆኑን በዚህ የምርጫ ወቅት በሚገባ የታየ ገሃድ ሆነ።

ለደንቡና የምርጫ ቦርድ ላወጣው ሕግና ስርአት ተገዢነታቸውን ያረጋገጡት ተቃዋሚች እንጂ ወያኔ ኢህአዴግ ህግ አውጪ ፣ ህግ ተርጓሚና አስፈፃሚም በመሆን ባለው ዘዴ ሁሉ እንደልቡና እንደሚመቸው ሲያደርግ ´ተው´ የሚለው ቀርቶ፣ ይሉኝታ እንኳን ይዞት ´እንዴት ነው ነገሩ?´ ያለ ሃይል አልነበረም።

ሕጋዊው የምርጫ ወቅት እስኪደርስ ድረስ ወያኔ ኢህአዴግ የሚያቀርባቸው ተዘዋዋሪ የምርጫ ቅስቀሳች ምንም ያልጠቀሙ መሆናቸው በምርጫው ጊዜ በገሃድ ቢታዩም ወያኔ/ኢህአዴግ ማስፈራሪያም፣ መፎከርያም፣ ማንአለብኝነትም ያሳየበት ነበር። በዚህ ወቅት ነው የገዢው ፓርቲ አምባገነንነት ነጥሮ የወጣውና የተደበቀ ማንነቱ መታየት የጀመረው። '*ዝንጀሮ የቂጧ ጠባሳ የሚታየው ዛፍ መውጣት ስትጀምር ነው*' የሚባለውም በተግባር በወያኔ/ኢህአዴግ ላይ የተመሰከረው በዚሁ ወቅት ነበር።እዚህ ላይ ነው በመንግሥትና በፓርቲው መሃል ያለው ልዩነት የተደባላለቀብኝ። ሁለቱ ተነጣጥለው መቅረብ አልቻሉም።

ተቃዋሚ ፓርቲዎች መንግሥት ስላልነበሩ፤ፕ ሮግራማቸውን ከማስተዋወቅ፣ የዴሞክራሲንና የሰብዓዊ

መብትን መርህ ከማስተማር ሕዝብን ከማንቃትና ከማደራጀት ውጭ፣ በሃገር አቀፍ ደረጃ ልማት አልሰሩም ሊባል አይገባም ነበር። ግን መንግሥትም የኢህአዴግ ካድሬዎችም ቅስቀሳቸውና ጥያቄያቸው በዚህ ላይ ያረፈ ነበር።እንደመንግሥት የሚንቀሳቀስና ፓርቲና ተቃዋሚ ፓርቲ ብዙ ልዩነት አላቸው። የመንግሥት ሥልጣን የያዘ ፓርቲ የመንግስትን በጀትና መዋቅር ይጠቀማል፤ በመንግሥት የሰው ሃይል፣ አባልም ሆነ አልሆነ፣ ይገለገላል። በመንግሥት ተሽከርካሪና ነዳጅ ይዘዋወራል። ተቃዋሚዎች ይህ ሁሉ እድል የላቸውም ብቻ ሳይሆን ምንም ነገር ለማድረግ የመንግሥትን ፈቃድና ይሁንታ ማግኘት አለባቸው።

የግንቦቱ ምርጫ ነፃና ፍትሃዊ በሆነ መልኩ እንዲካሄድ አስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ፤በተለይ ምርጫ ቦርድን በተመለከተ መልሶ ለማዋቀር፤የሚዲያ አጠቃቀም እና ሌሎችም ጉዳዮች ለውይይትና ለድርድር ጥያቄ ቀርቦ ገና ምላሽ አላገኘም። ትንሽም ቢሆን ድርድር የተደረገበትና ምላሽ ያገኘው የሚዲያ አጠቃቀም ነበር። ይህም ስምምነቱ መፈረሙ እንጂ ተግባራዊነቱ በእኩልነት የታዬ አልነበረም። ገዢው ፓርቲ በዜናም፣ በልዩ ፕሮግራምም፣ በተለያዩ ርእሶች፣ ለምርጫ ቅስቀሳ የሚሆኑ ፕሮግራሞች እያቀረበ ነው።በተቃዋሚዎች በኩል ከዚያችው ከተቆነጠረችላቸው ሰአት በስተቀር ትንፍሽ ማለት የሚቻልበት መንገድ አልነበረም።

‘ቅንጅት ምን ሰርቷል? ለሕዝቡ ይህን አድርጌያለሁ የሚለው ምን አለው?’ ይላሉ ካድሬዎቹ። እርግጥ በአንድነት የተቀናጁት ፓርቲዎች ረጂም የትግል ዓመታት አስቆጥረዋል። ያም ቢሆን፣ ከላይ እንደጠቆምኩት ሁሉ መንግሥት አልነበሩምና እንደገዢው ፓርቲ ይህን አደረግን ብለው በሃገር ደረጃ የሚያቀርቡት አይኖራቸውም። ሊኖራቸው የሚችለው ከቅንጅት አቻ ፓርቲዎች መሃል ባለፉት ምርጫዎች አሸንፈው ፓርላማ የገቡት አባላት ያደረጉት አስተዋፅኦና



ከሕዝብ ወግነው ያደረጉዋቸው ክርክሮችና ያቀረቡዋቸው የበደል ሪፖርቶች ናቸው። ይህን ሳስብ ወያኔ ኢህአዴግ በቅስቀሳው ወቅት፣ በተለይም በመገናኛ ብዙሃኑ በሬዲዮና በቴሌቪዥን በሚያቀርበው ቅስቀሳ እንዴት ገዝፎና ተቀባይነት አግኝቶ ሊሄድ ይችላል የሚለው ትልቅ የቤት ሥራ ነበር።

ሕብረተሰቡ ከአሁኑ ለቅንጅት ፍቅር እያሳየ ነው፤ ይህ ደግሞ በማስረጃ በሚቀርብ ፕሮግራም ተደግፎ የሕዝቡን ልብ የሚያሸንፍ ካልሆነ ዋጋ አይኖረውምና በጥንቃቄ፣ በቡድን ተጠናክሮ መሥራትን ይጠይቃል።በመኢአድ ቢሮ በርካታ የቪድዮ ዶኩሜንቶች አሉ፣ በማስረጃነት ተጣቅሰው ሊቀርቡ የሚችሉ። በጣም ጥቂት የዶኩሜንት ፊልም ደግሞ ከኢትዮጵያ ቴሌቪዥን መጠየቅ ነበር፣ ሌላው አማራጭ። ከመኢአድ ያለምንም ችግር ይገኛል፤ ከቴሌቪዥንስ?

ለቴሌቪዥን ደብዳቤ ተፅፎ ሲጠየቅ በደቂቃ 300 ብር ተጠየቀ።የምንፈልገውን ሁሉ በዚህ ዋጋ እንግዛ ብንል በሌለ ገንዘብ የማይቻል ነውና ሊገኝ ከሚችልበት ሁሉ፤በግለሰብ እጅ ያለውን ማጠያየቅ ስንጀምር በርካታ ዶኩሜንቶች ተገኙ።ያንን አሰባሰብን።አንዳንድ የኢህአዴግ ባለስልጣኖችም በጃቸው የሚገኘውን የቪድዮ ዶኩሜንት በተዘዋዋሪ ላኩልን። በዚህ መልክ የተቻለው ሁሉ ተሰባሰበ።ገዢው ፓርቲ የዚህ ሁሉ ችግር የለበትም። ቴሌቪዥን ጣቢያው በጁ ስለሆነ የሚፈልገውን ፊልም ብቻ ሳይሆን ባለሙያና ስቱድዮ ጭምር በነጻ መንግስት በሚከፍለው ዋጋና ደመወዝ እያንደፋደፈ ያሰራቸዋል።

ሕጋዊው የምረጡኝ ቅስቀሳ በይፋ ሲጀመር ተቃዋሚ ሃይሎች በየቦታው ስብሰባ ሲጠሩ የሕዝቡ ተሳታፊነት ቁጥር፤ፍቅሩ፤ተባባሪነቱና ከጎናችሁ ነን ማለቱ እየተጠናከረ መጣ። ያ ደሞ ለጊዜው፣ ወያኔ ኢህአዴግን ምንም አልመሰለውም ነበር። ‘ጊዜያዊ ፍቅር፤ መጨረሻው የማያምር፤’ ነበር የተባለው፣

በሕወሃት መንደር:: ካድሬዎችና የሕዋሃት ሹማምንት - ቁንጮዎቹን ጨምሮ ለበላይ አካላቸው የሚያቀርቡት ዘገባ 'በተጠራው ስብሰባ ሕዝቡ እንዳይሳተፍ፤ ቢሳተፍም የኛ ካድሬዎች ፈታኝ ጥያቄ እንዲያነሱና ተቃዋሚዎቹን መልስ በማሳጣት እንዲዋረዱ አድርገናል' የሚል ሃሰትና መሰረት የሌለው ሪፖርት ስለነበር፣ አመራሩ ተዝናንቶና ተዘናግቶ በእርገጥኝነት እንዲቀመጥ አደረገው::

## ከአንዳንድ ስብሰባዎች ናሙናዊ ዕይታ

በምኒልክ ትምህርት ቤት በተደረገ የመጀመሪያ ሕዘባዊ ስብሰባ ላይ ሕዝብ እንዳይመጣ በቀበሌ የቤት ሥራ ማህበራትና ሌሎችም ስብሰባዎች ቢጠሩም፣ ሕዝብ ግን አሻፈረኝ በማለት ወደ ምኒልክ ትምህርት ቤት ከስብሰባው እጅጉን ቀድሞ ነበር የመጣው::በስብሰባው ላይ የተገኙት የወያኔ ካድሬዎች ያነሱት ጥያቄ፣ ለመልስ የቅንጅቱን አመራር ሳያስጨንቅ በቀላሉ በተሰብሳቢው ሕዝብ መልስ እየተሰጠበት ጠያቂችዎን ያጋለጠና ካድሬም አዳራሹን ጥሎ የወጣበት ሁኔታ ነበር የታየው:: ይህም ለወያኔ ኢህአዴግ አመራር ሲዘገብ ሕዝብ እንዳልተሳተፈና ጥቂት ሰዎች የተገኙበት የማያሳስብ ስብሰባ እንደነበር ሆኖ ነውና፤ አመራሩ ሃሳቡን ጣለ::

በደብረዘይት በተደረገው ሕዝባዊ ስብሰባ በቅድሚያ የአዳራሹ ኪራይ ተከፍሎ ለሕዝብ ጥሪ ተደርጎ እኛም በሰአቱ ስንደርስ፤ቀድሞን ሄዶ የነበረው ዶ/ብርሃኑ ደብረዘይት ፖሊስ ጣቢያ ግቢ ውስጥ ከጣቢያው ሃላፊ ጋር ይነጋገራል:: ምክንያቱ አልገባንምና 'ምን ተፈጠረ?' ስንል ስብሰባው መከልከሉን ነገሩን:: የከተማው ፖሊስ ስብሰባውን ለማካሄድ እንድንችል አስፈላጊውን ጥበቃና መሰናዶ ያደረገ ቢሆንም፤ የከተማው አስተዳደር ሃላፊ ግን



ከከተማው ውጪ የገጠር ፖሊሶችን አምጥቶ ስብሰባውን መከልከሉን፣ እሱም ስልኩን ዘግቶ ከአካባቢው እንደተሰወረና ለማግኘትም የተደረገው ሙከራ እንዳልተሳካ፤ይሄው አስተዳዳሪም ተመራጭ እንደሆነ ተነገረን::ጉዳዩን ለማረጋገጥ ስንል ተሰባስበን ወደ አዳራሹ በመሄድ የአዳራሹን ሃላፊ ስናነጋግረው፣ 'እኔ አከራይቻለሁ ግን አስተዳዳሪው ማስጠንቀቂያና ገደብ ስለአደረጉብኝ መመሪያውን ተቀብዬ ዘግቻለሁ:: አሁንም ክፈት ካሉኝ እከፍታለሁ ምክንያቱም አዳራሹ በአስተዳደሩ ስር ነው' አለ:: ምን ያድርግ መመሪያውን ጥሶ የት ሊገባ? አልፈረድንበትም::

ዶ/ር ብርሃኑ ችግሩን ለአቶ በረከት በመደወል ቢያሳውቅም አስተዳዳሪው በስልክ ሊገኝ ባለመቻሉ መፍትሔ አልተገኘም:: በአዳራሹ የተሰበሰበው ሕዝብ ያቀረበው አማራጭ፣ "ሜዳ ላይ እንሰብሰብ" ነበር፤ ያ ደግሞ ˎ የተለያየ የራሱ ችግር አለው:: በቅድሚያ አስተዳዳሪው ከደብረዘይት ከተማ ውጪ ያመጡት የፖሊስ ሃይል ከከተማው ፖሊስ ጋር ግጭት ሊፈጥር ይችላል:: ይህ ደግሞ አጉል ነው:: በሌላ በኩል የከተማው አስተዳዳሪ የከለከሉትን የአዳራሽ ስብሰባ በሚያስተዳድሩት የከተማ ሜዳ ላይ ማድረግ አይቻልም:: ስለዚህም ያለው አማራጭ ሌላ ፕሮግራም መያዝ ብቻ ነው:: ስለዚህ በቦታው ለተገኙት የመገናኛ ብዙሃን ዘጋቢዎች ሁኔታውን አሳውቀንና እነሱም የሚመለከታቸውን አነጋገረው የዕለቱ ስብሰባ ተሰርዞ ሕዝቡም እኛም ተበሳጭተን ተለያየን:: ይህ አይነቱ የስብሰባ ክልከላ ሕብረተሰቡን ለምን የሚል ጥያቄ እንዲያነሳ፤ጥርጣሬ እንዲኖረው፤ከወያኔ ኢህአዴግ ጋር እንዲራራቅ አድርጎታል:: ይልቁንም ለቅንጅት ተጨማሪ ሃይል በማስታወቂያነትም በኩል ቢለካ በጣም ከፍተኛ ትርፍ ያስገኘ ነው::

ሕብረተሰቡ ለዴሞክራሲያዊ ሥርአት ግንባታ ቆርጦ ከመነሳቱ አኳያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችም ሰፊ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ እየፈጠሩ ናቸው::ተቃዋሚ ድርጅቶች ያሏቸው ድክመቶች እንደተጠበቁ ሆነው፣

በአጭር ጊዜና ባነስተኛ አቅም የፈጠሩት ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ተይቶ የማይታወቅ ድል ነበር:: በኔ አመለካከት ለዚህ ድል ደግሞ የወያኔ ኢህአዴግም ያላዋቂ አስተዋፅኦ አለበት:: ይህን ለማለት ያበቃኝም የደብረዘይቱ ስብሰባ መክልከል ያስከተለውን ሕዝባዊ ስሜት በማየት ነው::

የደብረ ዘይት ስብሰባ መክልከል ማታውኑ በሬድዮም በቴሌቪዥንም ቀረበ::ይህንን ያዳመጡት አቶ ጁነዲን ሳዶ ለቅንጅት አመራር ደውለው በሁኔታው ማዘናቸውንና በአስተዳዳሪውም ላይ እርምጃ እንደተወሰደ ገለጡ::ይህ ይባል እንጂ አስተዳዳሪው ከቢሮው ንቅንቅ አላለም ነበር፣ ማስተዳደሩንም ቀጥሏል:: ከ15 ቀናት በኋላ የደብረዘይት ስብሰባ እንደገና ሲጠራ ባለፈው ከመጣው ቁጥር በእጥፍ የጨመረ ሕዝብ ነቅሎ መጣ፣ ቦታም ጠበበ:: የድምፅ ማጉያ በመጨመር ውጪ ያለውም ሕዝብ እንዲሳተፍ ተደረገ:: በውይይቱ ላይ የተነሱት ጥያቄዎች የትምሕርት፣ የጤና፣የመሬት ፖሊሲን የሚመለከቱና ስለሃገር ሉአላዊነት፣ ስለአንድነት፣ስለልማት ነበሩ:: በየአንዳንዱ ነጥብ ላይ ፖሊሲያችን ላይ በሰፈረው መሰረት ማብራሪያ ተሰጥቶ ውይይት ተደርጎበት ስብሰባው በሚያስደስት ሁኔታ ተፈፀመ::

የትም ቦታ ቢሆን ካድሬዎች በሕዝቡ መሃል ያሉና ጥሩም ይሁን መጥፎ ተግባራቸውን የሚያከናውኑት በሕዝብ መሃል ሆነው ነው::በሕዝባዊ ስብሰባ ላይ ሲገኙ ሕዝቡ ያውቃቸዋል::ጥያቄም ጠየቁ፣ አስተያየት ሰጡ ሕብረተሰቡ ከቆሙለት ፓርቲ ጋር ፈርጆ ነው የሚያዳምጣቸው::እነሱም ለመናገር ሲነሱ በጥላቻ፣ በንቀትና በማንአለብኝነት ስለሆነ ብዙ ጊዜ ተቀባይነት የላቸውም:: እኔ ይህን እንደ ወያኔ ኢህአዴግ ድክመት አይቸዋለሁ:: የሕበረተሰቡን አዝማሚያ ካዩ በኋላ እንኳን፣ በደብረዘይት ለሚደረግ ስብሰባ ከአዲስ አበባ፣ በናዝሬት ለሚደረግ ስብሰባ ደሞ ከሞጆ፣ በማምጣት ማንነታቸውን ሰውሮ የሚፈለገውን



መልእክት እንደ ነጻ ተሳታፊ ግለሰብ ማቅረብ ያስችል ነበር::

ሌላው ያየሁት ድክመት የትም ይሁን የት የገዢው ፓርቲ ካድሬዎች የሚያነሷቸው ጥያቄዎች ቅደም ተከተላቸው እንኳን አይለወጥም:: *"ምን የተለየ እቅድ አላችሁ? ስለብሔር ብሔረሰቦች እኩልነት? ስለ ኤርትራ ሬፈረንደም? ስለአሰብ? ስለባድመ? ስለሴቶች? ስለገጠሩ አርሶ አደርስ? "* የሚል ተደጋጋሚ ሀሳብ ነው:: ርእሱም፣ቅደም ተከተሉም፣ሁሉም ቦታ ይሄው ነው::ወደ ክልሎችም ከዚህ የተለየ አልነበረም::

ደሴ በተጠራው ሕዝባዊ ስብሰባ ላይ ለመገኘት በወጣው እቅድ ላይ ደብረብርሃንንም አብረን ያዝነው::ቅዳሜ የደብረብርሃንን አካሂደን ጉዞ በማድረግ ደሴ ገብተን ለማደርና ዕሁድ ጠዋት ስብሰባውን ለማድረግ በወጣው እቅድ መሰረት ደብረብርሃን ቅዳሜ ጠዋት ስንደርስ የገበያ ቀን በመሆኑ የጠበቅነው ጥቂት ሕዝብ ነበር::የኛን መድረስና የስብሰባውን እርግጠኛነት በማየት 15 ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ አዳራሹ ጠቦ ቡና ለመጠጣት ከገባንበት ቡና ቤት ተጠርተን ስብሰባውን ጀመርን:: የሕዝቡ ተሳትፎ እጅግ የሚያረካና የሚያስደስት ነበር:: እዚህም ያው ለውጥ የሌለው የኢህአዴግ ካድሬዎች ጥያቄ አልቀረም::

ከደብረ ብርሃን ጋር ልዩ ትዝታ አለኝ::በመጀመርያ መምህራን ማሰልጠኛ ነበርኩና አስታውሰዋለሁ:: በኋላም ከባለቤቴ ጋር የጋብቻ ሥነስርአታችንን የፈጸምነው በደብረብርሃን ሥላሴ ባማረና በደመቀ ሁኔታ በመሆኑና ያም ጋብቻችን የተባረከ ሆኖ ልጆች ያፈራንበት የኖርንበት በመሆኑ አይረሳኝም::

ስብሰባው ተጀምሮ ዓላማና ተግባራችንን ካስተዋወቅን በኋላ ወደ ሕዝባዊ ውይይት ገባን:: በዚህም እንደተለመደው ቅድሚያውን ለካድሬዎች አደረግን፣የአካባቢው ካድሬ ጥያቄ ደሞ አንድ ጥያቄ

ተጨምሮበታል:: «ስለአሰብ ጉዳይ::እንደገና ጦርነት ልታስነሱ ነው የሚል» እኛ ለዚህ መልስ ከመስጠታችን አስቀድሞ ቤቱ በሙሉ መልስ ሰጪ ሆነ::ሉአላዊነትን ለመድፈር የሚደረግ ደባን አንቀበልም:: ማን ስለጦርነት አነሳ? አንተ ነህ ያልከው:: ሁሉም ጮኸ::ከኛም በኩል «አግባብ ያለው ሰላማዊ ዓለም አቀፍ ዳኝነት የሚኖርበት የዲፕሎማሲያዊ ሂደት ይደረግበታል» አልን::

ከዚያም የሕዝቡን ጥያቄ አስተናግደን መርቀውን መንገዳችንን ወደ ደሴ ቀጠልን:: በደብረብርሃን ስብሰባ የማይረሳኝ፣ ካድሬዎች ጥያቄ ሲያቀርቡ ተዘሎ ይሁን ወይም አቅራቢዎች ተደናግጠው የብሔር ብሔረሰቦችን ጉዳይ ሳያነሱት ቀሩ:: "ይህን ጉዳይ ዘላችሁታልና በኋላ እንዳያስገመግማችሁ እኛው አንስተን" መልስ እንስጥበት ተብሎ ጥያቄውም መልሱም ተስተናገደ::በአዳራሽ ያለው ሕዝብ በሁኔ□ውም፣ በተሰጠው መልስም ረክቶና አካሄዳችንም አስገርሞት ተለያየን::



ጉዟችንን ወደ ደሴ ቀጠልን::እግረ መንገዳችንን ያየነው ሁሉ የሚያሳዝን ነበር:: ደብረሲናን እንዳለፍን ዛፉ በሙሉ ተጨፍጭፎ ለማገዶነትና ለሌላም ተግባር፣



ያውም ለጋ ለጋው እየተመረጠ፣ ተጨፍጭፎ አየን::ማን አደረገው፣ ብንል «የአካባቢው አስተዳዳሪ ለነጋዴዎች ሸጠውት ነው፤ ያውም ሕዝብ ሳያውቅ፤ ጨረታ ሳይወጣ፣ 'በአወቅሁሽ ልጥቀምሽ' መንገድ ነው የተሸጠው» አሉን:: «እኛ ይህን የተከልነው አካባቢው ዛፍ አልባ ሆኖ ዝናቡም ርቆታል፤ በረሃ እየሆነ ነው ተባብለን በጂጊ ወጥተን ነበር:: አሁን ይህ ጉልበተኛ አስተዳዳሪ እንዲህ አደረገው:: ለማን አቤት ይባላል? የት ይጮሃል?» ብለውን ተለያየን:: ድርጊቱ እጅጉን የሚያሳዝን ነው:: "ምናለ ሌላው ቢቀር አሮጌውን ዛፍ ቢያስቆርጡት" ተባብለን መንገዳችንን ቀጠልን::

ከዶ/ር ብርሃኑ ጋር የመጓዝ አንዱ ችግር ምሳ የሚሉት ነገር እሱ ጋ ብዙ ጊዜ አይታወቅም:: "እንብላ" ሲባል "እሚቀጥለው ከተማ እንበላለን" ይልና ስንደርስ ደሞ፣ "የሚቀጥለው" እያለ አሰብንበት መድረስ እንጂ እንዳሰብነው አንበላም:: ዛሬም ያው ነው::

ምሳ ታስቦ ታለፈ ስንል ድንገት ምን እንዳሰኘው ሳይታወቅ "ምሳ እንብላ እንጂ!" አለ:: ቶሎ መኪና አስቁመን ገባን:: ቶሎ ቶሎ በልተን መንገዱን ተያያዝነው::

ቀኑን ስንጓዝ ውለን ደሴ ከምሽቱ 3:30 ደረስን::እንደገባን ለሁለት ተከፈልን:: አንዱ ወገን ደክሞት ሲተኛ ጥቂቶች ደሞ፤ "ደሴን በምሽት፣ ሕዝቡን በየመዝናኛው ቤት እንየው፤ስሜቱን እንረዳ፤ፍላጎቱን ለማወቅ እንዘዋወር" ያለው ነበር::በዚሁ ተከፋፍለን ስንዘዋወር ከአንድ በከተማው መሃል ወዳለ መዝናኛ ስንገባ ቤቱ ተጣቧል:: የኛን መምጣት ያየ ሁሉ ከውጪ ወደውስጥ ስንገባ ቦታ ይዞ በመዝናናት ላይ የነበረው በእንኳን ደህና መጣችሁ ስሜት እያቀፈ ቦታውን እየለቀቀ ተቀበለን:: ድንገት በኛ መምጣት የቤቱ ጠረን ሁሉ ተለወጠ፣ የደስታ ስሜት ተፈጠረ:: አዝማሪ ቆሞ መሰንቆውን እያገላበጠ በመምታት ያጫውተን ገባ::አንዱ ከፊት ለፊታችን ግጥም ሰጠ፣

ቀኑን ስንጓዝ ውለን ደሴ ከምሽቱ 3:30 ደረስን::እንደገባን ለሁለት ተከፈልን:: አንዱ ወገን ደክሞት ሲተኛ ጥቂቶች ደሞ፤ "ደሴን በምሽት፣ ሕዝቡን በየመዝናኛው ቤት እንየው፤ስሜቱን እንረዳ፤ፍላጎቱን ለማወቅ እንዘዋወር" ያለው ነበር::በዚሁ ተከፋፍለን ስንዘዋወር ከአንድ በከተማው መሃል ወዳለ መዝናኛ ስንገባ ቤቱ ተጣቧል:: የኛን መምጣት ያየ ሁሉ ከውጪ ወደውስጥ ስንገባ ቦታ ይዞ በመዝናናት ላይ የነበረው በእንኳን ደህና መጣችሁ ስሜት እያቀፈ ቦታውን እየለቀቀ ተቀበለን:: ድንገት በኛ መምጣት የቤቱ ጠረን ሁሉ ተለወጠ፣ የደስታ ስሜት ተፈጠረ:: አዝማሪ ቆሞ መሰንቆውን እያገላበጠ በመምታት ያጫውተን ገባ::አንዱ ከፊት ለፊታችን ግጥም ሰጠ፣

"አንሻም ግርግር አንፈልግም ጣጣ፣

ግንቦት መጥቶልሃል፤ልክ እንዳገባብህ ሹልክ ብለህ ውጣ፤"

ሲል፣ ሌላው ይህንኑ ግጥም ወስዶ አሻሽለና ለአዝማሪ "ያዝ" አለው

"የምንስ ግርግር የምንስ ሁከት፣

እንደገባህ ውጣ በዚያው በግንቦት!" ሲል ቤቱ ሆታ በሆታ ሆነ ሌላው ቀበል አርጎ፤

"ይቀጣ ካላችሁ ብአዴን ይቀጣ፣ ይቀጣ ካላችሁ ኢህአዴግ ይቀጣ፣

የ30 ዓመት ሰው እንዴት መሬት ይጣ!"

ሲለው "አበጅህ! አበጅህ!" ባዩ ከየቦታው ገነፈለ:: ለካስ ሁሉም የመሬቱ ነገር አንገብግቦት ነበር:: ጭብጨባ በጭብጨባ ሆነ:: ድገመው እየተባለ ተደጋገመ:: ሁሉም



ገጥሟል:: ይህኛው ግን ወዲያው እንደወረደ የገጠመው የዋዛ አልነበረም::

በደሴ የሚደረገው ስብሰባ በማግስቱ ዕሁድ ከጠዋቱ በ4 ሰአት ነበርና ምናሴ «ቁርስ እንብላ፣ ሰአት አለን» ብሎ ወደ ቁርስ ይዞን ሄዶ ሳለ ወዲያው ስልክ ተደወለ::

"ምነው?"

"አዳራሹ ሞልቷል ድረሱ" ተባልን በጣም የሚገርም ጉዳይ ነው:: የደሴ ሕዝብ ብዙ ጊዜ ስብሰባ ሲጠራ ዘግይቶ ነበር የሚመጣው:: ዛሬ ገና በ3:30 በገዢው ፓርቲ ትእዛዝ የተጠራውን የቀበሌና የእድር ስብሰባ ጥሎ ወደ ቅንጅት ስብሰባ መጣ:: የቀረበልንን ሳንጨርስ ብንሄድም አዳራሹ ተጨናንቆ መተላለፊያ ቦታም የለ:: አዳራሹ አልፎ፤ ግቢው ተጨናንቋል:: የቅንጅት አባላት ወደ መድረኩ ሲወጡ ታቦት የገባ ያህል በእልልታ ግቢው ተናወጠ::

የሚገርም ነው! በአጭር ጊዜ እንዲህ አይነት ተቀባይነትና የሕዝብ ፍቅር ማግኘት አደራው ቀላል አይደለም:: ብዙ ማሰብን፣ ብዙ ጥንቃቄን ይጠይቃል::ሕዝብ ፍቅርን ሲሰጥና ሲወድ ያለውን ሁሉ ሰጠ ማለት ነው:: ተቀባዩ ግን በጥንቃቄ ለሕዝብ ካልቆመና የሕዝብ አክብሮት ካላሳየ፣ ወገናዊነቱን ከላረጋገጠ፣ የህዝብን ጥላቻ ለማግኘትየሚወስደውም በጣም ያጠረ ጊዜ ነው:: ስለዚህ እያንዳንዱ የቅንጅት አባል ከሚቸረው ክብርና ፍቅር አኳያ የማይተናነስ ማንነት ይጠበቅበታል::

የቆየው አስተሳሰብ አሁን በዚህ የ97 የምርጫ ቅስቀሳ ተለውጧል::እገሌ ስላለ ብቻ ሁሉም ያንን ሃሳብ ማጽደቅ፤እገሌ ስለተናደደ ሁሉም መብገንገን፤ እገሌ ሲያነጥስ ሁሉም መዝረብረብ በቅንጅት አምባ የማይታሰብ ነው::ሁሉም የራሱን ጉንፋን፤የራሱን እራስ ምታት ይታመማል:: አመራር ላይ ያለው በሳቀ፣

አባላት ሁሉ አይገለፍጡም ያ:: ጊዜው ያለፈበት የአብዮታውያን ባሕል ሆኖ ተቀብሯል:: ጌታቸው ጀቤሳ (ያሬድ ጥበቡ) ካሜራውን ይዞ ሕዝቡን በግርምት ይመለከታል:: ወደ መድረክ እንዲመጣ ብጋብዘው አልፈለገም::በመግቢያ ንግግር መጀመር የተለመደ ነውና የቅንጅትንም ሰዎች፤ያሬድንም ከባሕር ማዶ የመጣ ደጋፊያችንን ለማስተዋወቅ በሰላምታ ጀመርኩ::

በዚያ መድረክ ላይ በተደጋጋሚ ቴአትር ተጫውቼበታለሁ:: አንድ ጊዜ ደግሞ የወሎ ልማትና ተራድኦ ማሕበር (ወልተማ) በዓል ላይ ጨረታ አካሂጄበታለሁ::ትዝ የሚለኝ፤በዚያ በወልተማ ምሽት ላይ ሼህ ሞሐመድ አላሙዲን ሁልጊዜ የሚሰጡ፤ ዘወትር የሚለመኑ በመሆናቸው ያን ዕለት አዳራሹን ሞልቶ ከተገኘው ታዳሚ ሁሉ በኪሳቸው ያለውን ሳንቲም አሰባስቤ በወሎ ሙዳይ ታስሮ ለሼሁ በእብነ በረድ ፋብሪካቸው ሥራ አስኪያጅ በኩል እንዲደርሳቸው መደረጉ ነው::



አሁን መድረክ ላይ የወጣሁት ለየት ላለ ፕሮግራም ነው፣ ለቅንጅት ሕዝባዊ ቅስቀሳ:: ሕብረተሰቡ አክብሮን በመምጣቱ አመስግኜ፣ በመድረኩ ላይ ያሉትንና ያሬድን አስተዋውቄ፣ የበኩሌን መግለጫ ወርውሬ ለባለተራዎች ለቀቅሁ:: ያሬድ




ካግራሞቱ አልወጣም፣ የሕዝቡ ስነስርአት ገርሞታል:: ያ ሁሉ ሰው አዳራሹን ሞልቶት ከመድረኩ ላይ ከሚናገረው ሰው ድምፅ በስተቀር ሌላ ምንም አይሰማም:: ያሬድን "እንዴት ነው?" አልኩት "እንዲህ ያለ የሰለጠነ ስነስርአት አልጠበቅሁም ነበር" አለኝ::

ሁላችንም የየድርሻችንን ከተናገርንና የቅንጅቱን አቋም ዓላማና ተግባር ምን እንደሆነ ካስረዳን በኋላ እንደተለመደው ቅድሚያውን ለኢህአዴግ ካድሬዎችና ደጋፊዎች ሰጠን::

መድረክ ላይ ሆኜ ሁለት የኢህአዴግ/ብአዴን ቱባ ባለስልጣኖች ከሕዝቡ ለመደበቅ ያህል የጸሀይ መነፅራቸውን አድርገው ሳይቀመጡ ኮለን ተደግፈው አይቻቸው ስለነበር ከነሱ ጥያቄ ስጠብቅ ነበር::በሌሎች እነዚያው አዲስ አበባ ላይ የተነሱት ጥያቄዎች ተነሱና መልሲ ተሰጣቸው::ሌላ ሲባል ደፋር ጠፋና ወደ ሕዝቡ ተመለስን::

የመጀመርያው ተናጋሪ ሙስሊሙ ደጋፊያችን «አቦ እባካችሁ ገላግሉን፤ መሮናል:: አያችሁ በወሎ ብዙ ጊዜ በሽፍታ እንዘረፍ ነበር፤ ታዲያ ሽፍታው ሲዘርፈን ትንሽ ጥሪት ይተውልናል:: በአውቶቡስም ላይ ቢዘርፈን የመኪና መክራያ ይሁናችሁ ብሎ ከወሰደው ይመልስልናል::ያሁኑ መንግሥት ሙጥጥ አርጎ ወስዶ የሚተውልን ቢኖር ድህነትና ችጋር ነው::እባካችሁ ገልግሉን» አሉን::



*(በሃገራችን ብዙ ሽፍታ እናውቃለን:: ለዘረፋ ሲመጣ ለሚመጣው ዓመት ድረስ መቆያ፤ ማገገሚያ ትቶልን ነው የሚሄደው:: ሌላ ዓመት ሲመጣ ቋጥረን እንድንቆየው ነው:: ይሄ መንግሥት ግን ሙልጭልጭ አድረጎ ሌላ ዓመት የሌለ ይመስል ባዶ አርጎን ለዘልዓለም ድህነት ዳርጎን እብስ ነው! አቦ ጦሱን ይገልግለን)*

ሌላው ቀጠሉ፤"ያሁኑ መንግሥት ባህላችንን፣ ልምዳችንን ስለማያውቀው የሚናገረው ሁሉ የሌላ ሃገር እየመሰለን ነው:: የት ቦታ ነው ሙስሊሙና ክርስቲያኑ መቀመጫ ለይቶ፣ መብያ ለይቶ የሚያውቀው ጃል?እንዴት ያለ አበሳ እኮ ነው የገባነው! መስጊድ ስናሰራ ክርስቲያን ወንድሞቻችንም አዋጥተው፤ ቤተክርስቲያን ስናሰራም ሙስሊሙም አዋጥቶ ነውኮ አብረን እንደየፈርጃችን ጸልየን፣ ከአንድ ማእድ ቆርሰን የምንበላው:: አሁን በጎሳ በሃይሞኖት ከፋፍሎ የሌለንን የማናውቀውን ጠብ ተጣሉ የሚል መንግሥት ነው ያጋጠመን::በኛ አካባቢ ከበደ አሊ ተብሎ ሙስሊም፤ሞሃመድ ካሳ ተብሎ ክርስቲያን ይሄው ባጠገቤ አለ፤ አንድ ነን እኮ! ምናለ አደብ ብታስይዙት ይሄን መንግሥት?" ብለው ቁጭ አሉ::

በአብዛኛው ብሶትና ምሬት ነው እንጂ ብዙም ጥያቄ አልተነሳም:: ጠይቁ ስንልም «ነግራችሁን፣ አስረድታችሁን፣ ገብቶን ምን እንጠይቃለን? በቃንኮ! ወስነናል:: የምርጫው ዕለት እንገናኝ» ተባለና አንድ ጠያቂ ተነሱ:: « እንዲያው ለነገሩ ወንድሞቼ! በወርሃ ግንቦት እኛ የምናውቀው ዝንብ እንጂ ንብ አይደለም:: ታዲያ ያሁኒቷ ንብ ከወግ ውጪ ከየት መጣች? » ብለው አዳራሹን ሳቅ በሳቅ አደረጉትና በዚሁ የመጨረሻ ምርቃት ተደርጎ ስብሰባው አለቀ::

እንዳጋጣሚ ወደ 11 ሰአት ላይ ደሴ ብዙ ሰው ገብቶ አደረ::ሰዉ የአክሱም ሃውልትን ሊቀበል ትግራይ ሄዶ የነበረ ሲሆን ወደ የመጣበት ሲመለስ አውቶቡሱ ደሴ አድሮ ነው:: የሚገርመው ነገር፣ በምርጫው ወቅትና ከምርጫም በኋላ ቅንጅትን ዘረኛ የሚሉት



የወያኔ/ኢህአዴግ ካድሬዎች የአክሱምን መምጣት በተመለከተ ማንኛውም ስብሰባም ይሁን ሌላ ጉዳይ ላይ የተቃዋሚ ፓርቲዎችን እንደ ኢትዮጵያዊነታቸው አለመጋበዛቸው ነው:: በዚህም ኢህአዴግ ያረጋገጠው ጉዳይ ቢኖር፣ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ኋላ ሊያስተካክሉ የሞከሩትን «የአክሱም ሃውልት ለወላይታው ምኑ ነው?» ነበር:: እንደመንግሥት ሊያስቡ አእምሯቸው እምቢ አላቸው እንጂ ጥሪውን ልከው ተቃዋሚች ቢቀሩ ለነሱ ፕሮፓጋንዳ ይሆናቸው ነበር::ወያኔ ኢህአዴግ ቅንጅትን ዘረኛ የሚለው እንዲያው በከንቱ መሆኑን በዚች እንኳን ማረጋገጥ ይቻላል::

የቅንጅት አመራር ግን የአክሱም ሐውልት የሕዝብና የሃገር መሆኑን ስለሚያምን ነው ለባለቤቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአክሱም ሐውልት መመለስ የደስታ መግለጫ ያስተላለፈው::

ሕዝባዊው ስብሰባ በየቦታው፤ በመከፋፈልና በኪራይ መኪና እየተደረገ ነው:: ወያኔ/ኢህአዴግ ተቃዋሚዎች ገንዘብም ስለሌላቸው በየምርጫ ጣቢያው አይሄዱም፤ አይሳካለቸውም ብሎ ገምቶ ነበር::የቅንጅትና በቅንጅት በተዋሃዱት ፓርቲ ደጋፊዎች አለን ባይነት ሁሉም አካባቢ ለመድረስ በቁርጠኝነት ተንቀሳቅሷል::

ከስብሰባው በኋላ ምሳ ተበልቶ እረፍት ተደርጐ የደሴንና አካባቢውን የቅንጅት ተመራጮች በማግኘት ከነሱ ጋር ሰፋ ያለ ውይይትና ምክክር ተደረገ:: ለቡና ከታደምንበት ሆቴል በርካታ የከተማው ነዋሪ እየመጣ የሆዱን እያጫወተን አይዟችሁ ድሉ የናንተ ነው እያለን አመሸ::

በልተን የምንጠግብ፣ ጠጥተን የምንረካ ስለማይመስላቸው በገፍ ነበር ግብዣው:: ግብዣ አንቀበልም ማለት የራሱ ችግር ነበረው:: ግብዣ በቃን ያልን እንደሆነ «ምነው ጠላችሁኝ እንዴ?» ነበር የምንባለውና በተቻለን የሁሉንም ስሜት መጠበቅ

ነበረብን::ሲበዛብን ነው ያንን ቦታ ትተን አልጋ ወደያዝንበት ሆቴል ያመራነው::በዚያ ከአልጋ ውጪ መብልም መጠጥም የለም::

## ከደሴ ወደ አዲስ አበባ

በማግስቱ ጠዋት ያሬድ ጥበቡ (ጌታቸው ጀቤሳ) የመኪናው ጉዞ ስላልተመቸው በአይሮፕላን ለመሳፈር ወደ ኮምቦልቻ መሄድ ስለነበረበት እሱን ኮምቦልቻ አድርሰን ወደ አዲስ አበባ ጉዞ ቀጠልን:: እግረ መንገዳችንን መንገድ ላይ ያሉትን የምርጫ ጣቢያዎች ሁኔታ ለማየት እየቆምን ለመሄድ ተወስኖ የመጀመሪያው መቆሚያ ሃርቡ ላይ ሆነ:: እንደደረስን ወደ ምርጫ ቦርዱ ፅ/ቤት ስንሄድ በሕዝቡ ላይ ጫና ተጥሎበታል:: ቅንጅት የሚል ስም እንዳይነሳ ታግዶ ሰዉ ተበሳጭቷል::

ዶር/ ብርሃኑ፣ አቶ በድሩና ሻለቃ አድማሴ ገብተው ለሃላፊው፣ የምርጫ ቦርድ ያወጣው መመሪያ መጣሱን፤ ይህም አግባብ አለመሆኑን አስረድተው ስምምነት ላይ ቢደረስም፣ ሁኔታው እንደሚቀጥል እየገባን ለጊዜውም ቢሆን ውጥረቱ ይረግባል በሚል እምነት ጉዞ ቀጠልን::

ደብረሲና ስንደርስ ሕዝቡ ተቀይሞ አገኘነው:: «ምነው ዘላችሁን ሄዳችሁ? እኛስ የናንተው አይደለንም?» በማለት ቅሬታቸውን አሰሙን::የጊዜ ጥበት መሆኑንና በሌላ መርሀ ግብር እንደምናገኛቸው ቃል ገብተን፣ ለቡናም፣ ለእረፍትም ወደ ቡና ቤት ጎራ አልን:: ጭራሽ ቡና ቤት ስንገባ ወከባው በዛብንና ያዘዝነውን ቶሎ ቶሎ ጠጥተን ጉዟችንን ወደ አዲስ አበባ ቀጠልን:: ትንሿን የደብረሲናን ከተማ መልቀቂያ የመጀመሪያው ዋሻ ስንደርስ መኪናው ድንገት አንድ ፍንዳታ የሚመስል ድምጽ አሰምቶ ቆመ:: ሁላችንም ግር አለንና ወረድን:: ጎማው ደህና ነው፤ታዲያ ምንድን ነው የጮኸው? ሾፌሩ ተመልሶ ወደጋቢናው ገብቶ



ሞተሩን ቢሞክረው ምንም ድምጽ የለም:: ኮፈኑን ከፍቶ ቢያየው ምን እንደነካው ማወቅ አልተቻለም::

ሁላችንም ሾፌሩን ለማገዝ የየአቅማችንን ብናደርግም ያሰብነው የመኪና አገልግሎት መነሳት ጨርሶ የሚሳካ አልሆነም::በግፊ ለመሞከር የመኪናው ፊት ወደ አቀበት ስለነበረ ወደ ቁልቁለት አዙረን ከተማ በማድረስ ሜካኒክ እንፈልግ፣ ካልሆነም የኪራይ መኪና ይዘን አዲስ አበባ ገብተን ማደር አለብን ተባብለን በዚሁ ተስማማንና ወደ ሥራ ገባን:: እኔ ካሜራ ይዤ ስለነበር ሌሎቹ በግፊት ላይ ተሰማሩ::

ምናልባት በግፊት ቢነሳ ተብሎ አቅጣጫውን ወደ ደብረሲና ከተማ ከመለስን በኋላ ቢባል፣ ቢባል አልሆን አለ:: ደግነቱ ቁልቁለት በመሆኑ ሁላችንም ገብተን በዜሮ እየተንከባለለ ከተማ ደረስን:: መካኒክ ቢፈለግ የለም:: ያለው አማራጭ በሌላ የኪራይ መኪና ወደ አዲስ አበባ መሄድ ነው::እንዳናድር ደሞ በማግስቱ ሰኞ የተጠራ ስብሰባ ስለነበር ገብቶ ማደር የግድ ሆነ::

የኪራይ መኪና ተገኘ::ችግሩ ግን ያ መኪና የሚወስደን ደብረ ብርሃን ድረስ ብቻ ነበርና ከዚያ በኋላ ሌላ መኪና መፈለግ፣ ካልተገኘም ደብረብረሃን አድሮ ሌሊት በበራሪ ለስብሰባው መድረስ ነበር ያለን አማራጭ:: ደብረብርሃን ስንደርስ ሌላ መኪና ስንፈልግ ወዲያው አገኘን:: እጥፍ ከፍለን ጉዞ ጀመርን:: በመኪናው ውስጥ አንዱ ተሳፋሪ ጋቢና ተቀምጠዋል እኔ ከኋላቸው ነበርኩ:: ሚስታቸው ልጃቸውን ታቅፈው ከጎናቸው አሉ:: ትንሽ እንደሄድን ዘወር ብለው ጠየቁኝ:: «እንዴት እየሆናችሁ ነው? ስለወታደሩ ምንድን ነው ያሰባችሁት? ደሞ እንደገና ሊበተን ነው?» አሉኝ::

«የቅንጅት አቋም ማፍረስ መበተን ሳይሆን ያለውን አስተካክሎ መቀጠል ነው፤ ለአንዴና ለመጨረሻ ከሃገራችን ቂም በቀል ጠፍቶ ሕዝብ አንድ ሆኖ እንዲኖር ነው ራዕያችን:: ለመበተን ኢህአዴግ መሆን ያስፈልጋል እኛ ደሞ ቅንጅት ነንና

አይበተንም፡፡በመበተን ሥራ አጥ ማብዛት እንጂ ምን ትርፍ ይገኛል?» አልኳቸው፡፡ ትንሽ ግራ ገብቷቸው «እውነትክን ነው» አሉኝ፡፡ የማኒፌስቶው ፅሁፍ ስለነበረኝ ገጹን፤ ገልጬ፤ አሳየኋቸው፡፡ ትንሽ አሰቡና የሚገርም ነው! ለኛ የሚነገረን እኮ



*(የቅንጅት አባላት ይዘዋወሩ የነበረው በኪራይ መኪና ሲሆን የኢህአዴግ አባላት ግን በመንግሥት መኪና፤ነዳጅና ሾፌር ነበር ከግራ፡- መሐመድ፣ ዶ/ር ብርሃኑ፣ ሻለቃ አድማሱና ገንጠል ብለው ያሉት አቶ በድሩ ሻለቃ አድማሱና በድሩ የመኪናው ችግር እንደማይመለከታቸው ዓይነት ለዶ/ር ብርሃኑና ለሞሐመድ የመግፋቱን ጣጣ ትተውታል፡፡ፊትፍታችሁ አኳኋችሁ አጉርሱን አይነት መሆኑ ነው፡፡ገንጠል ብሎ መቆሙ ካሁኑ ተግባራቸው ጋር ይገኛኝ ይሆን?)*

ሊበትኗችሁ ነው በሚል ነው» አሉ፡፡

«አይደረግም» አልኳቸውና ጨዋታችን በዚሁ ቆመ፡፡ ደብረብርሃን ስንደርስና ስንሰነባበት ወደ ጎን ወስደው መታወቂያቸውን አሳዩኝ፡፡ የጦሩ አባልና ሻለቃ



ናቸው፡፡ «አደራ ይህን እውነት ለሁሉም ይንገሩልን!» አልኳቸው፡፡ «በኔ ይሁንብህ» ስላሉኝ ያንን የማኒፌስቶ ኮፒ ሰጥቻቸው ተለያየን፡፡ የሚገርመው ነገር እኚህን ሻለቃ ለሁለተኛ ጊዜ በሚያዝያ 30ው ሰልፍ ላይ ሳገኛ ቸውና ሰላም ሲሉኝ አላወቅኋቸውም ነበር፡፡ መነጽር አድርገዋል "ሰላም" ብዬ ላልፍ ስል «አጠፋሀኝ?» አሉኝ በችኮላ «ዘነጋሁ» አልኳቸው፡፡ ሳቅ ብለው "ከደብረሲና ደብረብርሃን ስንመጣ ጋቢና ቁጭ ብዬ....." ሲሉኝ «ይቅርታ ሻ....» ብዬ ተውኩት፡፡ ተግባብተን «መልዕክቱን አድርሻለሁ፡፡ በርቱ፣ አብረን ነን» ብለውኝ ተለያየን፡፡

ደብረ ብርሀን እንደደረስን እኔ ከሻለቃው ጋር እያለሁ ወደ አዲስ አበባ የሚወስደን መኪና ተገኘ፡፡ዋጋ ሲጠየቅ ትንሽ ከመደበኛው ጫን ያለ ቢጠይቅም፣ ምርጫ ስለሌን ተስማማን፡፡ አሁን አብላጫ ተሳፋሪዎች እኛ ስለሆንን የዕድሜ ይሁን የጤንነት ጉዳይ የፊት ወንበር ቅድሚያው ተሰጠኝ፡፡ በጭራሽ አልተግደረደርኩም፡፡ ከደብረሲና ስንመጣ የመቀመጫ ጉዳት ደርሶብኝ ስለነበር በዚህ ተካካስ፡፡

መኪናውን ስናየው አዲስ ይመስላል፤መንገድ ገብቶ ዳገት አካባቢ ስንደርስ አዲስ ሆኖ ያገኘነው ቀለሙ ብቻ ነው፡፡እንደምንም ተጎትተን ከምሽቱ 5 ሰአት ገደማ ወደ አዲስ አበባ ስንቃረብ በየቤታችን የሚያደርሰን ወዳጅ በስልክ ፈለግንና ወደ አቶ የሸዋሉል ደወልን፡፡ ከነንደኛው ሁለት መኪና ይዘው መጡ፡፡ ከዚያ የተረፉት ቀደም ብለው በታክሲ ወደየቤታቸው ሄደው ስለነበር ችግሩ አስቀድሞ ተፈታና ወደ የቤታችን ገባን፡፡ለሰኞው ስብሰባም ለቤታችንም በቃን፡፡

የደብረ ብረሃኑና የደሴው ስብሰባ በሬዲዮና ቴሌቪዥን ይቀርባል የሚል እምነት ቢኖረንም የደብረ ብረሃኑ በሬዲዮ ሲነገር፣ የደሴው ዜና እምጥ ይግባ ስምጥ አልታወቀም፤ ጭጭ ጭጭ ሆነ፡፡በማግስቱ ሰኞ አቤት አልን፡፡ ቴሌቪዥን ፊልሙ ስላልደረሰን ነው አሉን፡፡ ሬዲዮ የደሴውን ዜናው እየጠበቅን ነው አሉን፡፡ ማታውኑ ፊልሙ ሳይታይ የደሴው ዜና ቀረበ፡፡ከዚህ

ነው የመንግሥት ሚዲያው ትንሽ ትንሽ ጫና የጀመረው::

## ወደ ቅንጅት ጉዞ




የቀስተደመና ሥራ አስፈፃሚዎች በስብሰባ ተጠምደዋል:: የስብሰባው ሪፖርት በሊቀ መንበራችን አማካይነት ይቀርብልናል:: ሁኔታው በእጅጉ የሚያበረታታ ነበር:: እስከዛሬ በሃገራችን ታሪክ ተደርጎ የማያውቅ ዓይነት ይዘት ያለው ጉዳይ ነበር:: በሃገር ውስጥ ቢሯቸውን ከፍተው፣ አባላት መልምለው የሚንቀሳቀሱ፣ ለሰላማዊ የፖለቲካ ትግል የተዘጋጁ አራት የፖለቲካ ፓርቲዎች በአንድ ግንባር ተሰልፈው ለመሥራት ድርድር የሚደረግበት ነው::ለብዙ ጊዜ ተሞክሮ እሩብ መንገድ እንኳን ሳይራመድ መቋጫው መበተን ይሆን የነበረውን ጉዳይ፣ ፈር ለማስያዝ የሚደረግ ስብሰባ ነው::



ከእነዚህ ፓርቲዎች መሃል በጣም ለጋ ዕድሜ ያለው ቀስተደመና ቢሆንም፣ በአመራር ላይ ያሉት ሁሉ በተለያየ መልኩ ከፍተኛ ልምድ ያላቸውና ስር ነቀል ለውጥ፣ዴሞክራሲያዊ ስርአት፣ነፃነት ለማምጣት የተዘጋጁ ናቸው:: በቀስተደመና ያለው አንድ አዲስ አካሄድ በጣም ግልጽና ዴሞክራሲያዊ መሆኑ ነው:: ለማንኛውም ጉዳይ ዴሞክራሲያዊ ውይይት ዋነኛው መመሪያ ሆኖ ተቀምጧል::

የቀስተደመና ፓርቲ አንደኛ መደበኛ ጉባኤ በተካሄደበት ወቅት የፓርቲያችን ሊቀመንበር ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ያቀረቡት ፅሁፍ ይህንን በግልጥ ያሳያልና አቀርበዋለሁ::

## ዶ/ር ብርሃኑ ያቀረቡት የመቀናጀት ቅድመ ዘገባ

'ቀስተ ደመና ኢትዮጵያ' በጣም አጭር፣ግን በጣም በሁኔታዎች ያሸበረቀና የጣፈጠ ታሪክ ያለው ለጋ ድርጅት ነው:: በዚህ በመጀመሪያው ጉባኤው ከሚወስናቸው ጉዳዮች አንዱ፣ የቅንጅቱን ውህደት መሆኑና ይህም የሚያስከተለውን የቀስተ ደመናን መክሰም ከግምት ውስጥ ስናስገባ ሊሰማን የሚገባው ስሜት በእድሜው ማጠር ማዘን ሳይሆን በአጭር እድሜው ያደረጋቸው እንቅስቃሴዎችና ያስመዘገባቸው ውጤቶች «ለካ በአጭር እድሜ ብዙ ነገር መስራት ይቻላል» ብለን የምንኮራበት ይሆናል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ::

የኢትዮጵያን የፖለቲካ ሁኔታና በፖለቲካውም መዘበራረቅ ምክንያት አገሪቱ ሊገጥማት የሚችሉ ችግሮችን በሚመለከት በቅርብ የምንተዋወቅ አንድ ስምንት የምንሆን ሰዎች ተከታታይ የሆኑና አንዳንድ ጊዜ በየሳምንቱ፣ አልመች ሲልም በወር አካባቢ፣ሲመች በአንድ ላይ ለምሳ እየተገናኘን ስንወያይ፣ አለበለዚያም በተናጠል ጥቂት ሆነን ስንገናኝ

ምናልባት አንድ ሁለት አመት አጥፍተናል፡፡ እነኚህ ውይይቶች በመሰረቱ የአገሪቱን የፖለቲካ ሁኔታ በመገምገም ላይ ያተኮሩ የሀሳብ መለዋወጦች ሆነው ለረጅም ጊዜ ቆይተዋል፡፡ ስብስቡም ወደ ተቀናጀ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ያመራል ተብሎ አልተጀመረም፡፡ በነኚህ ውይይቶች መቋጫ ኢህአዴግ የአገሪቱን ፖለቲካ እያበላሸው እንደሆነ፣በዚህ ከቀጠለ፤አገሪቱ ምናልባትም በቀላሉ ልትወጣው ወደማትችለው ቀውስ የምትገባ መሆኑን፣ በተለይ በአዋሳ፣ በጋምቤላ፣ በቴፒ... ወዘተ ያየናቸውና እያደር እየባሱ የሄዱ ግጭቶች አካሄዳቸው አጉል እንደሆነና ሁኔታዎች በዚህ ከቀጠሉና ይህንን የሚያበርድ የፖለቲካ ሁኔታ ካልተመቻቸ፤የአገሪቱ አንድነትና የህዝቡም ሰላማዊ ኑሮ ክፉኛ ሊናጋ እንደሚችል በትንተና ደረጃ ስምምነት ነበረን፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ለዚህ አጠቃላይ የፖለቲካ ችግር ምክንያቱ ኢህአዴግ የሙጢኝ ብሎ የያዘው ዘርን ከዜግነት የሚያስቀድም ፖለቲካ፣ ወይም በአገሪቱ ያሉትን ባህለዊ ስብስቦች (Cultural communities) በጠንካራ የዜግነት እኩልነት ሀረግ ከማስተሳሰርና ባህላዊ ልዩነቶችን እንደ አገራዊ ውበት ከመመልከት ይልቅ ልዩነቶችን ለመከፋፈያና ለጊዜያዊ ፖለቲካ ጥቅም ማግኚያ መሳሪያ አድርጎ የመጠቀም ጠባብና አደገኛ አካሄድ መሆኑን ተቀበልን፡፡ ከዚህ ቀጥሎ አሁንም በመርህና በአስተሳሰብ ደረጃ መፍትሄውን በሚመለከት በጥቅሉ ባደረግናቸው ውይይቶች በአገራችን የፖለቲካ ደህንነትና እንደአገር ወደፊት ሊወስደን የሚችለው በዜግነት እኩልነት ላይ የተመሰረተ፣ የባህላዊ ስብስቦችና የጋራ መብቶች ሙሉ ለሙሉ የሚያከብር ብቻ ሳይሆን እንዲበለጽጉ የሚንከባከብ፣ የይስሙላ ሳይሆን እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት መመስረት እና በዚህም ዙሪያ የአገሪቱን ልሂቃን ብሎም አጠቃላይ ህዝቡን አሳምኖ ማሰባሰብ (consensus) መፍጠር ወሳኝ ጉዳይ መሆኑን አመንን፡፡

ብዙ ጊዜ ፈጅተን የችግሩን አይነቶች፣ ምንጮቹንና መፍትሄ ይሆናሉ ብለን ባልናቸው ሀሳቦች ላይ በአብዛኛው ከተስማማን በኋላ ጉዳዩ የግድ ከወሬ ደረጃ አልፎ ተግባራዊ እርምጃ ወደ መውሰድና በግለሰብ



ደረጃ የእያንዳንዳችን ሚና ምን መሆን አለበት ወደሚለው ጉዳይ ውይይት ሲሸጋገር ለአገር በማሰብ ከተነሳ ግን ሌላ ጭብጥ ተግባር ካልነበረው ምሁራዊ ውይይት ምናልባትም ተግባር ውስጥ ሊገባ የሚችል እንቅስቃሴ ሊሆን እንደሚችል ፍንጮች መታየት ሲጀምሩ ለዚህ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ዝግጁ ያልነበሩት ከውይይቶቹ ቀስ እያሉ መቅረት ይጀምራሉ፡፡ በውይይቱ ዙሪያ የተሰባሰብነው ሰዎች ይህንን ጥያቄ ያነሳነው በዙሪያ ጥምጥም ሳይሆን በቀጥታ ነበር፡፡ ይህ ነገር በቀጥታ ካሉት ድርጅቶች ውስጥ በአንዱ ገብቶ የፖለቲካ እንቅስቃሴውን ወደመቀላቀል ወይንም በራሳችን የፖለቲካ ድርጅት ወደመፍጠር ቢሸጋገር የዚህ አካል ለመሆን የምንፈልግ ምን ያህል ነን? ብለን እርስ በእርሳችን ተጠያየቅን፡፡ ከአሁን በኋላ የሚደረጉ ውይይቶች ተግባር ነክ እንደሚሆኑና በዚህ ተግባር ውስጥ መሳተፍ የሚፈልጉ ሰዎች ብቻ ቀጣዩን ውይይት እንዲያደርጉ ተስማማን፡፡ በመጨረሻ በተግባር ላይ የተመሰረተውን ውይይት ጠለቅ ባለ መልኩና በስነስርዓት ውይይቱ የተጀመረው አንዲት ሴትና አራት ወንዶችን ባቀፈ፣ በሙያቸውም አንድ ፕሮፌሰርና አራት ዶክተሮች በጠቅላላው የአምስት ሰዎች ቡድን ሲሆን፣ ይህ ቡድን ነው በእርግጥም የቀስተ ደመና ጠንሳሽ እርሾ ሊባል የሚችለው፡፡

አምስቱ ጀማሪዎች በቀጣይ ያደረጉት ውይይቶች በሶስት አጠቃላይ ጉዳዮች ላይ ነበር ማለት ይቻላል፡፡

እነኚህም፡-

1. አሉ ከሚባሉ አገራዊ ድርጅቶች ውስጥ መርጦ አንዱን መቀላቀል ይሻላል ወይንስ በራሳችን ድርጅት መፍጠር?
2. በራሳችን ድርጅት ከፈጠርን የድርጅታችን መሠረታዊ ርዕዮተ ዐለም ምን ይሆናል? በአጠቃላይ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ የሚኖረን አቋምስ?
3. እኛ የፈጠርነው ድርጅት እስካሁን ካሉት ላይ የሚጨምረው ምንድን ነው?አሁን ካሉት

ድርጅቶችስ ጋር የሚኖረን ግንኙነት ምን ይሆናል ?የሚሉት ጉዳዩች ነበሩ::

በእነኝህ ጉዳዩች ላይ ረዘም ያሉና አንዳንድ ጊዜ ግማሽ ምሽቶችን የሚወስዱ ጥልቅ ውይይቶች አድርገናል:: የውይይታችንን አጠቃላይ ጠገግ የሚወስነው መጪውን የግንቦት 97 ምርጫ በሚመለከት የነበረን አጠቃላይ ስምምነት ነበር:: ይህም ግንቦት 97 ምርጫ ከዚህ በፊት የነበሩት አይነት ምርጫዎች ሊሆን አይችልም:: ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች በሰውና በንቃት ተሳትፈው አሁን ያለውን የኢህአዴግ ፍፁም የፖለቲካ ሞኖፓል ሙሉ ለሙሉ እንኳን መስበር ባይቻል በጣም በጣም ሊያዳክሙት:: ይገባል ይህ እንዲሆን ደግሞ በተቃዋሚው ጎራ ያሉትንና በዋና ዋና መሰረታዊ መስመሮች ላይ ቢያንስ በፕሮግራም ደረጃ ብዙ ልዩነት የሌላቸው ኃይሎች በቅንጅት የሚሰሩበት ሁኔታ መፈጠር አለበት:: ለዚህም ማድረግ ከሚገባን ነገሮች አንዱ የእነኚህን የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች ፕሮግራሞች በዝርዝር ማጥናት፣ በፕሮግራም ደረጃ ብዙ ተቀራራቢ የሆኑት እስከአሁን አብሮ ለመስራት ያልቻሉበትን ምክንያት ማጥናትና ማወቅ ያስፈልገናል በሚል ጊዜያችንን ወስደን እነኚህን ፕሮግራሞችና በተግባር ደግሞ በጋራ አብሮ ለመስራት እንቅፋት የሆኑትን ምክንያቶች በዝርዝር ተመልክተናል:: እነኚህን ጉዳዮች በሚመለከት የደረስንበት ድምዳሜ በአጭሩ:-

1. በእርግጥ ብዙዎቹ፣ በተለይ ሕብረ ብሔራዊ የሆኑት ድርጅቶች ለመዋሀድ ከደረሱ በኋላ በፕሮግራም ላይ ባልተመሰረቱ ልዩነቶች ውህደታቸውን ማሳካት እንዳልቻሉ::
2. ከዚህ በፊት ተቃዋሚች በጋራ ለመስራት ችግር የሆነባቸው በአብዛኛው በውስጥ አሰራራቸው፣ በአመራሮቻቸው አካባቢ ባሉ የግለሰብ ሰብዕና ልዩነቶች፣ በአገሪቱ የወደፊት የፖለቲካ ሂደትና የትግል አካሄድ ላይ ግልፅነት ማጣት፣ እያንዳንዳቸው ድርጅቶች ከምስረታ ታሪካቸው ጋር የተያያዙ የውስጥ ድርጅት ባህሎችና ከዚህም የተነሳ



አዳዲስ አሰራሮችንና ለውጦችን ለመቀበል ክፍት ፈቃደኝነት አለመኖር ...ወዘተ መሆናቸውን ነው::

ይህም ማለት በእነኚህ ከመርህ መለስ ያሉ ልዩነቶች ላይ ስልታዊ አካሄድ ከተካሄደ ብዙዎቹን ድርጅቶች ማቀራረብና በተለይ ለምርጫው በጋራ እንዲሰሩ ማድረግ ይቻላል የሚል ግንዛቤ ላይ ነው የተደረሰው:: እዚህ ላይ በተለይ ጥንቃቄ ሊወሰድበት የሚገባ ተብሎ የታመነበት በሕብረ ብሔራዊና በብሔር ላይ በተመሰረቱ ድርጅቶች መሐከል ከአጠቃላይ የዴሞክራሲ ሥርዓት ምስረታ አንፃር ተባብሮ መስራት አስፈላጊነቱ ላይ ክርክር ባይኖርም እንደነዚህ አይነት ድርጅቶችን መፍጠር ከተቻለ እነኚህን ሁለቱን አለመቀላቀል የተሻለ አማራጭ እንደሚሆን፣ በእኛ በኩል መገፋት ያለበት አቋም ነው:: በቅንጅት ደረጃ ለሁሉም ኢትዮጵያዊ ክፍት የሆኑ ድርጅቶች ቢቀናጁ፣ በብሔር ላይ የተመሰረቱ ድርጅቶች ጋር ግን በስልት ደረጃ አብሮ መስራት ቢሞከር ይሻላል የሚለው ነው:: በሌላ በኩል በድርጅቶች ደረጃ አብሮ ለመስራት እስካአሁን ችግር ከፈጠሩት ጉዳዮች አንዱ የፖለቲካው ሂደት በምርጫው ላይ ያተኮረ እንደመሆኑ፣ የሚፈጠሩ የድርጅት ቅንጅቶች በአገር ውስጥ የሚንቀሳቀሱና ሕጋዊ እውቅና ያላቸው ብቻ መሆን አለባቸው የሚለው ሁለተኛው መርህ ነው:: ከአገር ውጭ ባሉና በሕጋዊ መንገድ በተናጠል ወይንም ተቀናጅተው እንዲታገሉ ሁኔታው መመቻቸት አለበት:: ለዚህ ምርጫ የሚቀናጁ ድርጅቶች ባገር ውስጥ ያሉና በምርጫው የሚሳተፉ ቢሆኑ የሚመረጥ ነው::

እንግዲህ በእነኚህ መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ አቋም ከተወሰደ በኋላ ከላይ ከ1-3 በተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ ነው ውይይቱ የቀጠለው:፡ በዚህም መሰረት በመጀመሪያ ተ.ቁ በተቀመጠው ማለትም ያሉትን መቀላቀል ከአንዱ ጋር በግልጽ መወገንን ስሚያስከትል፣ በዚህም ምክንያት ድርጅቶችን ለማቀራረብ የሚደረገውን ሙከራ ሊያደናቅፍ እንደሚችል፡ከዚያም በላይ ግን የራስን ድርጅት መመስረት ቢያንስ እኛ የምናምንባቸውን መሰረታዊ እምነቶቻችንን በሚቀናጀው

ድርጅት መፍጠር ትክክለኛ መሆኑን፤ነገር ግን ዋና እንቅስቃሴያችን የድርጅቱን መመስረት እውን ማድረግ ተቀዳሚ ተግባራችን መሆን እንዳለበት አምነንበታል።

የራሳችንን ድርጅት ለመፍጠር ከተስማማን በኋላ የሚቀጥለው ተግባር የድርጅቱን መለስተኛ ፕሮግራም ማዘጋጀት፣ ሌሎች ተመሳሳይ አመለካከት ያላቸውን ሰዎች መቅረብና እንዲቀላቀሉን መጠየቅ ቀጣይ እርምጃዎቻችን ነበሩ። በዚህም መሰረት ቀደም ብለን ካደረግናቸው ዝርዝር ውይይቶች በመነሳት አጠቃላይ ርዕዮተ ዓለማችን ማህበራዊ ዴሞክራሲ (Social Democracy) እንደሚሆን፣ ይህንን አጠቃላይ ርዕዮተ ዓለም ግን በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ በመተርጎምና ከዚህ ጋር በተጣጣመ መልኩ በተቻለ መጠን በአጭሩ፤አሁን ያለውን የቀስተ ደመና ፕሮግራም መጻፍ፣ ይህም ሲሆን በተቻለ መጠን በጣም በቀላሉና ለሁሉም በሚገባ መልኩ ግን ደግሞ በቋንቋ አጠቃቀም ደረጃ የተምታታ ትርጓሜ እንዳይሰጥ በከፍተኛ ጥንቃቄ መሥራት፤ አንዳንዴም ብዙዎቻችን ካለን የአካዳሚ ልምድ የተነሳ ጸጉር ስንጠቃ እስከሚመስል ድረስ ተፋጭተን አሁን የቀስተ ደመና ፕሮግራምና መተዳደሪያ ደንብ የሆነውን ሰነድ አዘጋጀን።

ከዚያ በኋላ የነበረው ከባዱ ተግባራዊ ስራ ስለነበር በአንድ በኩል ከኛ በተጨማሪ ሰዎችን ማፈላለግ በእውነቱ እኛም የማናውቅበት አታካች ሥራ ነበር። በሌላ በኩል ግን የድርጅቱን መሰረት ከሌሎች ድርጅቶች ጋር አብሮ ከመስራት ጋር አያይዘነው ስለነበር እኛ ባሰብነው መሠረት ቅንጅት ሊፈጥሩ ይችላሉ ያልናቸውን ድርጅቶች አመራሮች አንድ በአንድ ማነጋገርና እነሱን ማሳመን ነበረብን። በእውነት ለመናገር ይህንን ስራ ስንጀምር በጣም የፈራነው ግን በጣም ቀላል ሆኖ ያገኘነው ሥራ ይህ ነበር። በመጀመሪያ ጊዜውም ሊሆን ይችላል ያናገርናቸው ድርጅቶች በሀሳቡ ላይ ምንም ማንገራገር አላሳዩም። በአንድ በኩል የእኛን ወደ ፖለቲካው መድረክ መምጣት ብዙዎች በደስታ ነበር የተቀበሉት።



ይህ ሁሉ ሲሆን ፕሮግራሙን በመቅረጽ የጠፋው ጊዜና የነበረው ዝርዝር ክርክር እንዲህ ቀላል አልነበረም። Social Democracy የሚለውን የተስማማንበትን የእንግሊዝኛ ቃል በአማርኛ ለመተርጎም በተለይም ማህበረሰባዊ ፍትህ ወይንስ ማሕበራዊ ፍትህ በሚል ያጠፋነው ጊዜ እንኳን በፍፁም ቀላል አልነበረም።

የመኢአድ ልምድና ቆራጥነት እስከ ወረዳና ምክትል ወረዳ በየመንደሩ በከተማም በክልልም ዘልቆ መግባቱ፤የኢዴአፓ መድህን ረጂም ልምድ ፤የኢዴሊ የወጣቶች ሃይልና ጥንካሬ በአንድነት ተቀናጅቶ ታላቅ ፖለቲካዊ ለውጥ በማምጣት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ እንደመዥገር ተጣብቆ መከራውን ከሚያበላው ችጋር እንደሚያላቅቀው ምንም ጥርጥር የሌለው ጉዳይ ነው።

ያም ሆኖ ከታሰበበት ግብ ለመድረስ ረጂም ውጣ ውረድ፣ ብዙ መሰናክል፣ ቁጥር የበዛበት እሰጥ አገባ እንደሚኖር ከጅምሩ ይታወቅ ስለነበር፤አንዱ ሲግል አንዱ ሲያበርድ፣ ደሞ ሲጠም ማቃናት፣ ደህና መንገድ በማስያዝ በኩል እድሜ ከልምድ የሰጣቸውና በለጋ ዕድሜ ወደ ትግል ገብተው የበሰሉት ተሰብሳቢዎች፣ እንደሚሆን እንደሚሆን እያደረጉት ወደ መግባባቱ ለጥቆ ወደመተማመኑ አልፎም ወደ ስምምነት እየተደረሰ መጣ።

የስብሰባው ዓላማ በአንድ ተሰባስቦ ለመቀናጀትና የሃሳብ፣ የተግባር፣ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የአባላት ጉልበት ለማግኘት ነው።«ቅንጅትን ለመፍጠር»። በተናጠል ለገዢው ፓርቲ ኢላማነት ከመጋለጥ በቅንጅት ተጠናክሮ መፈርጠም ጠቃሚነቱ ታምኖበት ተግባራዊ ለማድረግ ነው።ይህ ደግሞ በአንድ ጀምበር ተጀምሮ የሚዘጋ ሂደት ሳይሆን ከብዙ አቅጣጫ ክርክር የሚያስነሳ ጉዳይ ነው።ስልጣንን ያሳጣል፤ደረጃን ዝቅ ያደርጋል፤ስነስርአት የተጠናከረ ይሆናል፤ተጠያቂነት ያለበት ቢሆንም የበለጠ ይጠነክራል፤ግለሰቦች እኔ የሚሉት ይጠፋል፤የያንዳንዱ ፓርቲ አመራር ቦታውን ይለቃል፤በተናጠል ይቀርና በድምር ይሆናል።ታዲያ ይህ

ዕድገትና ጥንካሬ ቢሆንም ከግለሰቦች አመለካከት የተነሳ ችግር አለው::ግን በጥቅሙ ለሃገርና ለወገን ተብሎ ስለሆነ ግልን በመተው በተናጠል ወደ ቅንጅት በመለወጥ፤ሁሉንም ለሃገርና ለሕዝብ በሚል ቅድሚያውን በማድረግ ሁሉም ለቅንጅት መፈጠር ቆሙ:: የሚል ነበር ሪፖርቱ::

ስለዚህ ሁኔታና እንቅስቃሴ የሰሙ ሁሉ ገሚሱ "ያድርገው" ሲል፣ ሌላው "አይይ የማይሆን ነገር?" ይላል ከፊሉ ደሞ "እስቲ እስኪጣሉ ይቀጥሉ" ሲል፣ "የት ሊደርሱም" ተብሏል:: ይህ ጉዳይ በወያኔ/ኢህአዴግም አካባቢ ሲሰማ ተዋቸው፣ እባካችሁ! ለዚህ መች ታደሉና፤ዕድሜ የሌለው ቅንጅት ነው፤ ከኛ ጋር ካላቸው ልዩነት ይበልጥ የርስ በርሳቸው አለመግባባት ይበታትናቸዋልና ከቁምነገር አታስገቡት» ነበር የተባለው:: ለዚህም የተሰጠው የዕድሜ ገደብ ቢበዛ ስድስት ወራት ነበር:: እንዲያውም በሙጫ የተጣበቀ ቅንጅት ነው ተብሎም ለመዘባበቻነት ውሎ ነበር፤ሳይሆን ቀረ እንጂ::

የተወሰነለት የስድስት ወር ጊዜም አለፈ፤ የቅንጅቱ መሰረትም ሙጫ መሆኑ ቀረና ድርጅቶቹን በይበልጥ በማጠናከር የሕዝቡ እየሆነ መጣ::መንገዶች ሁሉ ወደ ቅንጅት ቢሮ፤ወሬው ሁሉ ቅንጅት መሆን ጀመረ::

## ገዢው ፓርቲና የምርጫ ሥልቱ ምላሽ

ኢህአዴግ በምንም መልኩ ይህን ምርጫ እሸነፋለሁ የሚል ሃሳብም ግምትም አልነበረውም::ይህ ማንአለብኝነት የተፈጠረው ደሞ የሕዝብ ፍቅር አለኝ ብሎ ከማመን የመነጨ ሳይሆን፣ ገዢው ፓርቲ ለምርጫው በማለት ያለ የሌለውን ገንዘብ አንጠፍጥፎ ባሰራው ካናቴራና በረጨው ገንዘብ በካድሬዎቹ ቅስቀሳ በየቀበሌ ባሉት አባሎቹ በመተማመን ነበር:: በዚህ



መሰል የምርጫ ወቅት አስቀድሞ ሊታይ የሚገባው ጉዳይ ግን ተዘንግቷል ብዬ አስባለሁ::

ምርጫን ለማሸነፍ በቅድሚያ የሕዝብን ልብ ማሸነፍ ያስፈልጋል::የሕዝብን ልብ ለማሸነፍ ደግሞ ታማኝ ሆኖ መገኘትን ይጠይቃል::ለሕዝብ ታማኝ ለመሆን ደሞ ለሃገር ተቆርቋሪነትን የሕዝብ ወገናዊነትን ማረጋገጥ ይጠይቃል::እርግጥ ቅንጅትም ይህን ሁሉ የሚያሟላ መሆኑ ገና ያልተፈተነበት ጉዳይ ነው:: ወያኔ/ኢህአዴግ ደሞ ባለፉት 14 ዓመታት የግዛት ዘመኑ በነዚህ ነጥቦች ላይ ከሕዝብ ጋር አልተግባባም::ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች ይህን ከግንዛቤ በማስገባት ነበር ወደ ቅስቀሳው መግባት ያለባቸው::

ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች ዓላማቸውን ለማሳወቅ እንቅስቃሴ ጀመሩ::የቅስቀሳው ሂደት ልዩነት ነበረው::የገዢው መንግሥት ቅስቀሳውን የሚያካሂደው በመንግስት የሥራ ሰአት ሰራተኛውን በልዩ ልዩ ዘዴ በመሰብሰብ አጀንዳው ለየት ባለ መልኩ ተቀርጾ ሥራን በተመለከተ ይጀመርና አንደኛው አጀንዳ በዚህ መልኩ ተጠናቆ፣ ድንገት ወደ ምርጫ በመግባት፣ "ኢህአዴግን መምረጥ ማለት የሥራ ማረጋገጫ የደምወዝ እድገት የስራ እጡ ወደ ስራ መግባት እንደሆነ ተደርጎ፤ ሠራተኛው ምንም ለመናገር እድል ሳያገኝ የስብሰባው መሪዎችና ካድሬዎቻቸው ብቻ በሚሰጡት ሃሳብ ላይ ተከናውኖ ኢህአዴግን ለመምረጣችሁ መተማመኛ ማሉልን፤ ፈርሙልን፤" በሚል ሰራተኛው ሕዝብ የቁም ስቅሉን የሚያይበት ነበር::ይህ ሁኔታ ደሞ ለቅንጅት ወዲያው ያውም በአብዛኛው ጊዜ ስብሰባው ሳይበተን ስለሚደርስ ለቅስቀሳችን ጥሩ መሳሪያ ሆኗል:: ጥንቃቄም እንድናደርግና ለተዘረጋው ዕቅድ ማፍረሻ እንድናዘጋጅ፣ አልፎም ለሕብረተሰቡ በስፋት በማሳወቅ ከዚህ ስህተትና አደጋ እንዲጠነቀቅ ምቹ ሆኗል::

በሌላ ጎኑ ደሞ በቅድሚያ ምልክት የተደረገበት የንቦችን መምረጫ በማዘጋጀት "ይህን ካርድ ይዛችሁ በመግባት፣ ከምርጫ ጣቢያ የሚሰጣችሁን በመተው፣

ይህን በኮሮጆው አስገብታችሁ የቀበሌውን መልሳችሁ ስታመጡልን ከ200-500 ብር ይከፈላችኋል" ተብለውም የምርጫ ካርድ የተሰጣቸው ነበሩ:: ለዚህም መራጩ ሕዝብ የወሰደው አቋም ወደ ምርጫ ጣቢያ በሚሄድበት ወቅት በር ላይ ያለው ጠባቂ የግድ እንዲፈትሸውና የተሰጠው የምርጫ ካርድ እንዲታይና እንዲወሰድ ማድረግ ነበርና በዚህም ኢህአዴግን ቀጥተው ቅንጅትን መርጠው እንደወጡ ፍተሻ ላይ ተያዘብን ብለው ለሰጣቸው አካል ያመለከቱ ዘዴኞች ነበሩ::

የገዢው ፓርቲ ወጣቱን ለመያዝና እንዲመርጠው ለማድረግ ከተጠቀመበት ዘዴ አንዱ፤በማህበር ያደራጃቸውን ወጣቶች በመሰብሰብ "ኢህአዴግን ካልመረጣችሁ ድርጅታችሁ ይፈርሳል እናንተም አሰብን ለማስመለስ በሚደረግ አላስፈላጊ ጦርነት ውስጥ ትገባላችሁ፤" የሚል ነበር:: ይህን የማደናገርያ ወጣቱ በዘዴ አከሸፈው::

ይህ አካሄድ መታቀዱና በአንዳንድ ኣካባቢ ተግባራዊ የመደረጉ ማስረጃ እንደደረሰን ቅንጅት የወጣቱን ድርጅት የሚያፈርስ ሳይሆን በበለጠ ተጠናክሮ የሚንቀሳቀስበትን መንገድ የሚያመቻች መሆኑን፤ወደ ጦርነትም እንደማይዘምትና ቅንጅት እንቅስቃሴው ሁሉ በሰላማዊ መንገድ ላይ እንደተመሰረተ፤ ወጣቱ በሁሉም መንግሥታት ዘመን የሚታሰረው የሚሰቃየው የሕብረተሰብ አካል ሆኖ መኖሩንና ቅንጅት ግን መብቱን ጠብቆ እድገቱን እያስተካከለ አምራች ዜጋነቱን በማረጋገጥ ለነገ ሃገር ተረካቢነት ያዘጋጀዋል እንጂ እንደሚባለው አለመሆኑን በፕሮግራሙ አስተላለፈ::

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ለመያዝ የተጣለው ዘዴ ደግሞ ከያንዳንዱ ትምህርት ቤት 3 አባላት የሚገኙበት ተወካይ በተማሪዎች እንዲመረጥ፤በምርጫውም ወቅት የአዲስ አበባ ወጣቶች ማሕበር አባላት እንዲሆኑ በማድረግ ጠቅላይ ሚኒስትር ተማሪዎችን በትምህርት ሥርአቱ ላይ ለማነጋገር እንደሚፈልጉ ተነግሮ ስብሰባው ላይ እንዲገኙ ተባለ:: በተጨማሪም የኢህአዴግ አባላትና ታማኝ መምህራን



ከተለያዩ ቀበሌዎች የወጣት ማሕበር አባሎችን ተሳታፊ በማድረግ ጠቅላይ ሚኒስትር ለጥቂት ጊዜ ስለትምህርት ፖሊሲው መሻሻል እንዲናገሩና ወዲያው በተቀየሰው ዘዴ ስለኢህአዴግ እንዲያነሱና ወጣቱ ከኢህአዴግ ጎን እንዲቆም በማግባባት ድጋፋቸውን ማግኘት ነበር እቅዱ:: በየትምሕርት ቤቱ የተወካዮች ምርጫ ተከናውኖ በፕሮግራሙ መሰረት ሁሉም ወደ ስብሰባው ቦታ ሄዱ:: ሰአቱ ሲደርስ ጠቅላይ ሚኒስትር ወደ አዳራሹ እንደገቡ ሰላምታቸው «እናንተ የኢህአዴግ ደጋፊ ወጣት ኢትዮጵያውያን፣ እንኳን ደህና መጣችሁ!» ነበርና ያልተጠበቀ ሰላምታዊ ማግባቢያው ብዙውን ወጣት አሰደነገጠም፣ አስገረመም::ማታ ይሄው ትርኢት በመገናኛ ብዙሃን ሲቀርብ «ወጣቱ በጠየቀው መሰረት ጠቅላይ ሚኒስትር በተገኙበት ውይይት አድርጎ ለኢህአዴግ ያለውን ድጋፍ አረጋገጠ» ተባለ::

እያንዳንዱ ተማሪ ወደ ስብሰባው አዳራሽ እንደገባ የተደረገለት ስጦታ የንብ ካናቴራ ነበር::አባላትና ታማኝ ወጣቶች ወዲያው ሲለብሱ አባል ያልሆኑም ጥቁር መዝገብ ላይ ገብተው እንዳይታፈኑ በመፍራት ለበሱ::ምን ያህል እውነት እንደሆነ ባላረጋግጥም ወጣቶቹ ከወጡ በኋላ የገቡት የጽዳት ሠራተኞች ለልጆቻቸው የሚሆን ያውም ለረጂም ጊዜ የሚበቃ ካናቴራ ከየወንበሩ ስር አግኝተዋል ይባላል::በዚህ ስብሰባ ላይ የነበረውና ገና ያልወሰነው መራጭ ወጣት ያን እለት ከስብሰባው እንደወጣ የመጣው ወደ ቅንጅት ቢሮ ነበር::ዛሬ ማንን መምረጥ እንዳለብን ጠቅላይ ሚኒስትሩ አሰረድተውናልና የአባልነት ፎርም ስጡን ነበር ያሉት::

ገዢው ፓርቲ ሁኔታው እየከዳው መሄዱን ቢረዳም የምርጫው ውጤት ግን ወደሱ እንደሚያደላ ጥርጥር አልነበረውም:: ይሁንና በመገናኛ ብዙሃን ቅንጅት የሚያቀርባቸው የቅስቀሳ ፕሮግራሞች አውነትን የያዙ የሕዘቡን ችግርና መፍትሔውን ያጣቀሱ ስለነበር ይህ ትንሽ ግር ብሎታል::

## *ሥልቱን የሳተ የአብዬ እስከ ወደ እምዬ "የፖለቲካ ዳጥ፣ አንሸራቶ ጉልበት ይቀጠቅጥ"*

በቴሌቪዥን ይካሄድ የነበረው ውይይት ላይ ቅንጅትን ወክለው የሚቀርቡት በሙሉ የሚያነሱትን ርዕሰ ጉዳይ በሚገባ ያወቁና ብቃትም ያላቸው መሆን እንዳለባቸው ስለታመነበት "ማን ምን ርእስ ይዞ ይቅረብ?" የሚለው በሚገባ ውይይት ተካሂዶበት ለየርእሱ ባለሙያዎች ተመድበውለታል:: የተመደቡትም የሚከራከሩበትን ርእስ በጥንቃቄ አውቀው ተዘጋጅተው ነበር የሚቀርቡት::

የገዢው ፓርቲ ይሆናሉ ብሎ ያቀረባቸው ተናጋሪዎች በአብዛኛው ለንቀትና ለስድብ፤ የተዘጋጁ ጥላቻ የሚታይባቸው፤ ለሕዝብ ከበሬታ የሌላቸው፤ እራሳቸውን ከማንም በላይ አዋቂ አድርገው ያስቀመጡና በዚያ ውይይት ወቅት እንደፓርቲ ተወካይ ሳይሆን ያላቸው የመንግሥትነት ስልጣን ጫና እንዲፈጥር የሚሞክሩ ነበሩ::

በተለያየ ርእስ ላይ በቀረበው ክርክር የገዢው ፓርቲ በአንደኝነት ያለፈበት ሁኔታ ቢኖር ስድብ፣ ድፍረት ያውም ሕዝብን መድፈር ነበር::በሃገር ውስጥ ያለው የስድብ ቋንቋ አልቆባቸው ከሩዋንዳ በሃፍረት የለሽ ድፍረት ተውሰውም አምጥተው ነበር:: ብቻ ሕዝቡ ስለተረዳውና ስለገባው ተቀባይ አላገኙም::ሌላው ቀርቶ በሃገር ውስጥ ያሉ የውጪ ተወላጆች እንኳን ምን ያህል እንደዘገነናቸው በተለያየ መልኩ ገልፀውታል::

*አንዳንድ ኢህአዴግን ጠንቅቀው የሚያውቁና በግልፅ ማንነታቸውን ያልገለፁት የኢህአዴግ አባላትና ካድሬዎች፤ ባለስልጣናትም ጭምር "ኢህአዴግ ይቺን ኢንተርሃሞይ የምትል ነገር ያላንዳች እቅድ አላነሳትም::ከዚህ ጋር የተያያዘ እቅድ ሊኖረው ይችላል"*



*የሚል አስተያየት ቢሰነዝሩም በቅንጅት በኩል ያንን ያደርጋል ብሎ መቀበሉ አስቸግሮ ነበር)*

በቴሌቪዥን ፕሮግራም በኩል ከተሰሩት ስህተቶች በጣም የሚያስገርመው፣ ቀን በግላጭ ሕዝቡ በየቤቱ ሲከታተል የቆየውን የክርክር ፕሮግራም በምረጡን ቅስቀሳቸው ላይ ሲቀርብ የዘመን አመጣሽ ቴክኖሎጂን ኤዲቲንግ (ቆርጦ መቀጠል) መጠቀም ነበር:: የቆርጦ ቀጥሉ አሰራር ምን ያህል የሞኝ ሥራ እንደነበር የሚያሳየው፣ ሕዝቡ በቀጥታ ሲተላለፍ የተከታተለውን ፕሮግራም በጣጥሰው ማቅረባቸው ነው:: ሕዝቡም ምን ያህል ቢንቁን ነው እንዲህ ቀይረው የሚያቀርቡት የሚል ትዝበት እንዲያነሱ አድርጎታል::

ይህ አይነቱ አቀራረብ የሚሰራው ምናልባት ፕሮግራሙ በቀጥታ ባይተላለፍ ነበር::ቀጥታ ሲተላለፍ ያየው ተመልካች ነው የቅስቀሳ ፕሮግራሙንም የሚከታተለው:: ለክርክሩ ፕሮግራም አንድ አይን፣ ለቅስቀሳው ደሞ የተለየ ዐይን የለውምና:: ማንኛውም የቅስቀሳ ፕሮግራም በጥንቃቄ የሕዝብን አመለካከት በማገናዘብ፤ ምን ምላሽ ያስገኛል? ጥቅሙና ጉዳቱ ምን ያህል ነው? ተብሎ ሊቀርብ ይገባዋል:: መቼም የማልረሳው በወያኔ ኢህአዴግ የቴሌቪዥን ቅስቀሳ የምትቀርበው የፊልም ቁራጭ ያቺ በግሬደር የአርሶ አደር ቤት ሲፈርስ የምታሳየው ናት:: ለምን እንደቀረበች ብዙም ግልጥ ባይሆንም፣ "ወደዚያ ሥርአት ሊመልሱህ ነው፣ ቤትህን ሊያሳጡህ ነው!" ለማለት ይመስላል:: ያ ቪድዮ የተቀረፀው ቀለመወርቅ ደበበ የተባለ ባለሙያ በፃፈውና ባዘጋጀው የቴሌቪዥን ድራማ ነው:: ድራማው የፊውዳሉ ስርአት ያደርስ የነበረውን መከራ የሚያሳይ ነው:: ታዲያ ካስፈለገ ድራማውን ሙሉውን ማቅረብ ነበር ባየሁት ቁጥር ያስቀኝ ነበር:: አይ አለማወቅ!

ለቅንጅት ያልተሰጠው ስም አልነበረም::የተቻለው ሁሉ የስም ማጥፋት ዘመቻ ሁሉ ተካሂዶበታል::ሕዝብ "ደሞ፣ ምነው ይህን ቅንጅትን ወያኔ ኢህአዴግ ይህን

ያህል ጠላው? እስቲ ምንድን ነው ሚስጥሩ?" ማለት ጀመረና ሲመራመር «ለካ ገዢው ፓርቲ ቢጠላውም እውነት ነው» ማለት ጀመረ:: በራሱ ሚዛን ለክቶ፣ "ምክንያቱም" አለ ሕዝቡ፤ "ምክንያቱም ቁምነገር የተጠነሰሰበት የፖለቲካ ድርጅት ነው" አለ:: ከዚያ በኋላ በጥንቃቄ የቅንጅትን ሁኔታ መከታተልና የፕሮግራሞቹ ሁሉ ሱሰኛና ደንበኛ መሆን ጀመረ::ለቅስቀሳ የሚሆኑ ነጥቦችና ለክርክር የሚጠቅሙ ሃሳቦች ያጎርፍለት ጀመር::

የቴሌቪዥኑ ክርክር ላይ የቅንጅት አቀራቢዎች በሚያነሷቸው ጭብጦችና ሕዝባዊነት አንጀቱ ቅቤ የሚጠጣው ተሳታፊ ሕዝብ በጭብጨባ አድናቆቱን ሲገልጥ፣ የኢህአዴግ አቀራቢዎች የጭብጨባ ትርፍራፊ እንኳን አጡ:: በተለይ ደጋግመው የሚቀርቡት አቶ በረከት ስለነበሩ በሰአት መጥፋት በማሳበብ በአዳራሹ ጭብጨባ እንዳይደረግ ማዕቀብ (በዓለም የስብሰባ ታሪክ ለመጀመርያ ሳይሆን አይቀርም) አስጣሉ::ይህ በሆነ በሳምንቱ በሚካሄደው ስብሰባ ላይ ኢንተር አፍሪካ ግሩፕ በክብር በደብዳቤ የጠራቸው የቅንጅት መግቢያ በር ላይ ታግደው ቆመው የኢህአዴግ ደጋፊዎች ገቡ:: የቅንጅት ተከራካሪዎች ሁኔታውን በማጣራት፤ «በክብር ከተጠራው ተሳታፊ መሃል የገቡት በአብላጫው የወያኔ ኢህአዴግ ደጋፊዎችና ካድሬዎች ሆነው ሌላው ሕዝብ ውጪ  ነውና መልስ ካልተሰጠው ክርክሩን አናካሂድም» አሉ::

በዚህ እነ አቶ በረከት አልተስማሙም::እንደ አማራጭ የቀረበውም፤«እንግዲያው በፊርማና ማህተም የጋበዛችሁትን ሕዝብ ወጥታችሁ ይቅርታ ጠይቁትና ይመለስ» ቢባሉም ኢንተር አፍሪካ  ግሩፕ ይህን ለማድረግ አልፈቀደም::የገዢው ፓርቲ ካድሬዎች ደሞ፤ ቅንጅት ርካሽ ጭብጨባ ፍለጋ ነው ይህን ሰበብ ያመጣው አሉ:: ቅንጅት ደሞ፣ «እኛ ለሕዝብ ከበሬታ ቅድሚያ እንሰጣለን:: ከ300 በላይ የሆነ ተጋባዥ አትገባም ተብሎ ታግዶ እኛ ፕሮግራሙን መካፈል ማለት የሕዝብ ንቀት ነውና አናደርገውም» በማለት የቅንጅት አባላት ጥለው ወጡ::



የገዢው ፓርቲ በዚያ ፕሮግራም ላይ እንደማንኛ ውም ፓርቲ ተጋብዞ ተሳታፊ ሆኖ ሳለ፣መመርያ የመስጠትም፣ የአዛዥነትም ስልጣን ሊኖረው አይገባም ነበር:: ነገሩ ከጅምሩ አንስቶ  የተገላቢጦሽ ነበር:: በክርክሩ ላይ ማን እንዴት መቅረብ እንዳለበት መመሪያ ይሰጥ ነበር፤ ፈላጭ ቆራጭነትም ይቃጣዋል:: አንዳንድ ጊዜ እንዲያውም ሌሎቻችሁ ዝም ብላችሁ እኔ ብቻ ላውራ ወደ ማለቱም ይዳዳቸዋል::  የተቃዋሚ ፓርቲዎች ይህን ሁሉ ችለው ነው በድል አድራጊነት የተወጡት::

ቅንጅት ለሕዝብ ያለውን ከበሬታ አሳይቶና ያንን አቋም ይዞ ከወጣ በኋላ፣ ያ የማዘዝ ሱስ ያለበት ወያኔ/ኢህአዴግ አሁንም በማያገባው ገብቶ ቅንጅት ሕዝቡን ይቅርታ ሊጠይቅ ይገባል፣ ካልሆነ በውይይቱ ላይ መገኘት የለበትም::» የሚል ሆነ አቋሙ:: ምን አገባው? ምን ቤት ነው? በዚያ ቦታ ያለው ሚና የአንድ ፓርቲ ያህል ነው:: ለምን ፓርቲውንና ገዢነቱን ያደባልቀዋል? ይህ የቴሌቪዥን ክርክር የኢንተር አፍሪካ ግሩፕ ፕሮግራም እንጂ:: የዋልታ፣ የሜጋ ወይም የፋና አይደለም:: እና ማን ነው ከተሳታፊነት ወደ ፈላጭ ቆራጭ ትእዛዝ ሰጪነት ያሸጋገረው? ነው ወይስ ስልቻ ቀልቀሎ፣ ቀልቀሎ ስልቻ መሆኑ ነው?

ቅንጅት የቴሌቪዥን ተሳትፎ ካቋረጠ በኋላ የተመልካቹ የፕሮግራም ተቀባይነትና ጣዕሙ ወረደ:: የቅንጅት አስፈላጊነት ወሳኝ ሆነና ቅንጅት እንዲመለስ ተጠየቀ፤ እሱም ተቀበለ:: የወያኔ ካድሬዎች "ሕዝብን በመድፈር ስብሰባ ረግጠው ወጡ" በማለት ሕዝብንና ቅንጅትን ለማጋጨት ጥረት ከማድረግ አልታገሱም:: በተደጋጋሚ በየቦታውና በየአጋጣሚው፤ በየቅስቀሳቸው ላይ ያንን እያቀረቡ ቅንጅትን ወንጀለኛ ለማድረግ ቁጭ ብድግ አሉ:: ሰሚ ጠፋና አልሳካ አለ:: ሕዝብ "የተወሰደው አቋዋም ለሕዝብ ካለ ከበሬታና ወገናዊነት ነው" ብሎ ደመደመ::

ምንም ይሁን ምን "ሕዝብ ከበሬታ ይገባዋል፤ሕዝብን እመራለሁ፤ሕዝብ ይመርጠኛል፤ሕዝብን አስተዳድራለሁ" የሚል ሃይል በምንም መልኩ እራሱንና የራሱን ብቻ ፍላጎትና ማንነት በማስቀደም ያዙኝ ልቀቁኝ ሊል አይገባም:: ይህ ደሞ የበለጠ የመረረ ጥላቻ ነው የሚያተርፍለት:: ሕዝብን የሚንቅ ሃይል ምን ሊሆን ነው በሕዝብ ፊት የሚቀርበው? በውድድር ለመሸነፍ አንዱ ምክንያት ታዛቢን፣ ተመልካችን ከመናቅ የሚመነጭ ጥላቻ ነው::

ወያኔ ኢህአዴግ ሲጨንቀው ቅንጅትን ኢንተርሀምዌይ የሚል የተውሶ የወንጀለኛ ስም ለጠፈበት:: ትርጉሙ በደንብ ባልገባቸውና ተፅፎ በተሰጣቸው ግብዝ ካድሬዎችም በየቦታው አስተጋቡት:: እንደእውነቱ ከሆነ ማንኛቸውም የቃሉን ታሪካዊ አመጣጥና ምንነት ትንሽ ንባብ ያካሄዱ አይመስልም:: ቃሉን ሲጠሩት በፈገግታና ደስታ በተመላበት ስሜት ነበር:: ኢንተርሃምዌይ የሚያስቅ ሳይሆን የሚያስለቅስ ሰቆቃ፣ እልቂት፣ ጭፍጨፋ ነው:: አይ አለማወቅ ደጉ! ያ ስም የተሰጠው ደሞ ዶ/ር ያዕቆብን ያህል ኢትዮጵያዊ፣ ያውም በተባበሩት መንግሥታት የኢንተርሃምዌይ ወንጀለኞችን እያጣራ ለፍርድ ለማቅረብ አቃቤ ህግ ሆኖ በሩዋንዳ ሲሰራ የነበረ ሰው ያለበትን ፓርቲ ነው:: በዚያ ስም፤ የሩዋንዳን ያህል ቀርቶ አንድ አስረኛውን ያህል ጥላቻ በመሃላችን የሌለንን ሰዎች በዚያ ስም መጥራት ምን አይነት አለማወቅና አረመኔነት ነው?

እኔ ስጋት ነበረኝ:: 'ይህ ስም ለምን ተነሳ? በሩዋንዳም ቢሆን ገዢው መንግሥት ነው ያንን የፈፀመው::ታዲያ አሁን ገዢው ፓርቲ ያንን ስም ለምን አነሳው?' የሚለው ጥያቄ አስግቶኛል:: ኢንተርሃምዌይ ተግባራዊ የሆነው የሩዋንዳ ገዢ መንግሥት የተቃዋሚ አባላትን በገቡበት እየገባ ከተሸሸጉበት እያወጣ መታወቂያቸውን እየፈተሸ እነሱው በከፈሉት ግብር በተገዛ መሣሪያ በሃገራቸው ላይ እንደጠላት ደማቸው ፈሰሰ፣ሰውነታቸው በገጀራና በመጥረቢያ ተቆራረጠ፣



እሬሳቸው ለጸሐይ ተሰጣ::አሁን ታዲያ በኛስ ሃገር ሁኔታ ማነው ኢንተርሃምዌዩ? ምንም መሳሪያ ሳይዝ በዕውቀቱና በልምዱ፣ በብእርና በወረቀት ለሕዝብ ነጻነት እታገላለሁ ብሎ የቆመው ነው ወይስ ታሪክ የመዘገበውን ጨካኜና አረመኔነት በተግባር በተደጋጋሚ የፈጸመው? ለዚህ ማስረጃና ምስክር ማቅረብ አያስፈልገኝም:: በዚያም ሆነ በዚህ ወያኔ ኢህአዴግ በቴሌቪዥን ክርክሩ አንድ ጊዜ ሳይቀናው በተጋጠመበት ሁሉ ግቡን ሳይመታ ነበር ፕሮግራሙ የተጠናቀቀው::

በክርክሩ ላይ ከቀረቡት የገዢው ፓርቲ ተሳታፊዎች ባቀረቡት ሃሳብና በአቀራረብ ችሎታቸው አቶ ግርማ ብሩ የማይናቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል::አቶ በረከትም በአነጋገራቸው ንቀት ማን አለብኝነት ቢኖርም ይናገራሉ፤ለማሳመን ይጥራሉ:: ብልጥ ናቸው:: ከንግግር መሃል አንዲት ቃል አውጥተው ነው ለመጫወት የሚፈልጉት:: ሰራም አልሰራም ቀላል አቀራረብ አልነበረም::

በተናጠል የፖለቲካ ፓርቲዎች ያላነሱዋቸውን ወይንም ማብራራት እንፈልጋለን በሚሏቸው ነጥቦች ላይ ፕሮግራም ተሰጠ:: ይህ አሁንም ለገዢው መንግስት ኪሳራ ማካካሻ አንድ ጠቀሜታ ይዞ የመጣ ፕሮግራም ነበር:: በዚህ ፕሮግራም ላይ ኢህአዴግን ወክለው የሚናገሩት ጠ/ሚኒስትር መለስ ነበሩ:: ሃሳባቸውን አቀረቡ፣ ቅንጅትንም ኢንተርሃምዌይ አሉት:: የሚዘገንን ነገር:: ቀሪ ሂሳባቸውንም በሁለት ሰአት ተኩል አወራረዱ::የአክሱም ሃውልት ለወላይታው ምኑ ነውም ተካደ:: ባንዲራው ጨርቅ ነው አልተነሳም፣ አሰብን አንፈልግም ሰበቡና ምክንያቱ አልተብራራም:: የባድሜ ጉዳይም ለይስሙላ ነው ተሞከረ::

ቅንጅት የመጨረሻ ቀራቢ ነበር፣ ዶ/ር ብርሃኑና ልደቱ ተመቻቸው:: በነገራችን ላይ ፕሮግራሞቹ የተቀረፁት አንዱ የሌላውን ባለማየትና ለዚያ መልስ በማያዘጋጅበት ሁኔታ ነው:: ሁሉም አስቀርፀው ከጨረሱ በኋላ ነው መተላለፍ የጀመረው:: ቢሆንም

ግን፣ ክርስቶስ ለስጋው አደላ ነውና ከመተላለፉ በፊት ወደ ላይ ሄዶ ሳይታይ ይቀራል ብላችሁ ነው?::

በዚህ በመጨረሻው የሁለት ሰአት ተምናምን ፕሮግራም ላይ ብርሃኑና ልደቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማወቅ ያለበትን ዕውነታ ሁሉ አዝረከረኩት:: የወያኔ ኢህአዴግ የንግድ ድርጅቶች አንዲት ብናኝ ጥቅም በማያገኘው የትግራይ ሕዝብ ስም እየነገዱባቸው እንደሆነ፤ ገዢው ፓርቲ ምን ያህል ገበሬውን እንዳደኸየው፤ የንግዱን ሕብረተሰብ አስሮ መንቀሳቀሻ እንዳሳጣው፤ የትምህርቱን፣ የጤናውን በአጠቃላይ ሁሉንም የኢህአዴግ ፖሊሲ ልክ አሳዩትና ወያኔን ባዶ አስቀሩት:: ሌላ ድል ለቅንጅት ተመዘገበ::

ኢህአዴግ አካሄዱ ሁሉ እያንሸራተተ ሊጥለው መሆኑን በመገንዘብ ቅንጅትን ጭራቅ አድርጎ ለማቅረብ በልዩ ዘዴ መንቀሳቀሱን አጠናከረ::ለዚህ አንድ ማሰሪያ እንደሚያስፈልገው በማቀድ፣ ቅንጅት በሬዲዮም በቴሌቪዥንም ባለው የምፅዋት ሰአት እውነቱን አጋለጠ::

*ለምሳሌ.........*

"የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!

ገዢው ፓርቲ ወያኔ/ኢህአዴግ፤ በጉልት ርስትነት የያዘው፤እንዳሻው የሚያዝበትን የሃገሪቱን የገጠርና የከተማ ቦታ ብቻ ሳይሆን፣ የሃገሪቱንም ሰፊ የቴሌቪዥን እና የሬዲዮ የስርጭት ጊዜንም ነው::ይህ ስርጭት በገዢው ፓርቲ ስር ያሉትን ብቻ ሳይሆን ህገወጥ በሆነ መንገድ ከፍቶ የሚጠቀምባቸውን የግሉ ሬዲዮ ጣቢያዎችን ይጨምራል:: ይህንን የሃገሪቱን የሬዲዮና የቴሌቪዥን አገልግሎት በፈለገው ሰአት፣ የፈለገውን እጅ እጅ የሚል ፕሮፓጋንዳ ሲነዛበት እንደኖረ እናውቃለን:: በዚህ የምርጫ ወቅት ደሞ፤አይኑን በጨው አጥቦ እኔም እንደተቀናቃኝ የፖለቲካ ድርጅቶች የስርጭት ጊዜ ይሰጠኝ ብሎ፤ያው እራሱ በርስተ ጉልትነት ከያዘው የቴሌቪዥንና የሬዲዮ



ሰአት ሰፋ ያለውን ጊዜ ለራሱ ገምሶ በመውሰድ ከእኛ ጋር እየተጋፋ ነው::ያንኑ ያረጀና ያፈጀ፤ከዚህ ቀደም ከሃገራችንና ውልቅልቃቸው ከወጡ የቀድሞ የምስራቅ አውሮፓ አምባገነን የኮሙኒስት ስርአቶች ተሞክሮ በውሸታምነቱ እና በቆርጦ ቀጥልነቱ ህዝብን ያታከተ፤ በመጨረሻም ለስርአቶቹም ያልበጀ ቅጥፈት እያሰራጨ ነው::

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!

"የኛ ምርጫ፣ በወያኔ ኢህአዴግ ከተያዘው ሰፊ የቴሌቪዥንና የሬዲዮ የስርጭት ሰአታት ተቆንጥረው፤በገዢው ፓርቲ ችሮታና ፈቃድ የተሰጡንን የማስታወቂያ ጥቂት ደቂቃዎች የቅንጅታችንን የምርጫ ማኒፌስቶ ለሕዝብ በመግለፅ ሙሉ በሙሉ በመጠቀም ነበር:: በከፍተኛ ህዝባዊነትና የሃገራዊነት ራእይ የተገነቡ ዝርዝር የልማት፤ የትምህርት፤ የጤና፤ የሰላም፤ የአንድነት፤ የእኩልነት፤ የፍትህ፤ የመልካምአስተዳደር፤ እና ሌሎችም ፖሊሲዎች እንዳሉን ደጋፊዎቻችን ያውቁታል:: ለዚህም ነው፣ «እባካችሁ እራሱ ተዋርዶ ሌላውን ማዋረድ ለሚፈልገው ወያኔ ኢህአዴግ አሉባልታዎችና ቅጥፈቶች መልስ በመስጠት ጊዜያችሁን አታጥፉ:: ያለቻችሁን ጥቂት ደቂቃዎች ፖሊሲዎቻችሁን በማስተዋወቅ ተጠቀሙባቸው::» በማለት የመከራችሁን፤ የወተወታችሁን::"

"ይህንን በማሰብም ነበር፤ባለፈው ሰኞ ምሽት፤በዚህ የምርጫ ፖሊሲ ሰነድ ውስጥ አርሶ አደሩን እና የገጠር መሬትን በሚመለከት ያሰፈርነውን የፖሊሲ ነጥብ ለህዝብ የገለፅነው::

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!

"በሃገራችን ታሪክ ተደጋግሞ እንደታየው፤ሰላማዊ ባልሆነ መንገድ፤ ስልጣን ላይ

በነበሩ መንግስታት እና በተቃዋሚዎች መሃል የተደረጉ ትንቅንቆች ሁሌ የዜጎችን ሕይወት በሺዎች አስቀጥፈው፤የንብረትና የሃብት ውድመት አስከትለው በመንግሥት አሸናፊነት የተጠናቀቁ ናቸው::እንደሌሎች ተቃዋሚዎች ይህ ዕጣ ያልገጠመው የወያኔ/ኢህአዴግ እንቅስቃሴ ብቻ ነው::ይህም የሆነበት የራሱ ታሪካዊ ምክንያቶች አሉት::

"ቅንጅታችን ከሃገራችን ያለፈ የፖለቲካ ታሪክ ትምሕርት ወስዷል::ከሰላማዊና ከህጋዊ ትግል ውጪ፤እስከ ጥርሱ ከታጠቀ መንግሥት መንጋጋ፤ስልጣን መንጠቅ ይቻላል ብሎ አያምንም:: "ህጋዊና ሰላማዊ ባልሆነ መንገድ፤ስልጣን ላይ ለመውጣት የሚሞክር ሁሉ በሃገር እና በሕዝብ ላይ መከራ ለማዝነብ የሚሻ ብቻ እንደሆነ ያምናል:: በዚህ መንገድ የተያዘ ስልጣን ሃገራዊ እና ህዝባዊ እርባና እንደሌለው ሁላችንም ከወያኔ ኢህአዴግ ተምረናል:: ይህ የቅንጅት እምነት ነው::ደግመን ደጋግመን ለሕዘብ የገባነው ቃል ኪዳን ነው::ይህ ገሃድ ሆኖ እያለ፤በእጃችን ሰንጢ እንደሌለን እየታወቀ፤የተዋጊ ጀቶች፤የታንኮች፤ የብዙ መድፎችና መትረየሶች ባለቤት የሆነው የገዢው ፓርቲ ለምን እራሱ ተሸብሮ እኛን ተቃዋሚዎችን በአሸባሪነት እየከሰሰ ሕዝብ ለማሸበር ይጥራል? መልሱ ግልፅ ነው::

"ሰላማዊና ሕዝባዊ በሆነ መንገድ እስካሁን ባደረግነው ትግል፤የወያኔ-ኢህአዴግ ድርጅት በገጠርም ሆነ በከተማ፤ ሃገሬው እንዳለው « በቅዳሜ ገበያ ለቀትር ፀሐይ እንደተጋለጠ ቅቤ እየቀለጠ» መሆኑን በማየቱና በማወቁ ብቻ ነው::

## ውሃ ቢወቅጡት እምቦጭ ኢህአዴጋዊ የፖለቲካ ዝቃጭ

በሁኔታው የተደናገጠው ወያኔ ኢህአዴግ የቀረው አማራጭ፤ ህዝብ ለተረጋጋ ሕይወቱ



የሚፈልገውን የሰላም መኖር፤በተቃዋሚዎች እንደሚደፈርስ አድርጎ በማቅረብ እራሱ ሽብር በመንዛት መልሰም ለሰላማችሁ ስትሉ ምረጡኝ ማለት ነው የተያያዘው:: በቅንጅቱ እና በሌሎችም ሰላማዊና ሕጋዊ የፖለቲካ ተፎካካሪዎች ላይ በሁሉም የሃገሪቱ ክፍሎች የሚያካሂደው አፈና እና እንግልት፤ ማስፈራራትና ተፅእኖ የዚሁ የወያኔ ኢህአዴግ የአሸባሪነት መርሃ ግብር ዋና ገፅታዎች ናቸው::

አሁን ደግሞ ይህ የአፈና መርሃ ግብር ያነጣጠረው፤በለውጥ ፈላጊነቱ፤ በአቅምና ቀልጣፋነቱ በህብረተሰቡ ውስጥ አቢይና ወሳኝ ሚና መጫወት በሚችለው የሃገራችን ወጣት ላይ ነው:: የሃገራችን ከተሞች በመንግሥት የተሳሳቱ የትምህርት እና የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች የከፍተኛ ትምህርትና ስራ የማግኘት እድል የተዘጋባቸው በመቶ ሺዎች በሚቆጠሩ ወጣቶች የተሞሉ ናቸው:: የከተሞችን የወጣት ቁጥር ያናረው በየከተማው ትምህርቱን እየጨረሰ ወይም ትምህርቱን እንዲያቋርጥ ተደርጎ በየወላጆቹ ቤት ሳይወድ በግድ የወጣት ጡረተኛ ሆኖ እንዲኖር የተፈረደበትን ከተሜ ብቻ አይደለም::በተሳሳተ የመንግሥት የመሬትና የልማት ፖሊሲ የተነሳ ሳያቋርጥ ከሚዘንበው የገጠር የድህነትና የችጋር ዶፍ ለማምለጥ፤ከተሞችን የተስፋ መስኮት አድርጎ ወደ ከተሞች የሚጎርፈው የዋህ የገጠር ወጣትም ቁጥር እጅግ ብዙ ነው::»

መንግሥት ከፍተኛው ቀጣሪ በሆነበት ሃገር ውስጥ፤በየከተማው የሚገኘው ወጣት ችሎታውንና ብቃቱን በማቅረብ በከተሞቹ ለሚፈጠሩ ጥቂት የስራ እድሎች እንኳን መወዳደር እንዳይችል፤ ይህን ጠባብ እድል ወያኔ ከየትኛውም ቦታ ለሚያሰባስባቸው፤ከታማኝነት በስተቀር ሌላ ተጨባጭ መመዘኛ ለማያልፉ በዝምድና፤በመንደር እና በጎጥ ልጅነት ለተሳሰሩ ጀሌዎች ሲያድለው ኖሯል:: ሥራ ያጣው ብቻ ሳይሆን፤በመከራም የተገኘች ስራ ያለው ወጣት ጭምር በገቢው አነስተኛነት የተነሳ ከስቃይ አላመለጠም::ይህ ብቻ አይደለም::ተወልዶ ባደገበት

ከተማ የተሻለ ሥራ የማግኘት እድሉ መዘጋቱ ብቻ ሳይሆን በሰላሳና በአርባ ዓመት የጎልማሳነት እድሜው መሄጃ አጥቶ ከእናቱ ጋር ተደርቦ እየኖረ ነው:: የራሱን ቤት፣ትዳርና ቤተሰብ መስርቶ መኖር አልቻለም::

በየከተማው በመንግሥት እጅ ያለችው የኪራይ ቤት እድል፣በከተማው ኗሪነት ቅድሚያ ለማይገባቸው ከወያኔ/ ኢህአዴግ ባለስልጣናትና ተባባሪዎቻቸው ጋር በተለያዩ መንገዶች ለተሳሰሩ ታማኞቻቸው ብቻ እየተሰጠ፣የከተሜው ወጣት « ጎጆ መውጣት » የሚለው አባባል ትርጉሙ ጠፍቶታል:: ኢትዮጵያ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች በስራ አጥነት፣በድህነት፣በተስፋ ማጣት እየደቀቁ የሚኖሩባት ሃገር ናት:: ኤይድስን በመሰለ አስከፊ በሽታ በለጋ እድሜያቸው የሚቀጠፉትን፣ የሃገራቸውን አስከፊ ድህነትና አፈና ለማምለጥ ሲሉ በእግራቸው ሳይቀር በረሃ እያቋረጡ በየሰዉ ሃገር ለመሰደድ ሙከራ ሲያደርጉ የሚያልቁትን ቁጥር በአንድ ላይ ስንደምረው እጅግ የሚዘገንን መሆኑን እናውቃለን::

ይህ የወጣቱ ሥቀይ የሚሰማው ሰብአዊ ፍጡር ችግራቸው እንዲቃለል የተቻለውን ያደርጋል እንጂ በቁስላቸው እንጨት አይሰድም:: የወያኔ ኢህአዴግ ባለስልጣናት ግን እንዲህ አይነቱ ሰብአዊነት ስለሌላቸው ይህን ምርጫ ተገን በማድረግ ሊዘምቱበት ያቀዱት በዚሁ መከረኛ ወጣት ትውልድ ላይ ነው::

ይህ ወጣት የቅንጅቱን ዓላማ በፍጥነት ተረድቶ፣ ለህብረተሰቡም በማስረዳት ለውጥ ፈላጊነቱን በየወረዳው በተጠሩ ሰላማዊና ህጋዊ የቅንጅቱ ስብሰባዎች ስላየ ወያኔ/ኢህአዴግ ተደናግጧል:: ዛሬ እንዲህ ከመደናገጥ፣ ባለፉት አስራ አራት ዓመታት የስልጣን ዘመናቸው የከተማውን ቦታ እየዘረፉ በሚሊዮኖች ብር የፈጁ ቪላዎቻቸውን ከመገንባት፣ በ20ሺዎች በሚቆጠሩ ብሮች ለማከራየት ከመጣደፍ፣ በሰበብ አስባቡ በውጭ ሃገር የስራ ጉብኝት ስም የሃገሪቱን የውጭ ምንዛሪ በውሎ አበል ስም እየሰበሰቡ የፈረንጅ ሃገር ባንኮችን የሚያስጨንቅ ዶላር ከማጠራቀም ይልቅ፣አንድ መለኪያ



ኮኛክ በሁለት ገበሬዎች የአመት ገቢ በማይሸፈንበት ውድ ሆቴል ውስጥ ሲጋበዙና ሲገባበዙ ከማደር ይልቅ፣የዚህን ወጣት ችግር ለደቂቃም ቢሆን ዞር ብለው አይተው ቢሆን ኖሮ ዛሬ ወጣቱን ከምርጫ ለማራቅ ያደገኛ በዘኔ ክሳቸውን ሊደረድሩበት ባልተገደዱም ነበር::

የሃገራችን ከተሞች ወጣት፣የአምባገነኖች እኩይ ኢላማ ሲሆን፣ሰበብ አስባብ እየተፈለገ ሊዘመትበት ሲፈለግ ዛሬ የመጀመርያው አይደለም:: ግራዚያኒም፣እነ አብርሃም ደቦጭ ያደረሱበትን ጥቃት ሰበብ በማድረግ በቅድሚያ የዘመተው በዘመኑ ተምሯል ብሎ ባሰበው የህብረተሰብ ክፍል፣በወጣቱ ላይ ነው:: ያለፉት የሃገራችን የመንግሥት ስርአቶችም ከማንኛውም የህብረተሰብ ክፍል በላይ ስርአታቸውን በተቃወመው ሰላማዊና ሃገር ወዳድ ወጣት ላይ ነው ቁጣቸውን ያዘነቡት::

ይህ ወጣት ግን ሃገር ተወረረ ብለው ገዢ-ዎቻችን በጠሩት ቁጥር ለሃገሩ ደሙን ከማፍሰስ በስተቀር ለመስዋእትነቱ የተለየ ወሮታ ክፈሉኝ ብሎ አያውቅም:: ሌላው ሁሉ ቀርቶ ዛሬ ወያኔ ኢህአዴግ ይህ አደገኛ በዘኔ በማለት ሊዘምትበት የተዘጋጀ ወጣት ሃይል ትናንት ከሻእቢያ ጋር ለመተናነቅ ወያኔ ኢህአዴግን አምኖ በፈቃዱ ወደ ባድሜ የዘመተ ወጣት ነው:: ግሚሱ ቤተሰብ በዚሁ ጦርነት ያልተመለሱ የውድ ልጆቹን ሃዘን ገና ያልተወጣ ነው:: ባለፈው የደርግ ስርአት በየከተማው መንገዶች የወደቁ ልጆቻቸውን፣ ወንድሞቻቸውን፣ የሚያስታውሱ እናቶች እና እህቶች ያሉት ወጣት ነው::

ይህንን ወጣት እና ቤተሰቦቹን ነው ወያኔ ኢህአዴግ በሩዋንዳ ከተሞች በመንግሥት ባለስላጣናት ተጨፍጭፈው በየመንገዱ የወደቁ ሰዎችን እሬሳ በየቀኑ እያሳየ እንዲሸማቀቁ የሚያደርጋቸው:: አላማው በሽብርና በፍራቻ ህዝብን እና ወጣቱን አስበርግጎ ከምርጫው እንዲርቁ ወይም ኢህአዴግን እንዲመርጡ ለማድረግ ነው:: ይህ ግን የሚሳካ ዓላማ አይደለም::

ሕዝቡ ጥቅምና ጉዳቱን ለይቶ አገናዝቦ ወስኖ ጨርሷል::

«ቀድሞ ነበር እንጂ መጥኖ መደቆስ

አሁን ምን ያደርጋል ድስት ጥዶ ማልቀስ» እያለ ነው:: ወስኗል!::

**ቅ**ንጅት ሰላም

**ቅ**ንጅት ፍቅር

**ቅ**ንጅት አንድነት

**ቅ**ንጅት ተስፋ

**ቅ**ንጅት ሕይወት

መሆኑን የተረዳው ወጣት በአምባገነኖች ሽብር ተደናግጦ ለድርጅታችን የሚሰጠውን ድጋፍ ከቶውንም አላቆመም::

«ወያኔ ኢህአዴጎች! እባካችሁ ይህንን ተረድታችሁ፤ በሰላም ከመኖር፤ ከመማር፤ ከመሥራት ውጪ የተለየ ዓላማ የሌላቸውን ወጣቶች እና ቤተሰቦቻቸውን ተሸብራችሁ አታሸብሩ::ቅንጅት ማንኛ ውንም የአምባገነኖች ድርጊት በህጋዊና በሰላማዊ ትግል አሸንፎ ድልን ይቀዳጃል::»

ይህን መልእክት ለሕዝቡ ስናቀርብ ሕዝብ ሁኔታውን በማገናዘብ ከልቡ አዘነና ለትግሉ ቆራጥ ውሳኔ ላይ ደረሰ:: ወጣቱም የመጣው ይምጣ እንጂ ለነፃነት ለፍትህ የተነሳውን ወኔያችንን የወያኔ ፕሮፓጋንዳ አያኮላሸውም በማለት ትግሉን አጠናከረ::



ቤተሰቡም፣ እኛም ለሰብአዊና ለዴሞክራሲ መብታችን ለሃገራችን ልማትና ለራሳችን ፍትህ ከናንተ ጎን እንቆማለን ብሎ ለራሱ መሃላ ሰጠ:: ወያኔ ኢህአዴግም ፀረሕዝብ እንቅስቃሴውን የሚያግዘው ልዩ መንገድ ቀየሰ::

## ከአረንቋ ወደ አረንቋ
## (From quagmire to quagmire)

ገዢው ፓርቲ በዚህ አላበቃም አዲስ በቀየሰው መንገድ ተንቀሳቀሰ::

ለጥቆ የገባው ወደ ዕምነት ቦታዎች ነበር:: በመጀመሪያ ወደ ሙስሊሙ አማኝ መሪዎች በመሄድ፤ "ቅንጅት ከተመረጠ ሃገሪቱ የክርስቲያን ሃገር ስለምትሆን ሙስሊሙ ቦታ አይኖረውም::እንዲያውም ከአሜሪካን መንግሥት ጋር ትስስር ስላላቸው ሙስሊሙን በሙሉ ሽብርተኛ በማለት ስለሚያስጨርሱት ኢህአዴግን ከመምረጥ ውጪ አማራጭ የላችሁም" በመባላቸው ኢህአዴግ ይመርጡኛል የሚል እምነት ነበረው::ምንም እንኳን አመራሮቹ ለኢሃአዴግ ቢቆሙም መከራና ፍዳ ሲቀበል፣ የዕምነት ቦታ ሲከለከል የነበረው አማኝ ሕብረተሰብ ግን የሚመርጠውን ከማወቅም ባሻገር የሙስሊሙን የእምነት ቦታ የደፈረውን፣ በመስጊድ ገብቶ የጨፈጨፈውንና ደም የቀባውን፤የእምነት ቦታ የዘጋውን፣ አለፈቃዱ የሃይማኖት መሪ በሌለበት መርጦ የሾመበትን ስለሚያውቅ፣ ምርጫውንም ወስኖ ነበርና በዚያም በኩል ቅጣቱን በምርጫ በፍርድ አቀመሰው::

የገዢው ፓርቲ ቀጣይ የምርጫ ጦር ቀጠና ያደረገው የክርስቲያኑን መንደር ነበር::የክርስትና እምነት ተከታዮች የየቤተክርስቲያን የሥራ ሃላፊዎች ጠቅላይ ሚኒስትሩ ስለቤተክርስቲያን ጉዳይ ለማነጋገር ፈልገዋል በሚል ሽፋን ለስብሰባ መጥራት ነበር:: ጠ/ሚኒስትሩ ውይይቱን ሲጀምሩ "በቤተክርስቲያን ያለውን ችግር እንድንወያይ ነው የተሰበሰብነው"

በማለት ያለውን ችግር ቀሳውስቱ እንዲያነሱ ስብሰባው ተከፈተ:: ቁጥራቸው አናሳ የሆኑ የኢህአዴግ ቀንደኛ ታማኞች አስተያየታቸውንና ለኢህአዴግ ያላቸውን ታማኝነት በመግለጽ "ኢህአዴግ ለዘልአለም ይኑር!" ቢሉም በርካታ የሆኑት ግን ይህን አባባል ከምንም ሳይቆጥሩ ጥያቄ አነሱ::

.....«ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ይህ ስብሰባ ከምርጫው ቀን ቀደም ብሎ መደረጉ ያለዎትን የእምነት ፍቅር ያሳያል:: ሆኖም ግን፣ እርስዎ ቀደም ሲል በሰጡት መግለጫ ይህ ምርጫ እንከን የለሽ ነው፤ማንም ማንንም ሊወቅስ የማይችልበት ዴሞክራሲያዊና ነፃ ይሆናል ብለው ለኢትዮጵያም ለዓለምም ሕዝብ የገቡትን ቃል ተቃዋሚዎች እንዳያበላሹትና ተወቃሽ እንዳያደርጉዎት፣ ተቃዋሚዎችም ተገኝተው ውይይቱን በአንድነት ብናደርግ መልካም ይሆናል፣ በእግዚአብሔርም ፊት አያስጠይቅም» በሚል ሀሳብ ቀረበና አብላጫው ተሰብሳቢ ደገፈው:: ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያላሰቡት ሁኔታ ስለገጠማቸው «ሃሳቡ ጥሩ ነው ግን ሰፊ ጊዜ ይዘን ሌላ ጊዜ እንነጋገርበታለን በማለት ስብሰባውንም፣ በክብር የጠሯቸውንም አባቶች ረግጠው ወጡ::

ይህ እቅድ እንደከሸፈ የጦር አቅጣጫው የዞረው ወደ ሴቶች በተለይም በዕድሜ ወደገፉና አቅመ ደካማ ወደሆኑ ሴቶች ነበር::አቀራረቡ ለየት ባለና የነዚህን ሴቶች ድክመት እንደመጠቀሚያ ያደረገ ነበር:: አንዱ መንገድ፣ በየመንደሩ ማህበር በሚጠጣበት በመገኘት ፅዋ በመሳለምና አማኝ በመምሰል ጠበል ቀምሰው አብረው በመቀመጥ፤በድንገት ዓየሩን በመለወጥና ስለምርጫው በማንሳት፤ ገዢውን ፓርቲ እንዲመርጡ በማግባባትና ለማሕበሩም መደገፊያ እንዲሆን ከ15 እስከ 30 ብር ድጎማ መስጠት ነው:: ሌላው በየመንደሩ የቡና ሰአትን በመጠበቅ ሳይጋበዙ እየደረሱ «ስለምትወዱን አቦል ላይ ደርሰናል» በማለት ተቀምጠው በዚያው በተለመደ መንገድ ድንገት የቡና ጠጪ ውን ወሬ ወደ ምርጫ በመለወጥ "ኢህአዴግን ምረጡ" በማለት ለቡና መግዣ ከ10 እስከ 15 ብር



በመቸር ከመንድር መንደር መዘዋወር ነበር:: በሁለቱም፤ ቅስቀሳ ላይ አንድም ገንዘቡን አልቀበልም ያለ ባለመኖሩ ምድረ ካድሬ፣ ኢህአዴግን እንደሚመረጥ በይበልጥ አረጋግጫለሁ የሚል ሪፖርት ለበላይ አካላት በሙሉ ልብ አስተላለፈ::

እነዚህ ድጎማ ተቀባዮች ግን ካድሬዎቹ እንደወጡ ሲሳሳቁበት የነበረው «ብሬን በጄ ካርዱን በሆዬ፤ይለያል ጉዱ ምርጫ ሲሄዱ» በሚለው ማሳረጊያ ነው:: ሁሉም ገብቷቸው ነበር::

ባለፉት «የምርጫ» ወቅቶችም ይሁን አሁንም ስለምርጫ ያለው ግንዛቤ፣ አንዱ ፓርቲ ሌላውን ለማሸነፍና የሕዝብን ድጋፍ በአመቺው መንገድ ለማግኘ ት መጣርና አንዱ ከሌላው ጋር እንደጠላት መተያየትን ነው::ቅንጅት ይህን አመለካከት ለመለወጥና ሕብረተሰቡም ዘወትር የፖለተካዊ ስብሰባ በሚደረግበት ወቅት በሚደረጉ ንግግሮች አንዱ ፓርቲ ሌላውን መንቀፍና ድክመቱ ላይ ማተኮር፣ የራስን ከፍ ከፍ የሌላውን ድምጥማጡን ማጥፋት ሳይሆን በእውነት ላይ የተመረኮዘ የሰለጠነና ዘመናዊ አካሄድ ለሕብረተሰቡ ማሳየትና ግንዛቤውንም ዘመኑ ወደሚፈቅደው ሰላማዊና የሰለጠነ ሂደት ለማምጣት ጥረት እያደረገ ነው:: ይህንንም በመገናኛ ብዙሃን ላይ ሲያቀርብ በነበረው የቅስቀሳና የክርክር መድረኮች በትንሹም ቢሆን ለማሳየት ሞክሯል::

ቅንጅት ይህን ምርጫ፣ ገዢው ፓርቲ እንዳለው፣ "ነፃና ዴሞክራሲያዊ ይሆናል" የሚል ትንሽም እምነት ባይኖረውም፣ ያም ሆነ ይህ ይህን የምርጫ ወቅት ማወደስ አለብን፣ ሕዝቡን ለምርጫው ማዘጋጀት ተገቢ ነው በማለት «ለዴሞክራሲ ሥርአት ግንባታ እንዘምር» በሚል መርህ ለሚያዝያ 30 በመስቀል አደባባይ ሕዝባዊ ስብሰባ ለማዘጋጀት አቀደ:: ይሁንና፣ አደባባዩ በኤግዚቢሽን ማእከል ስር ነው እዚያ ጠይቁ" ተብሎ ሲጠየቅ ተይዟል ተባለ:: ውስጥ አዋቂ ምንጮች ደግሞ፣" ተይዟል ማለት የሚቻለው ሲከፈልበት ነው፤ እስካሁን የከፈለ ስለሌለ አሁን

መጥታችሁ ብትከፍሉ ልትይዙት ትችላላችሁ" ስላሉ ቅንጅቱ ወዲያው ክፍያውን በመፈጸም ቀኑን ያዘው:: ይህን ሕዝባዊ ስብሰባ «ለዴሞክራሲ ደስታ እንፍጠር፤ እንደሰት በሚል ርእስ ሥር ብናካሂደው ምን ይመስልሃል» አለኝ ዶ/ር ብርሃኑ:: ሃሳቡን ተቀበልኩትና « ምንም አይነት የፖለቲካ ስብሰባ ስሜት ሳይፈጠር ዝም ብሎ ምርጫው ዴሞክራሲን፤ ሰብአዊ መብትን በአጠቃላይ ነጻነትን በእውነተኛ ገጽታው ለሕዝብ የሚሰጥ ምርጫ እንዲሆን የምንመኝበት ይሁን» ተባብለን ተስማማን:: ብርሃኑ ሃሳቡን ለሥራ አስፈጻሚ በማቅረብ አጸደቀና «ያው እንግዲህ ተፈቅዷል፣ አስፈላጊውን በማስተካከል አዲስ ባህል እናሳይ» ብሎ ሃለፊነቱን ጫነብኝ:: በነገራችን ላይ፣ ዶ/ር ብርሃኑ የምርጫ ዘመቻ ኃላፊ ነበር:: ደግነቱ የሚያስፈልገውን ኮሚቴ ሁሉ አዋቅሮ ስለነበር የኔ ድርሻ ያ በአግባቡ መከናወኑን መከታተል ነበር::

የሙዚቃ ባንድ ያስፈልጋል፤ መድረክ ያስፈልጋል፤ የድምጽ ማጉያ ያስፈልጋል፤ እለቱ ተወስኖ ለሕብረተሰቡ ጥሪ ማድረግ ያስፈልጋል፤ ለመብራት ሓይል ማሳወቅ ያስፈልጋል፤ ለፖሊስ ማሳወቅ ያስፈልጋል፤ ብዙ ያስፈልጋሎች ነበሩ:: ለሁሉም የሚያስፈልገው በጽሁፍ ደረሰ:: ሕዝቡ ገና ስለሁኔታው ሲሰማ ወሬው ሁሉ እሱ ሆነ:: ቀኑ ተወሰነና በሚዲያ ሚያዝያ 30 የሕዝባዊ ስብሰባ ጥሪ ተደረገ::

ይህን የሰማው ኢህአዴግ የቅንጅትን ሰልፍ ለማክሸፍ በሚል እቅድ ሕዝቡን ለሚያዝያ 29 ሰልፍ ጠራ:: የተጠራውም ሰልፍ በፍቃደኝነት ውጣ ሳይሆን ነጋዴው ሱቁን ዘግቶ እንዲወጣ፣ ካልወጣ የንግድ ፈቃዱ እንደሚነጠቅ፣ የመንግሥት ሰራተኛው ሰልፍ እንዲወጣና ቁጥጥርም በሰልፉ ቦታ እንደሚደረግ፤ ለመመላለሻ አውቶቡስና ሊዎንቺና እንደሚዘጋጅ፤ ወጣቱን ሰልፍ ካልወጣህ አደገኛ ቦዘኔ ብለን እናስገባሃለን በሚል የአዲስ አበባ የወጣቶች ማህበር አባላቱን ካናቴራ አልብሶ እንዲያወጣ፤የሴቶች ማሕበርም እንዲሁ ሆነና ከአዲስ አበባ እስከ



ወሊሶ፣እስከ ሞጆ፣እስከ ሰንዳፋ፣እስከ ሱሉልታ እንዲወጣ ትእዛዝ ተሰጠው:: መጓጓዣም ቀረበለት::

## ወደ ወልቂጤና አካባቢው

የቅንጅትን ተመራጮች በየቦታው እየተገኘን የማስተዋወቅን ተግባር ተከፋፍለን በማከናወን ላይ ነን::ዛሬ ኢላማችን ወደ እነሞር ምሁርና እዣ ወረዳዎች ነው::ልክ እንደማንኛውም የምርጫ ወረዳዎቻችን ሁሉ ወደዚህም ስንሄድ ተመራጮቻችንን አጅበን ነበር::በዚህ ጉዞ ላይ አንዳርጋቸው ጽጌም አብሮን ነው::ለኔ አንባቢው አዲስ ነው ወሊሶና ወልቂጤን እንጂ ይህን ቦታ በሙያ ስንዘዋወርም ረግጬው አላውቅም::ወሊሶ ስንደርስ የቅንጅት ጽ/ቤት አባላት ተቀበሉን ስለመሸ ማደር ነበረብንና በቀጥታ ወደመኝታ ወይም ሆቴላችን ከመሄድ ተብሎ በወሊሶ የቅስቀሳ ቡድን አባል አማካይነት ሜጋፎን ተጠምዶ ቅስቀሳው ቀጠለ::በኦሮምኛ በአማርኛ ተደጋጋሚ ማስታወቂያ ተላለፈ::አንዳርጋቸው ጽጌ ሜጋፎኑን ተቀብሎ «የጉበኞች ቀን ጠለቀች፤ሕዝብን በቀነ ቀጠሮ የሚያጉላሉ ዳኞች ጀንበር ጠለቀች፤በሕዝብ ላይ ያላገጡ የወያኔ ባለሥልጣናት ጀንበር ጠለቀች፤የሕዝብ ቀን የነጻነትና የፍትሕ ጮራ ይፈነጥቃል፤ቁንዶሚኖ!!» በማለት የወልቂጤን ከተማ በቅስቀሳ የቁም ስቅሏን አሳየናት ሕዝቡም አብሮን ሆ አለ::በዚሁ እለት ከመቀሌ ዩኒቨርሲቲ ተባረው የመጡ የቅንጅትን ደጋፊዎችን አግኝተን የልብ የልባችንን ተጨዋወትን::ይህን ጨርሰን ወደ ሆቴላችን ስንመለስ ጄኔራለ፤ ተስፋዬና ጄኔራል ወልደ ሥላሴ በረካን አገኘናቸው::አመጣጣቸው ለተመሳሳይ ጉዳይ ነበር::በተለይም ዶ/ር ያዕቆብን በምርጫው ለመደገፍ ነበር የመጡትና በሆቴሉ ግቢ ውስጥ አብረን አመሸን::ጀግናው ጄኔራል ተስፋዬ ያን እለት ነው መጽሐፉን ፈርሞ የሰጠን::በአጋጣሚ «ዘግሬት ሪቤሊዮን» የተባለው የኩባ ፊልም ላይ እኔ ጄኔራል ተስፋዬን ወክዬ ነበር የሰራሁትና ስለሱም አንስተን ተጨዋወትን ወልቂጤ አድረን በበነገታው ወደ ወራደዎቹ ገባን::በወረዳው ያደረግነውን ውይይት

ማጠቃለል ስላልተቻለ ሚያዝያ 29 ለመመለስ ቃል ገብተን ወደ አዲስ አበባ ተጓዝን:: በአዲስ አበባ መከናወን የነበረበትን ስብሰባና እንዲሁም አንዳንድ ዝግጅቶች እያደረግን በየወረዳው ስብሰባ እንዲፈቀድልን እየጠየቅን ጊዜው አለፈ ከጊዜው ማለፍ ጋር የተከናወነም ያልተሳካም የተደናቀፈም ነበር::ሂደታችን ግን አልቆመም ሚያዝያ 29 ደረሰ::

## ሚያዝያ 29

በዚህ እለት ዶ/ር ብርሃኑና እኔ ወልቂጤ በተዘጋጀው የቅንጅቱ ሕዝባዊ ስብሰባ ላይ መገኘት ስለነበረብን ወደዚያ ስንሄድ ሊዎንችናና አውቶቡስ ለጉድ ይከንፍ ነበር::የዚያን እለቱን ሁኔታ እኛ ለማየት አልቻልንም፣ ወሬ እንኳን ለመስማት ሞባይል ስለማይሰራ አልሆነልንም፣ ቢሆንም ሃሳብ አልገባንም:: ወልቂጤ ስንደርስ የጣት ሰላምታው ተዥጎደጎደ እልልታው አገሩን አተራመሰው:: ወደ ስብሰባው አዳራሽ ስንገባ ታቦት የገባ ያህል አዳራሹ ተናወጠ::

በስብሰባው ላይ ዘር፣ ብሔር ሳይል ሁሉም ነው የተገኘው::ዕድሜና ጾታ አልለየም::አዳራሹ ጠቦ ሜዳው ሁሉ ሰው በሰው ላይ ተደራርቧል::በአዳራሹ ውስጥ ያሉትን ወጣቶች ለቀሙት ሴቶችና ሽማግሌዎች ቦታ እንዲለቁ ተደርጎ ስብሰባው ቀጠለ::በቅድሚያ አንድ ወጣት ግሩም ግጥም አቅርቦ ወደ ውይይቱ ገባን::በውይይቱ ላይ በቅድሚያ እጁን ያወጣው የኢህአዴግ ካድሬ መሆኑን ለማወቅ የተቻለው በአዳራሹ የነበረው ሕዝብ «ይህ ስብሰባ የቅንጅት እንጂ የወያኔ/ኢህአዴግ አይደለምና ውጣልን» ሲሉት ነው::

ዶ/ር ብርሃኑ «ይህ አካሄድ ዴሞክራሲያዊ ስላልሆነ ሃሳቡን ማድመጥ አለብን፤ አለበለዚያ እኛም ፀረ ዴሞክራሲ መሆናችን ነው» በማለት እንዲጠይቅ አደረገ:: ግለሰቡ ያነሳው ጥያቄ፣ «እናንተ በሃገራችን ላይ ኢንተርሃምዌይን ልታመጡብን የተነሳችሁ ናችሁ፤ ስለዚህ ምን መልስ አላችሁ?" የሚል ነው:: በምላሹ



የቀረበለት ጥያቄ «ለኛም፣ ለህብረተሰቡም ግልጽ እንዲሆን ኢንተርሃምዌይ ምን እንደሆነ ብታስረዳን» የሚል ሆነ:: ጠያቂው፣ «እኔ ጠያቂ እንጂ ለማስተማር አይደለም የመጣሁት» በማለት ሊወጣ ሲል « አትወጣም! መልሳችንን ሰምተህ ትወጣለህ» ብለነው ዕድሉ ለኔ ተሰጠኝ::

« አንተ ኢንተርሃምዌይ የሚለውን ቃል ሲነገርህ ተቀብለህ የመጣህ እንጂ ምን እንደሆነ አታውቀውም:: ዛሬ ግን እንድታውቀው ማብራሪያ እንስጥህ:: ኢንተርሃምዌይ በሩዋንዳ ገዢው መንግሥት በዘር ላይ በተመሰረተ ጥላቻ ሕዝቡን በመከፋፈልና አንዱን የሌላው ጠላት በማድረግ፣ ያውም ባልታጠቀና ምንም መሳሪያ በሌለው ሕዝብ ላይ ያደረሰው እልቂት ነው:: እኛ መሳሪያ የለንም፣ በስልጣንም ላይ አይደለንም:: በዚህ መታማት ካለበት የሚታማው የናንተ ድርጅት ነው» ብዬ ጨረስኩ:: በአዳራሹ የነበረው ሕዝብ በሙሉ ሰውየውን አይንህ ላፈር አለው::

ስብሰባው ቀጥሎ፣ በርካታ ጥያቄዎች ተነስተው፣ መልስ ተሰጥቶባቸውና ውይይት ተካሂዶባቸው ስብሰባው በሰላምና በመግባባት ተጠናቀቀ:: ስብሰባውን ጨርሰን ስንወጣ የኢህአዴግ አባላትና ደጋፊዎች የሞሉት አውቶቡስ ወደ አዲስ አበባ ለሰልፍ ሊሄድ ተነስቶ ባጋጠመው የመኪና ብልሽት ከአዳራሹ ፊት ለፊት ቆሞ ነበር:: ከውስጥ የንብ ካናቴራ የለበሱት እነኚህ የኢህአዴግ ደጋፊዎች ከኛ ስብሰባ የሚወጡትን፤ የቅንጅትን ምልክት ጣታቸውን ወደ ታች እየዘቀዘቁ ለማናደድ በመሞከራቸው ትንሽ ችግር ሊፈጠር ነበር እኛ ነገሩን አቀዘቀዝንና ተለያየን::

በዚያ አውቶቡስ ውስጥ ባሉት መሃልም ሌላ ችግር ተፈጠረ:: "ቅንጅትን አትንኩ" ብንነካስ ምን ለመሆን?" በሚለው ቡድን መሃል አለመግባባት ተፈጥሮ "አትንኩ" የሚለው ያየለ በመሆኑ "ብንነካስ" ባዮች አውቶቡሱን ጥለው ለአቤቱታ ሄዱ:: አውቶቡሱ ደግሞ ጥሏቸው መንገዱን ቀጠለና ከሳሾች ሜዳ ላይ ቀሩ::

አሁን የምንሄድበትን አካባቢ ጨርሶ ረግጬው አላውቅም::እዣ የሚባል የጉራጌ አካባቢ ነው::መንገድ አለው፣ ግን ጠጠር መንገድ ነው:: ቤቶቹ ሁሉ ባህላዊ ናቸው::ሕብረተሰቡ ባህሉን የሚያከብር መሆኑ ከሚታየው ሁኔታ ይታወቃል::አለባበሳቸው፤ጸጉር አሰራራቸው፤ ሰላምታ ልውውጣቸው፤ ሁለመናቸው በባህላቸው መሰረት ነው::

አካባቢው ለም ነው፤ህዝቡም ሰራተኛ፣ ጥሮ ግሮ አዳሪ ነው::ይህን ደግሞ ቀደም ብዬም የማውቀው ነው::የሥራ ምልክት ጉራጌ መሆኑ በሁሉም ዘንድ የሚታመን ነው::የጉራጌ ልጅ የሚለምን ማየት የጀመርኩት በቅርብ ሲሆን፣ ያውም ጥቂት ነው:: መራመድ ሲጀምር ራሱን እንዲችል ቤተሰቡ ይመራዋል:: ይህን ነው የማውቀው::

እዣ አገና ስንደርስ በሃገሩ ባህል መሰረት የተደረገልን አቀባበል፣ ቅንጅት ምን ያህል የሕዝብ ፍቅር እንዳገኘ በግልፅ ያሳየን ነበር:: በየመንገዱ ያሉት ሕጻናት ሲያዩን ሰላምታ የሚሰጡን በቅንጅት የምርጫ ምልክት ነው:: ሴቱ ወንዱ ሁሉም ወደስብሰባው ሜዳ በመሄድ ላይ ነው::በአካባቢው ሃይለኛ ዝናም እየጣለ በመሆኑ ከፊሉ ጃንጥላውን ይዞ ባለበት ሜዳው ላይ ሲጠብቅ፣ ገሚሱ ወደቤቱ ሄዶ ነበርና፣ "መጡ" ሲባል በጣም ሃይለኛ ዝናም ቢጥልም፣ ሕዝቡ በዝናቡ ሳይሸነፍ፣ እኛም ለዝናቡ እጅ ሳንሰጥ ደርሰን ስብሰባችንን ቀጠልን:: በዚህ ጉዞ ላይ ዓለማየሁ ፋንቱ፤ ወርቅነህና አንዳርጋቸው ጽጌ ከኛ ጋር ነበሩ::ዝናሙ አላቆምም ቢልም የጀመርነውን ሳንጨርስ አንሄድም በማለት ከሕዝቡ ጋር ዝናቡንም ስብሰባችንንም አጠናቀቅን:: በዚህ ስብሰባ ላይ አንድ የእድሜ ባለጸጋ የሆኑ የአካባቢው ተወላጅ፣ «እያችሁ ልጆቼ! በዚህ መንደር እያንዳንዱ ነዋሪ በጓሮው ጎመን፣ በጮጮው ወተትና እርጎ፣ በጓዳው ትንሽም ቢሆን ስጋ አያጣም ነበር::





አሁን ያ ቀርቶ ከገበያ ለሚገዛውም እርዳታ ድጎማ አስፈልጎታል::ችግር ገብቶታል:: ጊዜ አያሳየው የለም፣ በዚህ እድሜዬ አይተን የማናውቀውን የጉራጌ ለማኝ አየን» አሉ፣ እንባቸው እንዳቀረረ:: መስማት ያለብንን ሰምተን ተመርቀን፣ «ከዚህ ችግር አውጡን፣ አንድነት ፍጠሩ! ፍቅር ያሳድርባችሁ፤ ቃላችሁን የምትጠብቁ እንድትሆኑ አምላክ ይርዳችሁ! ያ ካልሆነ እንደመረጥናችሁ አናወርዳችኋለን:: ምረጧቸው እንዳልን ጥሏቸው፣ አግልሏቸው እንልባችኋለን:: እግዚአብሔር ከናንተ ጋር ይሁን:: ደህና ግቡ::» ብለውን ጉዟችን ወደ አዲስ አበባ ሆነ::

በመልሳችን ወልቂጤ ለቡና ስንቆም በጠዋቱ የመምህራን ስብሰባ ላይ የነበሩ መምህራን እናነጋግራችሁ ብለው ጠዋት ስለነበረው ስብሰባ አጫወቱን:: በስብሰባው ላይ ኢህአዴግ መምህራን በምርጫው ከጎኑ እንዲቆሙ፣ እስካሁን ምላሽ ያላገኙ ጥያቄዎቻቸውም እንደሚፈቱ ቢነገርም፤ መምህራኑ፣ "አሁን ከረፈደ በኋላ ለምን ወደማይሆን ጉዳይ እንገባለን? 14 ዓመታት ያልተመለሰን ጥያቄ አሁን መመለስ ለምን አስፈለገ? በጣም ረፍዷልና ተዉን::" በማለት ስብሰባው እንደተበተነ አጫወቱን:: ይህን ሰምተን መምህራኑን አመስግነንና አይዟችሁ ብለን መንገዳችንን ወደ አዲስ አበባ ቀጠልን::

ከወልቂጣ ወጣ እንዳልን ዝናሙ እየከበደ መንዳት እስከማስቸገር ደረሰ፡፡ ብርሃኑና ወርቅዬ እየተፈራረቁ ቀስ ብለን በመንዝ አዲስ አበባ ለመድረስ ጥቂት ኪሎ ሜትር ሲቀረን፣ ሞባይል መስራት ስለጀመረ ስለሰልፉ ለማወቅ ስልክ መደወል ጀመርኩ፡፡ ዶ/ር ብርሃኑም መኪናውን አብሮን ለነበረው ወርቅነህ ሰጥቶ ስለነበር መደወል ያዘ፡፡ በመጀመሪያ ያገኘሁት ዜና "ብዙ ሰው ነበር፣ ግን የሚገርመው ተሰላፊው ወደሰልፍም ሲሄድ፣ ሲመለስም የቅንጅትን የምርጫ ምልክት እያሳየ፣ ሆ! እያለ ነበር" የሚል ሆነ፡፡

ይህ ማመን የሚያስቸግር ሁኔታ በመሆኑና፣ "የኢህአዴግ ካድሬዎች በከበቡበት ሁኔታ እንዴት ይሆናል?" በሚል ጥርጣሬ ደጋግሜ እተለያየ ቦታ ደወልኩ፡፡ ያው ነው ያገኘሁት መልስ፡፡አሁን ደሞ ሌላ የሚያሳስብ ነገር መጣብኝ፡፡ "ሚያዝያ 29 ሰልፍ የወጣና ሲደክም የዋለ ሕዝብ እንደገና እንዴት ለቅንጅት በ30 ይወጣል? ሕዝቡ ወያኔ/ኢህአዴግ በሚፈጥረው ረብሻ አደጋ ሊፈጠር ይችላል በሚል መንፈስስ ለመውጣት አያመነታም ወይ?" የሚለው ሃሳብ ወዘወዘኝ፡፡ አዲስ አበባ ገብተን ብርሃኑ ቤት ስንደርስ የሰልፉ ሪፖርት በቴሌቪዥን ይታያል ጠቅላይ ሚኒስትሩ በደስታ ራሳቸውን ስተዋል፤ የታዘዙትና ግዴታ የተጣለባቸው ሰልፈኞች ሳያምኑበት ስለወጡ፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር «ይህን ማዕበል የሆነ ድጋፍ ማንም ምንም ሊያደርገው አይችልም» ነበር ንግግራቸው፡፡ እውነትም ብዙ ሰው ነበር በግዴታም፣ በቀን ወጪም፣ በማስፈራራትም የወጣ፡፡ ቤቴ ገብቼ ስለሁኔታው ከባለቤቴ ጋር ስንነጋገር ባለቤቴ፣ «ምንም አታስብ ማስታወቂያውን መንግሥት ሰርቶላችኋል፡፡ ሕዝቡ በግዴታ ነው የወጣው፡፡ ያንን ብድር ለመመለስ ነገ ተነቅሎ ይወጣል» አለችኝ፡፡ ሁልጊዜ ግምቷ ልክ ስለሆነ አመንኳት፡፡ ግን ቢደክመኝም እንቅልፍ አልወሰደኝም፡፡ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ላይ ስለቀኑ ውሎ ባለስልጣናት አስተያየት ይሰጣሉ፡፡



አቶ ሕላዊ ዮሴፍ በቢሯቸው ውስጥ፣ ሕዝቡ ለኢህአዴግ ስላለው ፍቅርና ስለወጣው ሕዝብ ብዛት በደስታ ፈንድቀው ነው የሚናገሩት፡፡ እንደአባባላቸው፣ ነገ በቅንጅት ሰልፍ ላይ 100ም ሰው አይገኝም፡፡ የንግግራቸው ጥንካሬ አሳሰበኝ፡፡

# እንደፈርዖን ጦር የወያኔ ድጋፍ ሰልፍ በቅንጅት ሱናሚ ተዋጠ

## ሚያዝያ 30

አይነጋ የለም ነጋ፡፡ ከቤቴ ሁለት ሰአት ላይ ወጣሁ፤ ወደ ቢሮ፡፡ ቢሮ አካባቢ ብዙ ሰው አለ፡፡ "ካናቴራ እንግዛ፤ ባንዲራ ስጡን፤ መፈክር እንያዝ" የሚል፡፡ እኛ ደግሞ ካናቴራ የለንምና እንደደረስኩ ያገኘሁት መፍትሔ የምርጫ ምልክታችንን ጣት በፎቶ ኮፒ አባዝቶ ማደል ነበር፡፡ ሕዝቡ ደግሞ በቡድን አንዳንድ ስጡንና እናባዛዋለን በሚል ቀና ትብብር አፋጠነልን፡፡

በ3ሰአት ከ30 መስቀል አደባባይ ስደርስ ሕዝቡ መግባት ጀምሯል፡፡ ይደረግ እንደነበረው የመስቀል አደባባይ ለትራፊክ አልተዘጋም፤የቀይ መስቀል በዓልም ነበርና ሲያልቅ መብራቱ ጠፋ፤መብራት ሃይል ለመደወልና ትራፊክ ለማዘጋት ወዲያ ወዲህ ስል 4:30 ሆነ፡፡ አደባባዩ ሞልቶ መንገዱን ያለትራፊክ ትዕዛዝ የሕዝብ ናዳ ዘጋው፡፡ ትላንት ጎርፍ የተባለው ወደ ጅረትነት ተለውጦ የዛሬው ሰልፍ የሱናሚ ማዕበል ሆነ፤ያውም ስነስርአት የሞላው፡፡ መብራቶች እንዳይሰበሩ ስርአት እንዳይጣስ ሕዝቡ እርስ በርሱ ኮሚቴ ፈጥሮ ተደላድሏል፤ ተሰላፊም ጠባቂም ሆኗል፡፡

መስቀል አደባባይ ስንቱን ሕዝባዊ ስብሰባ በኩራት ያላስተናገደውን ያህል ዛሬ ምጥ ያዘው፡፡ ጠጠር መጣያ ጠፋ፡፡ ስአቱ 5:00 ስአት ነው፣ ገና ስብሰባው

**ለ8 ሰአት ነው የተጠራው:: ቦታው ከአሁኑ ሞልቷል::**



ለጥበቃ የተመደቡት የፖሊስ አባላት የሕዝቡን ስነ ስርአት ጠባቂነት ሲያዩ ዘወር አሉ:: ሕዝቡ እንደጎርፍ ገና መንገድ ላይ ነው:: ሰልፉ ሜክሲኮ ቆሟል፤ባምቢስ ከትሟል፤ ከቦሌ አቅጣጫ የሚመጣው ከሳይ ኬክ ቤት ማለፍ አልቻለም፤ ከደብረዘይት መንገድ የተመመው ገቢዎች ሚኒስቴርን አላለፈም፣ መንገዱ ሁሉ ሕዝብ ነው:: ከሱሉልታ የነቀለው ከ1000 በላይ ፈረሰኛ አዲስ አበባ መግቢያ ላይ በካድሬዎች እንዳይገባ ታግዶ ቆሟል::

**የ**ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በጉጉት ሲጠብቁትና የሕዝብ አካል መሆናቸውንና፤ ኢህአዴግ የኔ ናቸው በማለት የነዛው የሃሰት ፕሮፓጋንዳ የፈጠራ ወሬ መሆኑን ለራሱ ለኢህአዴግም የሚያረጋግጡበት ስለነበር ዝግጅታቸውን ጨርሰው መንገድ ሲጀምሩ ከግቢው እንዳይወጡ በሆድ አዳሪዎችና አሾክሻኪዎች፤ በጆሮ ጠቢ ካድሬ ተማሪዎች ጥቆማ ወድሮ ይጠብቅ በነበረ የስለላ ቡድን ታገዱ::

ተማሪዎቹ ቆራጥ ናቸውና ለዓላማቸው በመቆም የልቀቁን ክርክራቸውን ትግል ቀጠሉ:: ሁኔታው አላምር ያላቸው የስለላ ቡድን አባላት ጉዳዩን ለበላዮቻቸው



በማስረዳት የ"ልቀቁ" ትዕዛዝ በመሰጠቱ በትግላቸው እግዱን አስነስተው እራሳቸው ያዘጋጁትን <u>«የቅንጅት ደጋፊዎች የአዲስ አበባ ዩኒቬርሲቲ ተማሪዎች»</u> የሚል ቅስት ይዘው ከዩኒቨርሲቲ እስከ መስቀል አደባባይ ሆ እያሉ በሕዝብ ታጅበው ወደ አደባባዩ ሲገቡ ያጋጠማቸውን የጉልበተኛነት እገዳ ሕዝቡ ሰምቶ ስለነበር የጀግና አቀባበል አደረገላቸው::እውነትም ቆራጥ የሕዝብ ወገኖች!!

አዲስ አበባ በማታውቀው የሕዝብ ውቅያኖስ ተጥለቀልቃ ተጨነቀች:: ዜማው ሁሉ፣ ዘፈኑ ሁሉ "ነፃነት፤ ቅንጅት" ሆነ:: የምርጫው ቀን ገና የሚጠበቅ ቢሆንም ሚያዝያ 30/1977 ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነቱን በይፋ፤ለውጥ ፈላጊ መሆኑን በአደባባይ አወጀ:: መስቀል አደባባይ ጠጠር መጣያ ቦታ ጠፋ::



እስከ ሚያዝያ 29/1997ዓ የወያኔ ኢህአዴግ ሰልፍ ድረስ በትዕዛዝና በግዴታ፣ በድጎማ፤ ሰልፍ ይወጣ የነበረ ሕዝብ፤ "ሰልፍ ካልወጣህ ዋ!" እየተባለ ማስጠንቀቂያና ማስፈራርያን በመፍራት እሺ ይል የነበረ ሕዝብ፤ ከጃንሆይ የመብት ጥያቄን አለማንሳት፤ ከደርግ የመብት ጥያቄ ማንሳትና መታሰርን፤ ከወያኔ ኢህአዴግ የመብት ጥያቄን ማንሳትን በቁምና በአካል መሞትን በመሸሽ ዝም ይል የነበረና ብሶትና ቁጭቱን "በእህህ!"

ብቻ ይወጣ የነበረ ሕዝብ፣ ዛሬ ያንን ሁሉ አራግፎ ጥሎ በአዲስ የነጻነት ስሜት፤ በአዲስ ወኔ፤ በአዲስ የመብት ማስከበር አንድነት ነቅሎ ወጥቶ፤ መስቀል አደባባይንም፤ ወያኔ/ኢህአዴግንም፤ አይተውት የማያውቁትን፤ ያልጠረጠሩትን፤ ይሆናል ብለው ያላሰቡትን ጭንቀት እንካችሁ አላቸው። ትላንትም ታየ፣ ዛሬ ግን የተለየ ሆነ።

የሚያዝያ 29ኙ ማዕበል በሚያዝያ 30ው ሱናሚ ተዋጠ። በሕዝቡ ብዛት ያስከትላል ተብሎ የታሰበው መጥፎ ድርጊት ሁሉ አልታየም። ያ ሁሉ ሕዝብ ስነስርአቱ፣ ጨዋነቱ፣ እንግዳ አክባሪነቱ ፖሊሶቹ ሲመጡም አቀባበሉ፣ ምንም እንከን የማይወጣለት እጹብ ድንቅ ብቻ ሊባል የሚችል ሆኖ ሁሉንም አስገረመ፤ ሌላውንም አሳፈረ። ከሚያስፈልገው በላይ ታጥቀው የመጡት የፖሊስ አባላት ሁኔታውንና ሥነስርአቱን ሲያዩ የነሱ በዚያ ግድም መሆን ጥቅሙ ስላልታያቸው ቀስ ብለው ወደ ሌላ ቦታ ሄዱ። ከዚያ በኋላ የሚታዩት በየፎቁ ጣርያ ላይ ሆነው አንዳንድ ጊዜ የኛን ቪዲዮ አንሺዎች ሲያባርሩና ከፎቅ ሲያስወርዱ ነበር።

ለደንቡ ይህን መሳይ ዝግጅት በመስቀል አደባባይ ሲኖር ትራፊክ መዘጋት ቢኖርበትም፣ በዚህ እለት ግን አልተዘጋም። እርግጥ ጠዋት የቀይ መስቀል ዓመታዊ በአል ይከበር ስለነበር ያ ፕሮግራም እስኪያልቅ ብቻ ተዘግቶ ወዲያው ሲያበቃ ተከፈተ።ከዚሁ ጋር በተመሳሳይ ሙዚቃና ንግግር ይኖራል ተብሎ ተነግሮ ስለነበር መብራት ኃይልም ከቀይ መስቀል በዓል ጋር አብሮ ነው የተዘጋው።ሕዝቡ ግን መብራት ቢጠፋ ባይጠፋ ጉዳዩ ከመብራት ጋር ሳይሆን ከቅንጅት ጋር ስለነበር ደንታም አልሰጠው፣ ጭርሱንም ትዝ አላለው።

ያ ሕዝብ በዚያን እለት ያሳየው ጨዋነት ለታሪክ ሲነገር፣ ሲወሳ ሲተረክ የሚኖር ታሪካዊ ሁኔታ ነው።ሕዝቡ እንደ ጎርፍ ከየአቅጣጫው ሲጎርፍ እየዘመረና እየተደሰተ፣ ለበለጠ ደስታ ወደ ሜዳው ሲገባ መስቀል አደባባይ ምን ይዋጣት? ወያኔ ኢህአዴግስ ምን



ይሁን? ትላንት በግዳጅና በማስፈራሪያ ለጠ/ሚኒስትር የቀረበላቸውን የሕዝብ ስብሰባ ስጦታ እንደ ጉድ፣ እንደ ልዩ ታሪክ ታይቶ የነበረውን ሁኔታ ይሄኛው እንዳልነበረ አድርጎ ሲጨፈልቀው ምድር ቀውጢ ሆነች።መስቀል አደባባይ ቦታ አልቆባት ውሰት አማራት። ሰአቱ እየተቃረበ ሲመጣ የድምጽ ማስተላለፊያውን ወደ ቦታው ለማስገባት በሕዝብ መጨናነቅ የተነሳ ችግር ተፈጠረ። በስንት ቅብብሎሽና ችግር ደረሰ። ያም ሆኖ ከመድረኩ አካባቢ ውጪ ድምፅ ማጉያውን ወስዶ ለማስቀመጥ በጭራሽ የማይቻል ሆነ። ሰአቱ በመድረሱ "መቀመጥ አለበት ሕዝቡን ትብብር እንጠይቅ" ቢባልም የሚደረገው ንግግርም ሆነ የሚቀርበው ሙዚቃ ኦሎምፒያ ወይም ባምቢስ አለያም ሜክሲኮ ያለውን ሕዝብ በሌላ አቅጣጫም የሚገኘውን ሊያዳርስ ስለማይችል ባለው የድምጽ ማጉያ በዚያው በመስቀል አደባባይ ያለውንና ማጉያው የቻለውን ያህል ማድረስ የሚል ውሳኔ ላይ ደረስኩና በማማከር በዚሁ ተወሰነ።

ስምንት ሰአት ሲሆን የቅንጅቱ ሊቀ መንበር ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል፤የቅንጅቱ አባል ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም፣ የሕዝብ ግንኙነት ሃላፊው አቶ ልደቱ አያሌው፣ ዕጩ ተወዳዳሪ አቶ በድሩ አደም በየተራ ወደ መድረኩ መጡ። በቅድሚያ ኢንጅነር ሃይሉ ሲመጡ እግራቸው መሬት ሳይነካ በሕዝብ ሸክም ማለት ይቻላል ወደ መድረኩ ሲያመሩ እልልታውና ጭብጨባው ቀለጠ ልደቱ ሲመጣ ለየት ባለ ሁኔታ ነበር። በፒክአፕ መኪና ላይ ባንዲራ ለብሶ በአካባቢው ልጆች ታጅቦ ልደቱ! ልደቱ! እየተባለ ከመኪናው አናት ላይ ሆኖ ነው የመጣው።

በዚያ አደባባይ ውስጥ ሕዝብ ከጫፍ እስከ ጫፍ ሞልቶ ተትረፍርፎ ባለበት ሁኔታ፣ እንኳን መኪና ሰውም ለመግባት እጅግ ተቸግሮ በተጨናነቀበት ጊዜ፡ ማንም መኪና ይዞ እንዳይመጣ እየተደወለ ተነግሮ ነበር። መኪናም ያመጣና መንገድ የጀመረ ካለ መኪናውን ራቅ አድርጎ በማቆም በግሩ ቢመጣ እንደሚሻልና

ለመኪና ማቆሚያ ቦታ እንደማይኖር እየተነገረ ባለበት ሰአት፣ መልእክቱ ቢደርሰውም በተለየ አለባበስ ባንዲራችንን አንገቱ ላይ አጣፍቶ ከሩቅ



ቦግ ብሎ በሚታይ ሁኔታ ልደቱ መጣ ::

ልደቱ እንዲህ ሆኖ ሲገባ የፈራነው ነገር ቢኖር ምናልባት በግርግር መሃል አንድ ችግር ቢደርስበትስ ብለን ነበር:: ግን ምንም አልተፈጠረም፤ልደቱም የፈለገውን አደረገ:: ከልደቱ በቀር በመኪና ጫፍ ላይ ሆኖ ታጅቦ ፊት ለፊት "እዩኝ! እዩኝ!" እያለ የገባ አንድም የቅንጅት ሰው የለም::

ፕሮፌሰር መስፍን ሲደርሱ ታጅበው መንገድ እየተለቀቀላቸው ታቦት የገባ ያህል እልልታው፣ ጭብጨባው፣ "አበጀህ የኛ ሎጋ!" እየተባለላቸው፣ የሕዝብ አክብሮትና ፍቅር ታድሏቸው፣ በሕዝብ መሃል እንደማንም ተሳታፊ ሆነው መድረኩ ላይ ደረሱ:: እነዚህ የሕዝብን ልብ ለማሸነፍ የበቁት የቅንጅት አመራሮች ሕዝብን ከምንም በላይ አድርገው ስለሚያከብሩና ለህዝብም ስለቆሙ በየደረሱበት ሕዝቡ ራሱ ጠባቂ፣ ራሱ አጃቢ፣ ራሱ ተንከባካቢ ሆኖ ነው የሚያስተናግዳቸው እንጂ አደጋ ቢደርስብን ብለው አስበው፣ ተጠራጥረው አያውቁም:: ለምን ይጠራጠራሉ? ለሕዝብ ከበሬታና ፍቅር ሰጥተን



የምንቀበል ተጠሪነታችን ለሕዝብ እንጂ ለሥላጣናችን ባለመሆኑ የምንፈራበት አንዳችም ሰበብ የለንም:: ይህን የሕዝብ ፍቅር፤ አመኔታ፤ አክብሮት በጥንቃቄና በንቃት ካልጠበቅነውና አደራ በላ ሆነን ከተገኘን ያቀፈንን፣ የወደደንን ያህል አንቅሮ ሲተፋን መድረሻ እናጣለንና ልናስብበት የሚገባን ጉዳይ ነው::

"መች ይሆን የኢህአዴግ ባለስልጣናት እንዲህ አይነት የሕዝብ ክብር፣ የሕዝብ ፍቅር፤የሕዝብ ተቀባይነት የሚያገኙት? መች ይሆን ያለምንም የሕዝብ ፍራቻ በሕዝብ ታጅበው፤በሕዝብ ተከበው፤ በሕዝብ መሃል ፍቅር ተቸሯቸው ለመታየት የሚበቁት?" የሚል ጥያቄ መጣብኝና እኔው መለስኩት:: ቅንጅት ተመርጦ ወያኔ/ኢህአዴጎችን ነፃ ሲያወጣ ነው ይህን እድል የሚያገኙት አልኩት፣ እኔ ለኔ::

በመድረኩ ላይ ለሙዚቀኞች የተዘጋጀውን ቦታ ጋዜጠኞች አጨናንቀውት ስለነበር ሙዚቀኞቹ አስተናጋጅ ሆነው ቦታ እየለቀቁ ያስተናግዳሉ:: ዳምጠው የውዝዋዜ ባለሙያው ነበርና ሙዚቀኞቹን ያቀናጀው፣ የሚያየው ሁሉ አስገርሞት ጥግ ይዞ ሳያውቀው ያለቅሳል:: በደስታ እሱን አይቼ ሲገርመኝ አንድ እድሜያቸው የጠና እመቤት ጠጋ ብለውኝ «አቶ ደበበ ስታለቅስ ሳይህ ዛሬ ሁለተኛ ጊዜ ነው፤ አንድ ጊዜ በመድረክ ላይ በሙያህ፤ ዛሬ ደሞ ለሕዝብ» አሉኝና በነጠላቸው እንባዬንም፣ ላቤንም ጠረጉልኝ:: የሚገርመው የእውነትም ያለቀስኩት ሳላውቀው ነበር:: ያንን የሕዝብ ጎርፍ ሳይና ፍቅሩን ሲገልጽ በደስታ ነበር የማነባው፤ ሳላውቀው:: ባለቤቴ ትላንት መንግስት ማስታወቂያውን ሰርቶላችኋል ያለችው እውነት ሆነ::ያውም ከግምታችን በላይ::

የተባለው ስምንት ሰአት በመድረሱ ፕሮግራማችንን መጀመር ግዴታ ነውና ኢንጅነር ሃይሉ ሻውልን ለንግግር ከመጋበዜ በፊት እንደመክፈቻ አድርጌ በቅድሚያ «ዛሬ ሚያዝያ 30 ቀን የአዲስ አበባና አካባቢው ነዋሪ ሕዝብ ነጻነቱን አውጇልና እንኳን ደስ ያለን! ታግታችሁ የነበራችሁና ያንን አሸንፋችሁ

የተቀላቀላችሁን የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችም ሕዝባዊነታችሁን አስመስክራችኋልና የምስራች እላለሁ!» በማለት ኢንጅነር ሃይሉ ሻውልን ለንግግር ጋበዝኩ::

እስካሁን ድረስ ዶ/ብርሃኑ አልመጣም:: እርግጥ ለተመሳሳይ ሕዝባዊ ስብሰባ በሌሊት ከአዲስ አበባ ውጪ እንደሚሄድ ቢነግረኝም፣ ስድስት ሰአት እንደሚመለስ ቃል ገብቶልኝ ነበርና "የት ገባ? ሞባይል ችግር ነበረበት:: ቢሰራስ በዚያ ቦታ እንዴት መነጋገር ይቻላል?" ያም ሆነ ይህ ኢንጅነር ንግግር ሲጀምሩ ያ ሁሉ ሕዝብ ፀጥ ረጭ ብሎ ማዳመጥና ማጨብጨብ ጀመረ:: ያ ሁሉ ሕዝብ አደባባዩን ሞልቶት ኢንጅነር ሲናገሩ አንድ ሰው ብቻውን ሜዳው ውስጥ የሚያወራ ያህል ነበር ጸጥታው:: በዚህ ሰአት ዶ/ር ብርሃኑ ድንገት ቢመጣ ምን አይነት ሁኔታ ሊፈጠር እንደሚችልና በእልልታና በጭብጨባ፤ "ብርሃኑ!ብርሃኑ!" በሚል አቀባበል ንግግሩ ሊቋረጥ እንደሚችል ስጋት ያዘኝ:: ኢንጅነር ጨረሱ::

ቀጣዩ ተናጋሪ የተከበሩ አቶ በድሩ አደም ነበሩ:: አቶ በድሩ በንግግራቸው ላይ "ወያኔ/ኢህአዴግ በዚህ ምርጫ ተሸንፎ ወደ መጣበት ይመለሳል" አሉ:: ያ ደሞ ትክክለኛው ትርጉም የወያኔ ሹማምንት ተራ ሰዎች ሆነው ክቡር ጌታና ቀዳማዊት እመቤትነት ይቀራል ለማለት ነው:: በማታው የቴሌቪዥን ፕሮግራም ላይ ሲቀርብ ግን በብሔር ጥላቻ መልኩ ተተርጉሞና የትግራይን ቆራጥ ሕዝብ በሙሉ የወያኔ/ኢህአዴግ አባል አድርጎ በዘረኝነት መንፈስ አቀረበው:: አቶ በድሩ እንደጨረሱ ልደቱ የበኩሉን ስሜትና የምርጫውን ሂደት በዛሬው ያየው መሆኑን በማስረገጥ ደመደመ:: ጭብጨባው ቀለጠ:: በዚህ ሁኔታ እንዳለን ወያኔ ኢህአዴግ ይህን ሰላማዊና ስነስርአት የተሞላበትን ስብሰባ የሚያበላሹ ቅጥረኞቹ የሚገቡት ሰአት በ11:00 ሰአት እንደሆነ ጥቆማ ስለደረሰን ተዘጋጅቶ የነበረውን ሙዚቃ በማጠፍ ፕሮግራሙ ማብቃቱን ይፋ ከማድረጋችን መብራት ኃይል መብራቱን ለቀቀ:: ሕዝባዊ ትብብር መሆኑ ነው? ከዚህ ጋር ደሞ ዝናቡ



በመምጣቱ ሕዝቡ መበተን ጀምሮ ሳለ በመብራቱ መምጣትተመለሰ:: የዝናቡ ሃይለኛነት ሕዝቡን ሳይበግረው ሙዚቃ አለመኖሩን አውቆ



የድምጽ ማጉያውም በመነሳቱ በቡድን በቡድን ሆኖ ወደየቤቱ አመራ:: ይህም ሁኔታ ማታ በቴሌቪዥን ፕሮግራማችን እንደተቋረጠ ሆኖ ቀረበ:: የተቋረጠው የቅንጅት ፕሮግራም ሳይሆን የረብሻ ፈጣሪዎች የቅጥረኞች ኘሮግራም ነበር::

በመጨረሻው ከዶ/ር ብርሃኑ ጋር በስልክ ተገናኘ ን:: "ምነው?" አልኩት:: የደረሰበትን ነገረኝ:: በሰአቱ ተመልሶ ወደ መስቀል አደባባይ ሲመጣ ሰልፉ ሜክሲኮ ላይ ደርሷል፤ አይንቀሳቀስም:: ወዲያው ሕዝቡ ሲያየው መኪናውን አስቁሞ ብርሃኑን ከመኪናው አውጥቶ «ዶ/ር! መስቀል አደባባይ ብዙዎች ደርሰዋል አንተ ከኛ ጋር ሁን» በማለት ተሸክመውት ሲጨፍሩ ነው በሕዝብ ፍላጎት ተውጦ የቀረው:: ነፃ የሆነ የሕዝብ ወገን የትም መቼም ከሕዝብ አይሸሽግም:: ከሕዝብ ጋር ነውና ምንም ችግር ሳይገጥመው በዚያው የበዓሉ መጠናቀቅ ስለታወቀ ብርሃኑም ወደ ቤቱ ታጅቦ በሽክም ተመለሰ::መኪናውን ሌላ ሰው ነው የወሰደለት::

በማግስቱ እንዳየሁት ደስታና ቁጭት የተቀላቀለበት ስሜት ነበር በብርሃኑ ላይ ያየሁት:: ቁጭቱ ያንን መስቀል አደባባይ የታየውን ጉድ አለማየቱ

ነው:: ግን በቴሌቪዥንና በተቀረፀው ቪድዮ ተፅናና፣ በሕዝብ ትከሻ ላይ የዋለበት ደስታ ግን እስከመቼም ከልቡ የማይጠፋ ሆነ:: ለካ ደስታም ያስለቅሳል፣ ቅጥ ያሳጣል፣ የብዙዎቻችን ስሜት ያ ነበር::

በዚህ ታሪካዊ እለት የታክሲ አሽከርካሪዎች ያደረጉት አስተዋፅኦ መቼም ቢሆን የማይረሳ ታላቅ ውለታ ነው:: መንገዱ ተዘጋግቶ፤አውቶቡሶች አገልግሎት አቋመው ባለበት ሁኔታ ታክሲ አሽከርካሪዎ-ች ከአራቱም ማእዘን ሕብረተሰቡን በነፃ በማመላለስ ታላቅ አስተዋፅኦ አድርገዋል:: በታክሲ ላይ ተሳፍሮ የነፃ አገልግሎት የሚጠየቀው ዋጋ ሁለት ጣትን በማንሳት ሰላምታ መስጠት ብቻ ነበር::ያን እለት በዚህ ተግባር ላይ የዋሉ ሁሉ በታሪክ ሊመዘገቡ የሚገባቸው ባለውለታዎች ናቸው::

የመስቀል አደባባይን ስንከራይ (በኋላ ግን ገንዘቡ ተምልሶልን በነፃ ሁኗል)፣ አሳስቦኝ የነበረው ጉዳይ እነዚያ የከተማ ውበት የሆኑት መብራቶች በቀላሉ ሊሰበሩ ይችላሉ የሚል ነበር::እንደደረስኩም በድምፅ ማጉያ ሕብረተሰቡን አደራ ስሰጠው የዚህንም መብራት ጉዳይ ባካተተ መልኩ ነበር:: ሕብረተሰቡ ገብቶታልና ተሰላፊም፣ ጠባቂም፣ አሰተናጋጅም ሆኖ አንድም መብራት ሳይሰበር፤አንድም የተተከለ አትክልት ሳይረገጥ፣ በደፈናው አንዳችም ጥፋት ሳይፈፀም ጨዋ ሕዝብ በጨዋነት ተግባሩን አጠናቆ ወደ ቤቱ "ሆ"! እያለ ተመለሰ::

ዝናቡ ሲጀምርና በዓሉም እንደተጠናቀቀ ከተነገረ በኋላ ሁሉም ሄደው እኔ ብቻ ነበርኩና የቀረሁት፣ ከመድረክ ወርጄ መንገድ ስጀምር ያየ ሁሉ አጅቦኝ በመጨፈር አብሮኝ ጉዞ ሲጀምር ተመልሼ መድረክ ላይ ወጣሁ አጀብ አብዝቶ መሄዱን አልፈለኩትም ነበር:: ችግሬ የገባቸው ቀስ ብለው አሾልከው ካስወጡኝ በኋላ መጀመሪያ ያገኙትን መኪና አስቁመው አስገቡኝ ያን እለት የጓደኛዬ ልጅ ሰርግ ስለነበር ቤተሰቤ ቦሌ ኤር ፖርት ሞቴል ነበርና ወደዚያ ከመሄድም፣ እነሱንም ወደመስቀል አደባባይ ከማምጣትም ብዬ ባለመኪናውን



ታክሲ ወደማገኝበት እንዲያደርሰኝ ጠየቅሁት:: ባለመኪናው፣ "በጭራሽ አይደረግም! ቤትህ ነው የማደርስህ" ብሎ "አሻፈረኝ" አለ፤ "ቤቴ ሩቅ ነው" ብለውም፣ "ለምን የፈለገው አይሆንም" ብሎ ቤቴ ድረስ አደረሰኝ:: እስከዛሬም ድረስ እየተደዋወልን የምንጠያየቅ ወዳጆች ሆነናል::

ሚያዝያ 30 ታምር ይህ ብቻ አይደለም፤በዚያ ጭንቅንቅ ውስጥ እቃ ጠፍቶ ማግኘት ጨርሶ የማይታሰብ ጉዳይ ነው የሚመስለው፤በዚያን እለት ግን አልሆነም:: ወድቀው የተገኙ ስድስት የሞባይል ቀፎዎች መጥተው በድምፅ ማጉያ ተነግሮ ባለቤቶቹ ወስደዋል:: ሞባይሉን ያገኙት ወስደውት ቢሆን ማን ይወቅሳቸው ነበር? ሕሊናቸውን ስለከበደውና በዕለቱ ላይ ማንም መጥፎ ስሜት እንዳይኖረው በማሰብ ያደረጉት ነው:: ሞባይሉን ካመጡት አንዱ ወጣት «ጋሽ ደበበ! እኔ ሥራ የለኝም፣ ገንዘብ የለኝም:: ይህንን ብሸጠው ለጊዜው ይጠቅመኝ ነበር፤ ግን በቅንጅት ሰልፍ ላይ ሞባይሌን ተበላሁ ስለሚባል የቅንጅት ስም በአጉል እንዲነሳ በዓሉም እንዲወቀስ አልፈልግምና ለባለቤቶቹ ስጡልኝ» ብሎ አስገረመኝ::ሁሉም ሃላፊነት የተሰማቸው ናቸውና ሊመሰገኑ ይገባል::

ማታ በመንግስት የመገናኛ ብዙሃን ስለሕዝባዊ ስብሰባው ዘገባ ሲቀርብ የኢህአዴግን ደጋፊዎች ሁሉ የሚያሳዝን ሆነ:: አንድ ሕፃን ልጅ እድሜው ከ14 ዓመት ያልበለጠ፣ «አላሙዲን ሌባ» በማለት በአደባባይ ያሰማውን ስሜቱን በቴሌቪዥን ሃገር ሁሉ እንዲሰማው አደረጉ:: በአደባባይ ሲባል የሰማው ቁጥር ቢበዛ አካባቢው ከነበሩ አያልፍም ነበር:: ያውም በዚያ ጭንቅንቅ ውስጥ መደማመጥ ከተቻለ ነው:: ያንን መተዉ የሼህ አላሙዲንን ክብር አይነካም ነበር:: ቴሌቪዥን ግን በግላጭ ሕዝብ እንዲሰማው አደረገና ከሕፃኑ በከፋ መልኩ ሰድቦ ለሰዳቢ ሰጣቸው::

ሌላው ደሞ ጠቅላይ ሚኒስትር ባንዲራውን "ጨርቅ ነው!" ያሉትን በተምሳሌት ባንዲራችንን ሜዳ

ላይ አንጥፎ ጨርቅ ተባለብን ለማለት ያቀረበውን ወጣት፣ ባንዲራውን እንደደፈረ አይነትና ኢህአዴግ ለባንዲራው ተቆርቋሪ እንደሆነ ተደርጐ ቀረበ። ሕዝቡ ግን ለምን በዚያ መልኩ እንደቀረበ ተረድቶ «ደሞ ከመቼ ወዲህ ኢህአዴግ ለባንዲራው ይቆረቆር ጀመር » አለ።ይጠቅማል ተብሎ ያን እለት የቀረበው ሁሉ አልጠቀመም።ይልቅስ መሳቂያ መሳለቂያ ሆኖ አረፈው። የሕዝቡን ቁጥር ለማሳነስ የቴሌቪዥን ካሜራ በአደባባይ ባዶ ቦታ በመፈለግ ያጠፋው ጊዜ ቀላል አልነበረም፣ ግን ባዶ ቦታ ከየት ይምጣ? ባዶ ቦታ በሽ በሽ የነበረው በቅዳሜው ሰልፍ ነበር።

ከሕይወቱ በላይ ቅድሚያ በመስጠት ከጎናችን የቆመው ወንድማችን፤ "ኬ" በማለት የምንጠራው፤ የወሎን የህዝባዊ ስብሰባ ሙሉ ወጪ ያችንን የሸፈነልን፤ በገንዘቡ ብዙ ቀዳዳችን የደፈነልን የቁርጥ ቀን የቅንጅት ደጋፊና ኢትዮጵያዊ፤ታሞ ሆስፒታል ነበር። ይህን ሕዝባዊ ስብሰባ ካላየሁ አልድንም ብሎ በስንት ችግርና ማግባባት በቤተሰብ ልመና ነው አርፎ እንዲተኛ ያደረግነው። መተኛት አይባልም፣ በሆስፒታል ቅጥር ግቢ መዋል ብንለው ይሻላል። ለክፋቱ ደሞ የሞባይል ግንኙነት ተቋረጠና እህ የሚልበት መንገድ አልነበረም። ሁኔታውን ለማወቅና እፎይ ለማለት ሾፌሩን ከመስቀል አደባባይ ሆስፒታል፣ ከሆስፒታል መስቀል አደባባይ በማመላለስ የየደቂቃ ሪፖርት ለመሰብሰብ ቢሞክርም በመሃሉ የሕዝቡ ቁጥር መንገዱን ሁሉ ስለዘጋበት ያም ተቋረጠ።

"ምነው ይህ በሽታ ከሰልፉ በኋላ በሆነ ኖሮ" ብሎ ምሬት ያዘው። በመጨረሻ ማታ ሁኔታውን በቴሌቪዥን ሲያየው፣ በሪፖርተሩ ዘገባ የወጣውን ሕዝብ ትላንት ከወጣው ቁጥር እንዳይበልጥ ተደርጎ ቢቀርብም፣ ኬን ግን አንጀቱን የሚያርስ እልል የሚያሰኝ ስሜት ፈጠረበትና ሳያውቀው በደስታ አለቀሰ። ኬ ውጪ ሄዶ እንዲታከም ሃኪሞች ቢነግሩትም "ይህን ሳላይና ምርጫ ሳልመርጥ ንቅንቅ አልልም፣ አሻፈረኝ" ብሎ ነበር የቆየው። የምርጫው እለት የሃኪምም ትእዛዝ ጥሶ፤ የቤተሰብ ምክርም እምቢ



ብሎ፤ የጓደኞቹን ልመናም አልሰማም ብሎ አንዲት ድምፅ ብዙ ዋጋ አላት በሚል ቁርጠኝነት፣ እውነትም ሰልፉ ፈውስ አስገኘለት መሰል፣ በሌሊት ሄዶ መርጦ እፎይ አለ። የቅንጅት አመራር አባላት፣ "ያንተ ደህንነት ነው እንጂ የሚጠቅመን በመታመምና ከዚያም ላለፈ ሁኔታ መዳረግ ይጎዳናል፣ እባክህ ሂድና ታከም" ብለው ቢማጸኑትም አልሰማም ብሎ እምቢ አለ። አሁን ድምጽም ሰጠ፣ ሰልፉንም አየ፣ ውጤቱንም አወቀና ለመሄድ ተዘጋጀ። የቅንጅቱ አመራር አባላት በደህና ጤናውን ይዞ እንዲመለስ ተመኙለት። ድጋፉ ብዙ ነውና "ብዙ ዕድሜ ይስጠው" እያልን ነው። "ኬ ያደረግኸው ሁሉ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነውና እንመካብሃለን" አልነው።

ሕዝብ ያላንዳች ተፅእኖና ግዴታ ባመነበትና በቆመለት፤የኔ ብሎ በተቀበለው የነገና የዘላቂ ሕይወቱ ነፃነት፣ ሰብአዊና የዴሞክራሲያዊ መብቱ ማረጋገጫ ቀን፤ ብሎ ያን በመሰለ በሰከነ አካሄድ፤ የሰለጠነ ስነ ስርአት፤በኢህአዴግ ካምፕ በማይታወቅ ኢትዮጵያዊ ጨዋነት፤ማንነቱንና ምንነቱን አሳየ።ለዓለም ሕዝብ አስመሰከረ።

ኢህአዴግ ምንም ይበል ምንም፣ ስለ ቁጥሩም ያሻውን ቁጥር ይጥቀስ፣ ይህ ሕዝባዊ ስብሰባ ግን የሚያዝያ 29ኙን ሰልፍ እንደፈርያን ሠራዊት የዋጠ ነበር።

የቅንጅት አመራሮች ቅስቀሳ በወጡበትና ከሕዝብ ጋር ባደረጉዋቸው ስብሰባዎች ሁሉ ሕዝቡን ሲሉት የነበረው ኢህአዴግ ገንዘቡን ሲሰጣችሁ የናንተው ነውና ተቀበሉት፣ በምርጫው ወቅት ግን ካርዳችሁን የሕይወት ጉዳይ ስለሆነ ለማን እንደምትሰጡ አስቡ፤ ይበጀናል የተሻለ አስተዳደር ያስፍናል፣ ቃሉን ቢያጥፍ ውረድ እንለዋለን የምትሉትን ፓርቲ ምረጡ። እኛን ብቻ ምረጡ አንልም፤ ካመናችሁበት ኢህአዴግንም ቢሆን በነጻ፤ ያለፍርሃት ከሆነ ምረጡት፤በፍርሃት ግን ማንኛውንም ፓርቲ አትምረጡ፤ ሲሉ ስለነበር ሕዝቡ

አመዛዝኖ ሁኔታውን ከህልውናው ጋር መክሮበት የሚበጀውን ለመምረጥ ወሰነ። በምርጫው ቀን ደሞ በዚያች ቅንጅት "ከስከድ ሚሳይል የበለጠ ሃይል አላት" በሚላት የምርጫ ካርድ ሊቀጣው ተዘጋጅቶ ቀኑን በጉጉት መጠባበቅ ያዘ።

## የፓርቲና፣የመንግሥት፣መገናኛ ብዙሃን

አበው ሲተርቱ «ቀበጡን ጅብ በላት መዝጊያዋን አውሳ»፣ ወይም «የቀበጡ ዕለት ሞት አይገኝም» ይላሉ። ለወያኔ ኢህአዴግ ሲስተካከል ግን «አይቀብጡ ቅብጠት ለመዘረር በቅንጅት» ተብሏል።

ቅንጅት የመገናኛ ብዙሃንን በሚገባ ለመጠቀም አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት በማድረግ በቴሌቪዥን በተሰጠን 6 ደቂቃ በሬዲዮም ላለን 13 ደቂቃ ዕቅድ አውጥተን ተያያዝነው። ኢህአዴግ ሚዲያው በጁ ነው፣ዋልታ ሪፖርት ይሰራል፣ፋና ሙሉ ጊዝውን መድቧል፣አዲስ ዘመንና ሄራልድም ገፆቻቸውን አዘጋጅተዋል። እኛም ያለችንን የምጽዋት ሰአት ይዘናል። ወያኔ ኢህአዴግ የመገናኛ ብዙሃን ቅስቀሳውን ሲጀምር በክስ፣ ግለሰቦችን በመጥቀስ የስም ማጥፋት ዘመቻ በማካሄድ ነበር መነሻ ያደረገው። ሕዝቡ ይሰማዋል እንጂ ከቁጥር አላስገባውም። የሚባለው ሁሉ አልጥምህ ያለው ገና ከጅምሩ ነው። እኛና ሕዝቡ ደሞ በጣሙን ተግባብተናል። ከእኛ ምን እንደሚጠበቅ አውቀናል። የሚፈልገውን ብቻ ሳይሆን የሕዝቡን ሰቆቃና ችግር፣ብሶቱን በሚገባ አጢነን ነበር ያመቻቸንለት።

አንዱን ለምሳሌ ያህል እንመልከት:

በየክልሉ ለወያኔ ኢህአዴግ ባላቸው ታማኝነትና ትዕዛዝ ተቀባይነት የአመራሩን ቦታ የያዙት የወያኔ ኢህአዴግ ካድሬዎች፣ ከላይ ከአለቆቻቸው በወረደላቸው መመሪያ መሰረት እንከን የሌለው ተብሎ ቃል የተገባለትን ምርጫ በተለመደው የወያኔ "በሬ ወለደ"



ፕሮፓጋንዳ በቅንጅታችን ላይ ዘመቻ ለማካሄድ ዝግጅታቸውን አጠናቀዋል። አንድ ቀን በደሴ ከተማ በከንቲባው ፅ/ቤት በተካሄደው ስብሰባ በቅንጅቱ ላይ መጥፎ ፕሮፓጋንዳ የሚያናፍሱ ታማኞች ተሰብስበው መመሪያ እንደተሰጣቸውና የመንቀሳቀሻ በጀትም ከሕዝብ ከተሰበሰበው ገንዘብ እንደተመደበላቸው በስብሰባው ከነበሩ ደጋፊያችን ተነግሮናል።

በዚያው ጊዜ በድሬዳዋ፣ ካውንስል መሰብሰቢያ አዳራሽ፣ ከፍተኛ የኢህአዴግ ባለስልጣናትና የቀበሌ ሹማምንት ተመሳሳይ የሆነ ስብሰባ አካሂደው የሚከተለው ውሳኔ ተላልፏል:-

### የትኩረት አቅጣጫዎች

ለወጣትና ለሴቶች ማሕበራት፣ ቁጠባና ብድር ለወሰዱ ሰዎችና አዲስ ለሚሰጣቸው ለሃይማኖት መሪዎች፣ ለችግረኞች ድጎማ መስጠት ለመምህራንና ለምድር ባቡር ሠራኞችና መሪዎች፣ ለድሬዳዋ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ሠራተኛ ማሕበር መሪዎች፣ በተለይ ያኮረፉ ሰዎች፣ ማለትም የቀድሞው መንግሥት ሠራተኞች በሚኖሩባቸውና በብዛት በሚገኙባቸው ቀበሌዎች 02፣ 03፣ 04፣ 05፣ 06፣ በካቢኔ አባላት አማካይነት ጭምር ቅስቀሳ ማድረግ። በ02 ሳቢያን ከሥራ የተባረሩ የቀድሞ ጦር አባላት ያሉበት ስለሆነ ጥንቃቄ የተሞላበት የፖለቲካ ሥራ መሥራት ከመሃከላቸውም «ተመልምለን የምንጠብቅ የቅንጅት ወታደሮች ነን» የሚሉ መመልመልና ለፕሮፓጋንዳ ሥራ መጠቀም። በ03 የምድር ባቡር ሠራተኞች ያሉበት ስለሆነ ችግራቸው እንደሚፈታ በመግለፅ ከፍተኛ የፖለቲካ ስራ መስራት በ04 (ከዚራ) የቅንጅት አባሎችና ደጋፊዎቻቸው በስፋት የሚንቀሳቀሱበት ስለሆነ የደህንነት ሃይሎች ጥብቅ ክትትል እንዲያደርጉባቸው።

‘የልማቱም ሆነ የቁጠባና ብድር አሁን መጀመሩ የሕብረተሰቡን ችግር የሚፈታ አይደለም፣ የምረጡኝ ዘመቻ መደለያ ነው’ በማለት የቅንጅት አባሎች ደጋፊ

ለማሰባሰብ ቤት ለቤት የቅስቀሳ ሥራውን ተያይዘውታል፤ እኛን በእርግጥ ቀድመውናል:: ይህን ለመምታትም ከፍተኛ ሥራ ያስፈልጋል:: ለዚህ አንዱ መሳሪያ ‘ቅንጅት ለውድድር ያቀረበው ሰው ጡረታ የወጣ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም’ በማለት ማጥላላት ነው:: የድሬዳዋ ተማሪዎች ድጋፋቸውን ለቅንጅት እየሰጡ እንደሆን ታይቷል:: ስለዚህ ተማሪዎችን ለመያዝ አስተማሪዎችን በመሰብሰብ የቅንጅት አቅጣጫ ጥሩ እንዳልሆነ በማሳመን በጥብቅ መንገር ነው:: በአጠቃላይ ድሬዳዋ የሚገኘው የመንግሥት ሰራተኛ ደመወዝ ከመንግስት እየበላ ልቡን ለቅንጅት ያደረገበት ጉዳይ የሚያሳስብ ነውና መፈተሽ አለበት:: ጎበዝ! በመጨረሻው ከምንም በላይ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ ቅንጅት ቢያሸንፍ ለእኛ ለአመራሮች ከፍተኛ ችግር መሆኑ ነው:: ቅንጅት ሲያሸንፍ የራሱን አባሎችና ደጋፊዎችን በኛ ቦታ ስለሚያስቀምጥ አሁን የምናገኘውን ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም ከየትም አናመጣውም:: ስለዚህ ለራሳችን ህልውና መታገል አለብን:: ለገጠር ቀበሌዎች ስኳር፤ ስንዴ፣ በግ ማስራጨቱ ይቀጥል:: የእድር ማሕበራት ቤተሰቦቻቸውን እንዲያስመዘግቡ፤ ተማሪዎች ኢህአዴግን ከመረጡ የስኮላርሽፕ እድል የሚሰጥ መሆኑን መንገርና ማሳመን ፎርም ማስሞላት፤ የስንዴ እርዳታ የቅስቀሳ መጠቀሚያችን ይሁኑ::" የሚሉ ናቸው::

ይህ የቅስቀሳ ዘመቻ ከ15/8/97 ጀምሮ በካድሬዎችና በድርጅቱ አባላት፣ ከ17/8/97 ጀምሮ ተመሳሳይ ስብሰባ በሐረር - በጅጅጋና - በሂርና እንዲካሄድ ተወስኖ ስብሰባው ተጠናቋል:: ይህ ነው እንከን የለሽ ይሆናል ተብሎ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ቃል የተገባው የምርጫ ሂደት::

ወያኔ ኢህአዴግን የሚመሩት ግለሰቦችና በከፍተኛ የመንግስት ስልጣን በሃላፊነት ደረጃ ያስቀመጧቸው ጀሌዎቻቸው፣ ሺህ ጊዜ ቢፍጨረጨሩ፣ ቅንጅቱ በዝርዝር ያስቀመጣቸውን አማራጭ ፖሊሲዎች



በጥልቀትና በብቃት መመከት የሚችል አማራጭ ፖሊሲ ማቅረብ እንደማይቸሉ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ግልፅ ሆነ::

ፖሊሲዎቻችንም በከተማውና በገጠሩ ሕዝብ ድጋፍ እያገኙ ሲመጡ ቅንጅት አማራጭ የለውም በማለት ብዙ የቀባጠረው ወያኔ/ኢህአዴግ ማጣፊያው አጠረበት:: ፖሊሲን በፖሊሲ አሸንፎ፣ ሕዝብ ፊት ተቀባይነት አግኝቶ በምርጫ ውድድር እንደማያሸንፍ ሲያውቀው እራሱ ተሸብሮ ሕዝብን ማሸበር ዋነኛው ዓላማ አድርጎ መንቀሳቀስ ጀምሯል::

## <u>ቅንጅት ስለወታደሩ</u>

በሃገራችን ውስጥ የሕዝብ ደም በከንቱ የፈሰሰባቸው የሰቆቃ ታሪኮች በፊልም መረጃ ተቀርፀው በማስታወቂያ ሚኒስቴር እጅ የሌሉ ይመስል ሩዋንዳ ድረስ ተጉዞ በየመንገዱ የወደቀ የሰው እሬሳ ክምር እያሳየ፣ "ተቃዋሚዎች ቢያሸንፉ ይህ ነው የሚጠብቃችሁ" እያለ ተሸብሮ ሊያሸብረን ጣረ::

የወያኔ ኢህአዴግ መንግሥት፣ በቴሌቪዥን እየደጋገመ የሚያሳየንን የሩዋንዳን እልቂት የፈፀሙት ስልጣናችሁን አካፍሉ የሚል ፈተና የገጠማቸው የመንግሥት ባለስልጣናት ናቸው:: በሚያዙት የጦር ሃይልና በዘረኛ ቅስቀሳ ተነሳስተው ምንም መከላከያ በሌላቸው ንፁሃን የሃገሪቱ ዜጎች ላይ የዘመቱት እነዚህ የመንግሥት ባለስልጣናት ናቸው:: ወያኔ ኢህአዴግ ህዝብን ማሸበር እንኳን ቢፈልግ ለምን እንዲህ ዓይነቱን የሽብር ፕሮፓጋንዳ እንደሚያሰራጭ ለእኛ ለሃገሬው ህዝቦች ብቻ ሳይሆን ለውጭ ታዛቢዎችም ግራ አጋቢ፤ "ስልጣኔን ከተፈታተናችሁ የሩዋንዳ አረመኔ ገዢዎች በሰላማዊ ሕዝብ ላይ እንደዘመቱት፣እዘምትባችኋለሁ"የሚል ካልሆነ፤ሌላ ምን ትርጉም ይኖረዋል?ይህስ ከሆነ ህጋዊ እና ሰላማዊ በሆነ መንገድ ለመወዳደር ፈቃደኛ ነኝ ተብሎ መቀላመድ መጀመርያውኑ ለምን አስፈለገ?

ወያኔ ኢህአዴግ አንድ ያልገባው ወይም ገብቶት ግን ለመቀበል ፈቃደኛ ያልሆነበት ጉዳይ፣ ከኢትዮጵያ ሕዝብ አብራክ የወጣው መከላከያ፣ የፖሊስና የፀጥታ ሐይል በህገመንግስቱ ላይ እንደሰፈረው የሕዝብና የሃገር ጠባቂና ባለአደራ እንጂ የግለሰብ ወይም የአንድ ቡድን ጦር አለመሆኑን ነው:: ለቡድን ሥልጣን ብሎ በቆመለትና ወገኑ በሆነው ሕዝብ ላይ ግፍ ለመፈፀም ፈቃደኛ እንዳልሆነ አምኖ መቀበል ነው ያቃተው::

ኢህአዴግ የመከላከያ፣ የፖሊስና የፀጥታ ኃይሉ በህገ መንግሥቱ ላይ እንደተቀመጠው ለሃገር ሉአላዊነት፣ ለሕዝብ ደህንነትና ሰላም የቆመ፣ የሕዝብ ውሳኔ ተግባራዊ መሆኑን የሚያረጋግጥ እንጂ፤በግድና ከሕዝብ ፈቃድና ምርጫ ውጪ የሚሞከርን የስልጣን ቅሚያ ተግባራዊ ለማድረግ የቆመ ጦር አለመሆኑን መረዳት ነው ያቃተው::

የኢትዮጵያ የመከላከያ፣ የፖሊስና የፀጥታ ሃይል ግን ለምንና ለማን መቆም እንዳለበት ባግባቡ ያወቀ ነውና የሕዝብ ወገን፣ የህዝብ መከታ፣ የሃገር አለኝታ መሆኑን፤የገባውም ቃል ኪዳን ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ መሆኑን ስለምናምን እንተማመንበታለን:: ጦሩን፣ የፖሊስ ሃይሉን የፀጥታ ተቋሙን ለመበተን ኢህአዴግ መሆንን ይጠይቃል:: እኛ ደግሞ ቅንጅት ነንና ከመከላከያው፣ ከፖሊስ ሃይሉና ከፀጥታው ተቋም ጋር ለሃገርና ለሕዝብ ልእልና አብረን እንቆማለን:: ከመበተንና ከማፈናቀል የሚገኘው ድህነት ነውና አንበትንም፣ አናፈናቅልም:: ዕውነታው ማኒፌስቷችንም፣ መመርያችንም የሚመሰክረው ይሄንኑ ነው::

ይህ ገዢው/ፓርቲ ቅንጅትን ኢንተርሃምዌይ ነው ላለውና ስለጦሩ ያቀረብነው ፕሮግራም ነው::

ሌላው ወያኔ ኢህአዴግ ላቀረበው መሰረተ ቢስ የወሬ ናዳ ቅንጅት የሰጠው መልስና በአንድ ቦዘኔ ተብሎ ቅንጅትን በመደገፉ ፍዳውን የበላውን  የህግ እስረኛ ቃለ መጠይቅ ያቀረብንበት የቴሌቪዥን ፕሮግራም ነበር::



ገዢው/ፓርቲ እንከን የለሽ ምርጫ ለማድረግ አስፈላጊውን ሁሉ እናደርጋለን በማለት ለኢትዮጵያ ሕዝብ የገባውንና በቀን 3 ጊዜ የሚደጋግመውን የምርጫ ሂደት እንደ ይሁዳ ዶሮም ሳይጮህ ቃሉን እያጠፈ ነው:: አደገኛ ቦዘኔ ተብሎ ወህኒ ከወረደ በኋላ ሚያዝያ 3/97 ፍርድ ቤት "ነፃ" ብሎ የለቀቀው አንድ የአካል ጉዳተኛ ላይ የቅንጅት ደጋፊ ተብሎ የደረሰበት የግርፋት ኢሰብአዊ ድርጊት አንደኛው እንከን የለሽ የምርጫ ሂደት ነው::

በአዲስ አበባ የሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ጠ/ሚኒስትሩ ወጣቱን በትምህርት ጉዳይ ላይ ለማነጋገር ስለሚፈልጉ ወኪል ላኩ ተባሉ:: ተመርጠው የተላኩት ተማሪዎች መሰብሰቢያ አዳራሽ ሲገቡ ከተማሪው ውጪ በሚስጥር ከየቀበሌው ባላቸው ታማኝነት ተጠርተውና ጠ/ሚኒስትሩን የሚጠይቁትም 14 ጥያቄ ተዘጋጅቶ ተሰጥቷቸው የሚጠባበቁ ነበሩ:: ጠ/ሚኒስትሩ ወደ አዳራሹ ሲገቡ አብዛኛው ወጣት የማያውቀውን ሚስጥራዊ ሰላምታ 'በአዲስ አበባ የምትገኙ የኢህአዴግ ደጋፊ  ወጣቶች እንኳን ደህና መጣችሁ' በማለት ነበር በኢህአዴግ ሊቀ መንበርነታቸው አግባብተው፤ በጠ/ሚኒስትርነታቸው ወደ ሚቀጥለው አጀንዳ የገቡት:: 'ጠ/ሚኒስትሩ ስለትምህርት ጉዳይ ሊያነጋጋሯችሁ ነው' ተብሎ ተጠርቶ የነበረውን ወጣት ኢህአዴግን ምረጥ ማለቱ ነው እንከን የለሽ? ጠንካራ ተቃዋሚ የለም ሲባል የነበረው አሁን ደሞ ተለውጦ ጥሩ ተቃዋሚ የለም ማለት ተይዟል:: ጠንካራው ሲመጣ ጥሩ የማይሆንበት፤ሕዝብን ወክሎ፤ የሕዝብ ወገን ሆኖ፤ የሕዝብን ምሬትና ሰቆቃ ለማስወገድ በመንቀሳቀሱና አቋመ ጠንካራ አይበገሬ በመሆኑ ነው:: ጥሩ የማይሆንበትም በኢህአዴግ አምሳል ተቀርፆ በስመ ተቃዋሚ ዝም ብሎ የሚንቀሳቀስና አቋሙ የኢህአዴግ፣ ዓላማው የኢህአዴግ ሁለንተናው ኢህአዴጋዊ አለመሆኑ ነው::

በሃይማኖት ውስጥ መንግሥት አይገባም የሚለውን የሚያፈርሰው ደሞ ባለፈው ዕሁድ

የሙስሊሙን ሕብረተሰብ አባላት የትንሳኤ እለት በስብሰባ ማዕከል <u>የጥሪው ወረቀት እንዳይለይ</u> በሚል የቁጥጥር መሳሪያ ስብሰባ ተጠርተው ኢህአዴግን ምረጡ የሚል ተማፅኖና ምክር ሲሰጥ ነበር፡፡ ሌላው እንከን የለሽ ሂደት፡፡

ጠቅላላው የአዲስ አበባ ነዋሪ በቀበሌዎች አስገዳጅ ጥሪ እንዲወጣና ተቃዋሚዎችን እንዲቃወም፣ መመሪያና ትዕዛዝ በመስጠት፤ ‘ባትወጣ ወየውልህ’ እየተባለ ጥሪ ተደርጎለት በማያምንበት እንዲወጣ እየታመሰ ነው፡፡ ይህም እንከን የለሽ የተባለው ምርጫ ሂደት ነው፡፡

አቃቂ ቁጥራቸው ከ300 የማያንሱ የጋሪ ባለንብረቶችና አሽከርካሪዎችም በሐሙሱ የተቃውሞ ሰልፍ እንዲወጡ፣ ባይወጡ እያንዳንዱ የ30 ብር መቀጫ እንደሚጣልበት ማስጠንቀቂያ ደርሶታል፡፡ ደሞ ሌላው እንከን የለሽ ሂደት፡፡

ደርግ የሕዝብ ድጋፍ ኖሮት አያውቅም፡፡ግን ሁል ጊዜ ሕዝቡን በቀበሌዎችና በካድሬዎች ማስፈራራት ሰልፍ ያስወጣ፣ ለራሱ ንግግርም ያስጨበጭብ፣ ማታም በመገናኛ ብዙሃን ‘ሰፊው ሕዝብ ሰልፍ ወጥቶ ተቃውሞውን አሰማ’ ይባልለት ነበር፡፡ ያንንም እንከን የለሽ ልንለው ነው፣ እንዳሁኑ እንከን የለሽ አባባል፡፡

ምናለ፣ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃ ውሳኔ ተገዢ ብንሆን? ሕዝቡ የሚያምነውን ያለምንም ተቀጥላ፤ ማስፈራሪያና ካርድ ግዢ፤ የቡና መግዣና የዶሮ መግዣ ድጎማና ማግባቢያ፤ በደካማ ጎኑ በችግሩ፤ በድህነቱ መንጠላጠልንና መብቱን ከማስረሳት ተቆጥበን ለነፃ ውሳኔው ተገዢ ብንሆን?

ምናለበት ችግሩን እያነሳን፤ ‘ከመረጥከን እናደርግልሃለን ካልመረጥከን ሃገራችን የእሬሳ ክምር



ይታይባታል’ በማለት ባናስፈራራው? ስልጣን ላይ ያለ መንግሥት ሕዝብን የማረጋጋት ሃላፊነት ሲኖርበት አሁን እየታየ ያለው የተገላቢጦሽ ነው፡፡ ይህ ደሞ ከመንግሥት የሚጠበቅ አይደለም፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከደርግ ሥርአት ብዙ የተማረው አለ፡፡ በተለይ ሰልፍ ውጣ ሲባል መውጣትንና የፍጆታ እቃዎችን ከቀበሌ የመግዛት ሰርቲፊኬት ማግኘትን ምንም ሳያምንበትና ብዙውን ጊዜ ምን እንደሆነም ሳይገባው በቀበሌ አብዮት ጥበቃ በመገደድ ሰላማዊ ሰልፍ ወጥቶ፤ አጨብጭቦ፤ "ተቃወመ" ተብሎ፤ ማታ እሱ ሰልፉ ላይ እንዳልነበረ በመገናኛ ብዙሃን እንደ አዲስ ሲቀርብለትም አይቷል፡፡ አሁንም ‘ለሐሙስ ሰልፍ ውጣ’ ሲባል ባይወጣ፤ በገዢው ኢህአዴግ ካድሬዎች ምን እንደሚደርስበት ስለሚያውቅ ይወጣል፡፡ ማታም በመገናኛ ብዙሃን በራሱ ፍላጎት` ወጣ ሲባልም ያዳምጣል፡፡ ተቃወመ ሲባልም ይሰማል፡፡ ያ ግን የምርጫ ውሳኔውን አያስለውጠውም እንዲያውም ለውሳኔው ፅናት፣ ጉልበትና እልህ ይሆነዋል፡፡

ምናለ ማስፈራራቱ፣ ዛቻው፣ ፉከራው፣ ‘እኔ ከሞትኩ...’ ባይነቱ ቀርቶ ለሃገራችንም፣ ለሕዝባችንም ታሪክ ብንሰራ? ምናለ የመግዛት ሥርአትን በምርጫ በማስወገድ ዓለምን በሚያስገርም መልኩ ለዴሞክራሲያዊ ምርጫ ተገዢ ብንሆን?ምናለ ሌላው ዓለም የአፍሪካ ምርጫ እያለ የሚስቅበትን በትክክለኛ እንከን የለሽ ምርጫ ብንለውጥበትና ብናስደነግጠው?

ለመሆኑ በወያኔ/ኢህአዴግ ሚዛን እንከን ያለውና እንከን የለሽ ልዩነቱ በምን ሲለካ ይሆን? እስከ አሁን ያለውን ሂደት በምንም መልኩ እንከን የለሽ ለማለት የሚቻል ቀርቶ የሚታሰብ እንዳልሆነ መላው የኢትዮጲያ ሕዝብ የሚያየው ነውና ያውቀዋል፡፡

የኢህአዴግ ካድሬዎች፣ ባለስልጣናትም፤ ናቸውና፤ ትናንሾቹ ካድሬዎች ደሞ በየቀበሌው፣ በየጉራንጉሩ ያሉ ናቸውና እንደ ፓርቲም እንደ መንግሥትም ሆነው ያዛሉ ያስፈራራሉ፤ ይዝታሉ፤ ይፎክራሉ። በዩኒቨርሲቲ የኢህአዴግ ካናቴራ በትእዛዝ ሲታደልና አብዛኛው ለመልበስ ፈቃደኛ ሳይሆን በማስገደድ እንዲለብስ ማድረጉና ካልለበሰ የሚደርስበት ጣጣ መብዛቱ፤ እንከን የለሽነት ነው? የቅንጅቱን አርማ በፈቃዳቸው በገንዘባቸው አሰርተው በመልበሳቸው መከራ፣ ፍዳ የሚወርድባቸውስ፣ እንከን የለሽነት ነው?የእንከን የለሽ ሚዛኑ በኢህአዴግ መስፈርት ምን እንደሆነ ግራ የገባው ጉዳይ ነው። ገዢው ፓርቲ አሁን በስልጣን ላይ ነውና 'አባቱ ዳኛ ልጁ ቀማኛ' አይነት ሂደት ሲያከናውን፤ ስብሰባ ያለምንም ችግር በየቦታው ሲጠራ፤ የምረጡኝ ካናቴራውን አስለብሶ በየቤተክርስቲያኑ ካድሬዎቹን ሲያስማራ፤የተቃዋሚ ፓርቲዎች ቅስቀሳ እንዳይደረግ በየመንገዱና መንደሩ ውስጥ በመንግሥት መኪና የተቃዋሚዎችን የኪራይ መኪና በመከተል ሲያደናቅፉ፤ የምረጡኝ ወረቀት የሚለጥፉትን ሲያሳድድ የሚጠይቀው አለመኖሩና እንደልቡ እንከን የለሽ ያለውን እንከን በእንከን ሲያደርግ ውሎ፤ ማታ በመገናኛ ብዙሃኑ 'እንከን የለሽ' ማለቱ ማንን ለማታለል ነው? ይህን ሁሉ ሕዝቡ ያያል፣ ይታዘባል።

በየክልሉ ያሉት የገዢው ፓርቲ ተሹዋሚዎች ሕዝቡን የግድ፣ያለፍላጎቱና በማያምንበት ሁኔታ 'ተቃወም ካልተቃወምክ መከራህን ትበላለህ' ነጋዴው የንግድ ፈቃድህን፤ ሠራተኛው ሥራህን፤ ሥራ የሌለውና ጡረታ ላይ ያለው ኑሮህን፤ ወጣቱ በቦዘኔ ስም ነፃነትህን፤ እየተባለ ሁሉም በየፈርጁ የማስፈራርያው ናዳ እየወረደበት ነው። ይሄም የእንከን የለሽ አንዱ ገፅታ ነው።

ተቃዋሚ ፓርቲዎች ምርጫውን 'እንከን የለሽ በሆነ፣ በሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ሂደት' ተብሎ ለሕዝብ



የተገባውን ቃል በማመን ለምርጫ ቢዘጋጁም ገዢው ፓርቲ የሚደርስባቸው እንከን በእንከን የሆነ ሂደት ተሰላችተውና ተመርረው ከምርጫው እራሳቸውን ያገላሉ' በሚል እምነት ጫና ቢያበዛባቸውም፣ እነሱ ግን የሕዝብን ድጋፍ አበረታችና ቆራጥ አቋም ጋሻና መከታቸው አድርገው ዘመቻውን በጀመሩት በሰለጠነው ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ሂደት ቀጥለውበታል።

ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ከጎኑ በቆራጥነት የተሰለፉትን ኢትዮጵያውያን ሁሉ፤ በቀረበላቸው ድጎማ ሳይሸነፉ ገንዘቡን በኪሳቸው፣ ምርጫውን በሆዳቸው የያዙትን፤ የሚደርስባቸውን መከራ ችለው ለቅንጅት ድል አድራጊነት በተለያየ የቅስቀሳ ሥራ ላይ የተባበሩትን፤ ቅንጅት ሥራ ነው፤ቅንጅት ፍቅር ነው፤ ቅንጅት አንድነት ነው፤ ቅንጅት ኢትዮጵያዊነት ነው በማለት የሚዘምሩትን የነገ ተተኪዎች ላደረጉለት ድጋፍና ትብብር ከልብ እያመሰገነ እንከኑን ሁሉ ችሎ ለድል እንደሚበቃና ለዚህም ብርታቱና ጥንካሬው ላለፉት 14 ዓመታት ግፍና መከራ የተጫነበት የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደሆነ እምነቱ ጠንካራ ነው።

ገዢው መንግሥት ያልገባውና ያልተረዳው የኢትዮጵያ ሕዝብ ቻይ ቢሆንም፤በቃኝ ሲል ደሞ ለውሳኔው ጠንካራነት ማረጋገጫው ለማድረግ የወሰነውን እንደማይቀለብስና በውሳኔው ጸንቶ እንደሚቆም ነው። ለ14 ዓመታት መከራና ስቃዩን፣ ውጣ ውረዱን ተሸክመን አብረን ኖረን፤ ሰብአዊነታችን ሲረገጥ ከዛሬ ነገ ይሻል ይሆናል በሚል ተስፋ በደርግ ስርአት ሲጨፍርብን የነበረውን አብዮታዊ ዴሞክራሲ ይለወጥ ይሆናል በሚል ቀቢጸ ተስፋ ስንናፍቅ፤እርስ በርስ የመናቆርን አባዜ ይቅር ስንል ሰሚ ማጣትን፣ በስህተት እንኳን ለኢትዮጵያ ማሰብ ይጀመር ስንል ሁሉ ችለን ኖርን። አሁን ግን መሸከም ሲያቅተን ሌላ አማራጭ ያስፈልገናል በማለት የተነሳንና የቆረጠን ሕዝብ፤የነፃነትን ጣዕም በመጠኑም ቢሆን የቀመሰን ሕዝብ ወደ ነበረበት መልሶ በሰለቸው መንገድ መግዛት አይቻልም።

ገዢው ፓርቲ ወያኔ/ኢህአዴግ፣ ደግሞ ደጋግሞ ማስፈራሪያ አድርጎ ሊጠቀምበት፤ በስሙ የሚነግደው በኢትዮጵያ የመከላከያ ሃይላችን፣ በፖሊስ ሰራዊታችን፤ በደህንነት ተቋማችን ነው:: እነሱ ደሞ በህገመንግሥቱ ላይ በግልፅ በሰፈረው መሰረት ሕብረብሔራዊ ሆነው ሃገርና ሕዝብን ለመጠበቅ ተቋቋሙ እንጂ ግለሰብን ወይም አንድ ድርጅትን ዘለዓለማዊ ገዢ አድርገው ሊያስቀምጡ አለመቋቋማቸውን የማያውቁት ይመስል፣ በስማቸው መጠቀም አግባብነት የለውም:: ቅንጅት፣ ተቋማቱ ለምን እንደቆሙ ለማወቃቸውና የሕዝብን ውሳኔም ተግባራዊ ለማድረግ፤ ምርጫውንም ነፃ፣ ፍትሃዊና ዴሞክራሲያዊ እንዲሆን ለኢትዮጵያ ሕዝብ የገቡትን ቃል እንደሚጠብቁ ቅንጣት ታህል ጥርጥር የለውም::

ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ የመከላከያ፣ የፖሊስና የደህንነት ተቋማትን በሚመለከት በማኒፌስቶው ላይ በግልፅ ያስቀመጠው (ማኒፌስቶ ገጽ 26):: ይህ ነው ትክክለኛው አሠራር:: ይህንንም ምርጫ እንከን የለሽ ለማድረግ ገዢው/ ፓርቲ ሊከተለው የሚገባ አካሄድ ይህ መሆን አለበት::


## ሕዝባዊ ስብሰባዎች

## አዲስ አበባ

የመጀመርያው ስብሰባ በአዲስ አበባ የተካሄደው በብሔራዊ ሎተሪ አዳራሽ ውስጥ ነበር:: ተሰብሳቢው ከሁሉም ብሔር ብሔረሰቦች፣ ሃይማኖቶች የተውጣጡ አባላት የተሳተፉበት ነበር:: ለቅንጅት ደሞ ኢትዮጵያ የብዙ ብሔር ብሔረሰቦች ሃገር መሆኗ ውበታችን፣ ድምቀታችን፣ የአንድነታችን ሃይል፣ የሉአላዊነታችን ማረጋገጫ ነውና ይህንኑ በተሻለ መንግሥታዊ አስተዳደር እናስተካክለው ለማለት የቅንጅትን ዓላማ ለማወቅ የመጣ ነው:: የቀስተደመናም አርማ ይህንኑ



ያመለክታል::



በዕለቱ ስብሰባውን በመሃል ወንበርነት የመራሁት እኔ ስለ ነበርኩ የመጀመርያውን ምሬት የሞላበትን ንግግር አቀረብኩ::

«መኖር ለምን አስፈለገን? ምኞታችን ካልተሟላ መኖር እራሱ ምን ትርጉም አለው? ለመሰቃየት መኖር? ለመጨነቅ መኖር? በሃሳብ ነጋ መሸ ለመጨነቅ? እንዲህ አይነቱን ኑሮ ታዲያ ኑሮ ብለን ልንኖርበት የሚገባን ነው? ለመኖር የሚያስፈልጉንን ለማግኘት፤ ለኑሮ ምቾት የሚሆነንን ለማስተካከል፤ ኑሮ የሚጠይቀውን ለማስተካከል፤ እኛም ሰው ከሚባለው ፍጡር ወገን ነንና፤ እኛም ኢትዮጵያዊ የሚለው የዜግነት መጠርያ የተሰጠን ነንና፤ እኝም አዋጅ ከሚወጣላቸው፤ መመርያ ከሚደነገግባቸው ወገን ነንና፤ እኛም አዋጅ ከሚታወጅባቸው አካል ነንና፤እኛም ኑሮን ለመኖር መብቱ ሊኖረን ይገባል::

ኑሮ፤ስንል፤ደሞ፤የተመቻቸ፤የተደላደለ፤እንደሰው ነታችን፤እንደ፤ኢትዮጵያዊነታችን ድርሻችን፤ የዜግነት ድርሻችን ሳያንስ ሳይበዛ ሊቀረጥልን ይገባል:: ይህ ሲነፈገን ደሞ ለዚህ የዜግነትና የሰብአዊነት መብታችን መታገልን፤ መጠየቅን፤ የሚከለክል አንድም ደንብ የለም::ባይኖርም ግን እራሳችን በራሳችን ለራሳችን በፈጠርነው ፍርሃት ተተብትበን ስለችግራችን፤ ኑሮ ስለ